# የልጆች መጽሐፍ ቅዱስ

ከብሉይና ከአዲስ ኪዳን የተውጣጡ ታሪኮች፣
ፓት አሊክሳንደር እንደተረካቸው

መግለጫዎች በሊንደን ኢቫንስ

አዘጋጅና አሣታሚ
ሣህለ ጥላሁን
አዲስ አበባ 1992 ዓ.ም.

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All right reserved
1992 (1999 እ.ኤ.አ.)

ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው:-
"The Lion Children's Bible"
By Pat Alexander
copyright 1981

አሳታሚ ሣህለ ጥላሁን
አዲስ አበባ

<u>ማሳሰቢያ:-</u>

አዘጋጁ ይህን የትርጉም መጽሐፍ ለልጆች ሲያቀርብ የመጀመሪያ ጊዜው ስለሆነ አስተያየታችሁን በመ.ሣ. ቁ. 10817 አዲስ አበባ እንድትልኩለት በታላቅ ትሕትና ያሳስባል::

# ምሥጋና

በዘላለም ፍቅሩ የወደደን እግዚአብሔር እኛን ደካሞችን ለሥራው ይመርጥና የሚረዱንን ከጎናችን ያስቀምጣል:: ይህም የሚሆነው እንዲሁ ነው::

ይህን የልጆች መጽሐፍ ቅዱስ ለማሳተም በጣም ተጨንቄ በነ(ረበት ሰዓት፣ ከጎኔ ሳይለዩ በጸሎት፣ በተለይም ውድ ጊዜአቸውን በመስጠት የአሳብና ያላሰለሰ ጥረትና ማበረታታት ያደረጉልኝን የወርልድ ቪዥን ኢስት አፍሪካ ሪጂናል ዳይሬክተር  አቶ ሙሉ ጌታ አበበን፣ ናሽናል ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ወ/ሚካኤልን፣ ስቲዋርድሽፕ ዲሬክተር ዶ/ር መልሳቸው መስፍንና የሥራ ባልደረባቸውን አቶ መኮንን አነጋን ከልብ እያመሰገንሁ እግዚአብሔር አምላካችን እናንተንና ቤተሰባችሁን እንዲባርክ ልመናዬ ጽኑ ነው::

እንዲሁም÷ ይሀ መጽሐፍ ለወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጥቅም እንዲውል ውድ ጊዜአችሁን በመስጠት በአሳብ፣ በእርማትና ስለ መጽሐፉ ገንቢ አስተያየት የሰጣችሁኝ የቃለ ሕይወት÷ የመካነ ኢየሱስ፣ የገነት፣ የሙሉ ወንጌል፣ የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ፣ አቶ አይዲቆ አየለ፣ አቶ ኩርሲ ሸፈኖ÷ አቶ ሰለሞን ተካ፣ አቶ ማሞ ገ/መስቀል፣ አቶ ሙሉጌታ ዘውዴ፣ አቶ ደረሰ ብሩ፣ ወ/ሮ ተናኜ ለማ፣ ዶ/ር አታላይ ዓለም፣ አቶ ንጋቱ ገ/መድ ኅን፣ ወ/ሮ ብጽአት ትርፌ፣ መጋቢ አሸብር ከተማ፣ አቶ ታምራት ደለለኝ፣ አቶ ተመስገን ሣህለ፣ አቶ ታዬ ንጋቱ፣ አቶ ሚሊዮን በለጠ፣ ወ/ሮ አበራሽ ታከለ፣ አቶ ሚናስ ብሩክና አቶ ዘነበ ገብረሃናን ከልብ እያመሰገንሁ፤ ጌታ ይባርካችሁ እላለሁ::

የሥራ ድጋፍ ካደረጉልኝ መካከል ጽሑፉን በኮምፒዩተር በመጻፍና በማቀነባበር የረዳችኝን ወ/ሮ አልማዝ ወርቁን፣ የንግድ ማተሚያ ቤት ኃላፊዎችንና ሠራተኞችን ላደረጉልኝ ቅንና ልባዊ ትብብር ከልብ እያመሰገንሁ፣ ሌሎችም በዚህ ጽሑፍ ስማችሁን ያልጠቀስኩት በአሳብና በጸሎት ከጎኔ በመቆም ድጋፋችሁን የሰጣችሁኝን ጌታ ኢየሱስ አብዝቶ ይባርካችሁ እላለሁ::

# ማውጫ

## የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ


| ብሉይ ኪዳን | ገጽ |
|---|---|
| በመጀመሪያ | 11 |
| አዳምና ሄዋን | |
| የኖህ ጀልባ | 13 |
| የባቢሎን ግንብ | 17 |
| አብርሃምና ሎጥ | 19 |
| የይስሐቅ ፈተና | 22 |
| ሚስት ለይስሐቅ | 24 |
| የያዕቆብ ታሪክ | 27 |
| ዮሴፍና ወንድሞቹ | 33 |
| ሙሴ የእግዚአብሔርን ጥሪ ሰማ | 41 |
| ፈርኦን እምቢ አለ | 44 |
| የመቅሰፍቶቹ ታሪክ ከግብፅ አገር መውጣት | |
| መና በምድረ በዳ | 48 |
| የእግዚአብሔር አሥር ሕጎች | 51 |
| የእግዚአብሔር ልዩ ድንኳን | 54 |
| አመፅ | 59 |
| አሥራ ሁለቱ ሰላዮች | |
| ረአብና ሰላዮቹ | 62 |
| ኢያሪኮ የምሽግ ከተማ | 64 |
| እስራኤል በተስፋይቱ ምድር | 67 |
| የጌዴዎን ሦስት መቶ ሰዎች | 70 |
| ጉልበተኛው ሶምሶን | 73 |
| ሩት ከቤቷ ወጣች | 76 |
| የሐና ሕፃን | 79 |
| ንጉሥ አንጋሹ ሳሙኤል | |
| እረኛው ልጅና ግዙፉ | 87 |
| ዳዊትና ጎልያድ | |
| ዳዊትና የንጉሡ ወንድ ልጅ | 91 |
| የዳዊትና የዮናታን ታሪክ | |
| ንጉሥ ዳዊት ሺህ ዓመት ይንገሥ | 95 |
| ዳዊትና ቤርሳቤህ | |
| ነቢዩ ናታን | |
| የአቤሴሎም አመፅ | |
| ጠቢቡ ሰሎሞን | 101 |
| የሳባ ንግሥት | |
| ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤት ሠራ | 105 |
| ኤልያስና የበዓል ነቢያት | 109 |
| ንጉሥ አክአብና የወይን ቦታው | 115 |
| የኤልሳዕ ታሪኮች | 117 |
| የሱነሙ ቤት | |
| የንዕማን ታሪክ | |
| ኢዮአስ ወጣቱ ንጉሥ | 123 |
| የሰሜኑ ወራሪ | 127 |
| ንጉሡ ሕዝቅያስና ነቢዩ ኢሳይያስ | |
| ኢዮስያስ ያገኘው ነገር | 133 |
| ኤርምያስና የኢየሩሳሌም ውድቀት | 136 |
| ሕዝቅኤልና ግዞተኞቹ | 142 |
| የዳንኤል ታሪክ | 145 |
| የወርቁ ምስል | |
| የብልጣሶር ድግሥ | |
| ዳንኤል በአንበሳ ጉድጓድ | |
| እንደገና በኢየሩሳሌም | 152 |
| ዕዝራና ገዥው ነህምያ | |
| የከሸፈው አድማ | 158 |
| የንግሥት አስቴር ታሪክ | |
| ኮብላዩ | 162 |
| የዮናስ ታሪክ | |


## የኢየሱስና የተከታዮቹ ታሪክ


| | |
|---|---|
| አዲስ ኪዳን | 165 |
| ልጃገረዲቱ ማርያም | 166 |
| 'ስሙ ዮሐንስ ነው' | **168** |
| መጥምቁ ዮሐንስ | |
| በበረት የተወለደው ንጉሥ | 171 |
| እንግዶችና ኮከብ | 175 |
| 'የጠቢባኑ ታሪክ' | |
| ልጁ በቤተ መቅደስ | 179 |
| የንጉሡ አዋጅ ነጋሪ | 181 |
| ኢየሱስ ወደ ሠርግ ቤት ሄደ | 185 |
| አሥራ ሁለቱ ጓደኞች | 186 |
| ከበር ውጭ የተሰጡ ትምህርቶች | 188 |
| 'የተራራው ስብከት' | |
| ሽባው ሰው | 193 |
| ማዕበሉ | 195 |
| የኢየሩሳሌም ጉዞ | 196 |
| የሰንበቱ ችግር | 199 |
| የንጉሡ ሄሮድስ የልደት በዓል | 201 |
| እምነትና የኃጢአት ይቅርታ | 202 |
| መልካሙ እረኛ | 204 |
| ከሞት መነሳት! | **206** |
| የእግዚአብሔር መንግሥት | 208 |
| የተራቡት ሰዎች | 211 |
| ኢየሱስ 5000 ሰዎችን መገበ | |
| በተራራው ላይ | 212 |
| ሁለቱ ልጆች | 214 |
| ፈሪሳውያንና ጥያቄዎቻቸው | 216 |
| ማርታ፣ ማርያምና አልአዛር | 219 |
| ወደ ኢየሩሳሌም በጉዞ ላይ | 222 |
| በርጤሚዎስና ዘኪዎስ | 223 |
| ንጉሡ በአህያ መጣ | 225 |
| የመጨረሻው መዕድና | |
| አልፎ መሰጠት | 227 |
| የሞት ፍርድ | 231 |
| ከሙታን መነሣት | 236 |
| ነፋስና እሳት | 242 |
| አንካሳው ሰውዬና የተሰጠ ማስጠንቀቂያ | 244 |
| እስጢፋኖስ | 246 |
| ጳውሎስ ከክርስቲያኖች ጋር ተባበረ | 248 |
| ጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ | 250 |
| የጳውሎስ ጉዞዎች | 253 |
| እሥራትና የመርከብ አደጋ | 258 |

# መቅድም

መጽሐፍ ቅዱስ ለልጆች ተወዳጅና አስደሳች በሆኑ ታሪኮች የተሞላ መጽሐፍ ነው:: በዚህ በአዲሱ የልጆች መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ታሪኮች ወላጆችና ልጆች በአንድነት ሆነው ወይም ልጆች ለብቻቸው ሊያነቧቸው እንዲችሉ ግልጽ በሆነና በቀላል አቀራረብ የተጻፉ ናቸው::

የሊንደን ኢቫን ጠንካራ ሥዕላዊ መግለጫዎች ለትናንሽ ልጆች እንኳን ሳይቀር ታሪኩን በሚገባ ለመግለጽና ለማስደሰት የሚችሉ ናቸው::

የመጽሐፉ የጥራዝ መጠን ልጆች በቀላሉ እንዲይዙት በማለት ታስቦ በአነስተኛ መጠን የተዘጋጀ ነው::

ጽሑፉም ለአዲስ አንባቢዎች ግልጽ እንዲሆን ከፍ ባሉ ፊደሎች የተጻፈ ነው:: ታሪኮቹንም በሚመለከት ከመጀመሪያው ከፍጥረት ታሪክ ጀምሮ የአዲስ ኪዳን ሃተታዊ ጽሑፍ መደምደሚያ እስከሆነው እስከ ጳውሎስ የመርከብ አደጋና ሮም ከተማ እስከገባበት ድረስ ያሉት ዋና ዋና ታሪኮች ተካትተዋል::

እነዚህም ታሪኮች የአፈጻጸማቸውን ትክክለኛ ቅደም ተከተል የያዙ ሲሆን፣ እነርሱም ብዛት ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ መጻሕፍት ከሚናገሩለት ከ "አንዱ" ታሪክ ጋር በቅርብ የተዛመዱ ናቸው::

ከእያንዳንዱ ታሪክ ጋር ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ደግሞ በነዚህ ታሪኮች የሚደሰቱ ወጣትም ሆኑ አረጋውያን አንባቢዎች ወደ መጽሐፍ ቅዱሳቸው ሄደው ሙሉውን ታሪክ እንዲያገኙት የሚረዳቸው ነው::

# መግቢያ

በአገራችን ልጆች እጅግም ትኩረት አይሰጣቸውም:: በአንዳንድ ቤተሰቦች በተለይም በገጠሩ አካባቢ ልጆች የሚበሉት ከወላጆቻቸው ማዕድ የተረፈውን ፍርፋሪ ነው:: ልጅ አይራበው እንጂ እየተባሉ ጥብቆ ቢጤ የሚገዛላቸውም በዓመት አንድ ጊዜ ነው:: ይህ ለልጆች የሚሰጠው አነስተኛ ግምት በመንፈሳዊውም ዓለም ተንፀባርቆ ልጆች ከዕድሜያቸውና ከአእምሮ ብስለት ደረጃቸው ጋር የሚመጥን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት አያገኙም:: ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ የሰጠው ሕያው ቃል ቢሆንም ከቋንቋ አንፃር ከልጆች መረዳትና ግንዛቤ ጋር እንዲጣጣም ሆኖ የቀረበ ባለመሆኑ የልጆችን ለእግዚአብሔር ያላቸውን ጥማት የሚገታ ይመስላል::

የልጆች የሰንበት ትምህርት ቤት መጻሕፍትን በማሳተምና በማሰራጨት እንዲሁም በማሰልጠን የረጅም ጊዜ ልምድ ያካበቱት አቶ ሣህለ ጥላሁን መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ በመረዳት በኩል ልጆች ያለባቸውን ችግር እንደሚገባ ስለተገነዘቡ ለልጆች መረዳት በሚመጥን ቋንቋና አገላለጽ የተዘጋጀውን ይህንን የልጆች መጽሐፍ ቅዱስን ተርጉመው በማቅረባቸው ልጆች የእግዚአብሔር ቃል ፍቅር እንዲያድርባቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: . . . ::

አቶ ሚናስ ብሩክ

## የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ

# ብሉይ ኪዳን

ከመጀመሪያው እንጀምራለን፤ ዓለም ራሱ ከመፈጠሩ በፊት በመጀመሪያ እግዚአብሔር ነበረ፤ እርሱም ዓለምንና በውስጡ ያሉትን ሁሉ ፈጠረ፤ የመጀመሪያዎቹን ሰዎች ፈጠረ፤ በኋላም ነገሮች እየተበላሹ ሲመጡ እግዚአብሔር መፍትሄውን አዘጋጀ፤

አንድን ሰው መረጠና በእርሱ በኩል ሕዝብን መረጠ፤ ከዚያም ሕዝብ መካከል አዳኝን መረጠ:: መጽሐፍ ቅዱስ በርካታ እጅግ አስገራሚ ታሪኮችን የያዘ ነው:: ደግሞም እርሱ አንድ ታሪክ ነው::





# በ መ ጀ መ ሪ ያ

## ዘፍጥረት 1–4



በድሮ ጊዜ ገና በመጀመሪያ እግዚአብሔር
ዓለማችንን ፈጠረ፡ ፀሐይ ቀን እንድታበራ ሠራት፣
ለሌሊት ደግሞ ጨረቃንና ከዋክብትን ፈጠረ፡
ሰማይንና ምድርን ባሕርንም ፈጠረ፡ ወፎች በሰማይ
እንዲበርሩ፣ ዓሣ በባሕር ውስጥ እንዲዋኙና እንስሶች
ደግሞ በመሬት ላይ እንዲሆኑ ፈጠራቸው፣ እግዚአብሔር
የፈጠራቸውን ሁሉ ተመለከተና በጣም ደስ አለው፡ ዓለም
ለሰዎች ዝግጁ ሆነች፡ ስለዚህ እግዚአብሔር አንድ ወንድና
አንድ ሴትን ፈጠረ፣ እነርሱም አዳምና ሄዋን ናቸው።

እግዚአብሔር አዳምንና ሄዋንን በዓለም ላይ አለቃ አድርጎ
አስቀመጣቸው። ይኸውም አትክልቶችንና ዛፎችን፣ ወፎችንና
ዓሣዎችን፣ እንስሶችንም እንዲጠብቁ ነው፡ ደግሞም እጅግ ደስ
የሚያሰኝ የመኖሪያ ቦታን ሰጣቸው። በዚህ ቦታ ቀዝቃዛ ወን
ዞች፣ የጥላ ዛፎችና እንዲሁም የተለያዩ የሚበሉ ፍሬዎች ነበሩ፡
ይህ ቦታ የኤደን ገነት ይባል ነበር።

አዳምና ሄዋን በጣም ደስተኞች ነበሩ፡ እግዚአብሔር በፍጹም
አታድርጉ ያላቸው አንድ ነገር ብቻ ነበረ። አንድ ልዩ የሆነች
ዛፍ ፍሬዋን እንዳይበሉ ተከልክለው ነበር። እርሷም መልካምንና
ክፉን የምታሳውቅ ዛፍ ነበረች። ከበሉ ግን እንደሚሞቱ እግዚአ
ብሔር ነገራቸው። ስለዚህ አዳምና ሄዋን የእግዚአብሔር
ወዳጆች ሆነው ይኖሩ ነበር፡ ትእዛዙንም ይፈጽሙ ነበር።

ዳሩ ግን እግዚአብሔር የሠራውን ዓለም ለማበላሸት
የሚፈልግ አንድ ወገን ነበር፡ ከዕለታት አንድ ቀን ሄዋን
በዚያች መልካምንና ክፉን በምታስታውቅ ዛፍ አጠገብ ስታልፍ
ለስለስ ያለውን የእባብን የሹክሹክታ ድምፅ ሰማች፤

"ይህች ፍሬ እንዴት እንደምታምር ተመልከች፡ አፍሽን
ምራቅ አልሞላውም? ለምን አትሞክሪአትም ይህች ፍሬ በጣም
ጠቢብ ታደርግሻለች፡ ብትበያት ልክ እንደ እግዚአብሔር
ብልህ ትሆኚአለሽ" አላት። ሄዋንም የእባቡን ለስላሳ ድምፅ
አዳመጠች።



ወደ ፍሬዋም ተመለከተች፤ ከዚያም እግዚአብሔር እንዴት መልካምና ርህሩህ እንደሆነ ረሳች:: እንደ እግዚአብሔርም ብልህ ለመሆን ፈለገች፤ የወደደችውንም ለማድረግ ፈለገች::

ሄዋንም እጇን ዘረጋችና ፍሬዋን ቀጠፈች:: እርሷም መብላት ጀመረችና ለአዳምም ግማሹን ሰጠችው::

ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ነገሮች ሁሉ መበላሸት ጀመሩ:: እግዚአብሔርም አዳምና ሄዋን ያደረጉትን ነገር አወቀ:: ማንም ከእርሱ አንዳች ነገርን መደበቅ አይችልም:: ከዚያ በኋላ አዳ ምና ሄዋን የእግዚአብሔር ወዳጅ ሊሆኑ ስላልቻሉ ከፊቱ አባረራቸው:: እየተደሰቱ ከእግዚአብሔር ጋር እየተራመዱና እየተነጋገሩ የሚኖሩበትን የኤደንን ገነት ትተው መሄድ ግድ ሆነባቸው:: ከዚያ በኋላ ወደዚያ ቦታ እንዳይመለሱ ሰይፍ የመዘዘ መልአክ ጠባቂ ሆኖ ተመደበ::

አሁን ሰውነታቸው እስኪደክም ድረስ ከባድ ሥራ መሥ ራት ግድ ሆነባቸው፤ ስቃይ ምን እንደሆነ አወቁ፤ ከሁሉም የባሰው ደግሞ የእግዚአብሔር አስፈሪ ማስጠንቀቂያ ተፈጸመባ ቸው፤ ይኸውም በሸመገሉ ጊዜ እንደሚሞቱ አወቁ:: የኤደንን ገነት ከለቀቁ በኋላ አዳምና ሄዋን ቃየልና አቤል የተባሉ ሁለት ወንዶች ልጆችን ወለዱ፤ ልጆቹም ባደጉ ጊዜ ቃየል መሬትን የሚያርስና እህልን የሚዘራ ገበሬ ሆነ፤ አቤል ደግሞ የአባቱን መንጋ የሚጠብቅ እረኛ ሆነ፤ በእህል መሰብሰቢያ ጊዜ ቃየል ካገኘው እህል ለእግዚአብሔር ስጦታን አቀረበ፤ ይህም ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረቡ ነበር፤ አቤል ደግሞ ከበጎቹ ጠቦቶች አንዱን ለእግዚአብሔር ሰጠ፤ ስጦታዎቹ በእርግጥ መልካም ነበሩ፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን ፍቅር በስጦታ መግዛት አንችልም:: እርሱ ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆንን ይመለከታል::

አቤል መልካም ሰው ነበረ፣ ስለሆነም እግዚአብሔር በአቤል ስጦታ ተደሰተ:: ቃየል ግን ቀናተኛና ቁጡ ሰው ነበረ፤ ወንድሙን አቤልን በጥላቻ ተመለከተው፤ በእርሱ ስጦታም እግዚአብሔር እንዳልተደሰተበት ተረዳ::

ከዕለታት አንድ ቀን ቃየል አቤልን በሜዳ ላይ ሳሉ ገደለው:: ማንም ያላየው መሰለው:: እግዚአብሔር ግን ያደረገውን ነገር አውቆአል:: እግዚአብሔርም ቃየልን ለዘላለም ከቤቱና ከቤተሰቡ አውጥቶ በማባረር ቀጣው፤ በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር የፈጠረው መልካም ምድር እየተበላሸ መጣ::





# የኖህ ጀልባ

ዘፍጥረት 6–9

ብዙ ዘመን አለፈ፤ ብዙ ሰዎች ተወለዱ፤ እነርሱም ልጆችን ወለዱ፤ ከዚያም በኋላ ሞቱ:: በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር በፈጠረው ዓለም ነገሮች ሁሉ ብልሽታቸው እየተባባሰ ሄደ፤ ሰዎች እርስ በርሳቸው ይዋጉ ጀመር:: እርስ በርሳቸው ይጣሉና ይጎዳዱ ጀመር፤ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ፈቃዱም ግድ አልነበራቸውም፤ እርሱን የሚሰማው ስለጠፋ ሰውን በመፍጠሩ አዘነ፤ አንድ አማራጭ ብቻ ነበረው፤ በአዲስ ሰው እንደገና መጀመር ግድ ሆነበት:: በጣም እያዘነ በምድር ላይ የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ ለመደምሰስ ወሰነ፤ ታላቅ ጎርፍ ለማምጣት ወሰነ::



ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆነ አንድ መልካም ሰው ነበረ፤ ስሙም ኖህ ይባል ነበር:: እግዚአብሔርም ለኖህ ስለ ጎርፉ ጉዳይ ነገረውና ወደፊት ሊያደርግ ያሰበውን ገለጸለት፤ እርሱም ኖህንና ቤተሰቡን ለማዳን ፈለገ፤ እግዚአብሔርም ኖህን ትልቅ ጀልባ እንዲሠራ አዘዘው፤ ይህም ጀልባ ኖህንና ሚስቱን ሦስቱንም ልጆ ቹን ካምን፣ ሴምንና ያፌትን ከነሚስቶቻቸው እንዲሁም ደግሞ ከእያንዳንዱ የእንስሳትና የአእዋፍ ዓይነት ሁለት ሁለት ለመያዝ የሚችል በጣም ትልቅ ጀልባ መሆን ነበረበት:: ደግሞም ለሁሉም ለረጅም ጊዜ የሚበቃቸ ውን ምግብ ለመያዝ ቦታ ያለው መሆን ነበረበት፤ ኖህም ይህን ሁሉ በጥንቃቄ አደመጠና ልክ እግዚአብ ሔር እንዳዘዘው አደረገ::





ሰዎችም ጀልባውን ሲሠራ ለማየት ይመጡ ነበር፡ ሥራውም በጣም ረጅም ጊዜ የሚወስድ ነበረ፣ በየቀኑም ሰዎች የሚሠራውን ሲጠይቁት እግዚአብሔር ስለ ጎርፉ የተናገረውን ይነግራቸው ነበር፣ ዳሩ ግን ምንም አላሰቡበትም ነበር። ኖህም አእምሮ የሌለው ነው ብለው አሰቡ፣ መሆን አለበት፣ እንዲህ ያለ ያማረ ጀልባ ከባህር ሩቅ በሆነ በደረቅ ሜዳ መሥራት ምንድን ነው ብለው ተገረሙ፡ ኖህን ግን ሥራውን ሊያስቆሙት አልቻሉም። ሥራውን ቀጠለና በመጨረሻም የጀልባው ሥራ ተፈጸመ፣ ከዚያም ዝናብ መጣ። በዚያም ቀን እግዚአብሔር እንዳዘዘው ኖህና ቤተሰቡ እንዲሁም ወፎቹና እንስሶቹ ሁሉ ወደጀልባው ውስጥ ገቡ። እግዚአብሔርም ከበስተኋላቸው መዝጊያውን አጥብቆ ዘጋው።





ዝናቡ ያለማቋረጥ ወረደ፤ በየቀኑም መዝነቡን ቀጠለ፣ ወዲያውም ወንዞቹ ሁሉ ሞልተው ውሀው በምድር ላይ መንጣለል ጀመረ፣ ወደ ጀልባውም ደረሰ፤ ውሃው በጀልባው ዙሪያ ከፍታው እያደገ መጣ። ጀልባውንም ወደ ላይ አነሳውና ኖህና ቤተሰቡ መንሳፈፍ ጀመሩ። ዝናቡ እየቀጠለ ሲዘንብ ውሀው ወደ ላይ እያደገ በሄደ መጠን ሁሉም ነገር ተሸፈነ፤ አንድም ሰው አንዳችም ነገር ሊተርፍ አልቻለም፤ የተራሮችም ጫፍ እንኳን ሊታዩ አልቻሉም። በሕይወት ሊተርፉ የቻሉት ኖህና ቤተሰቡ እንዲሁም ከእነርሱ ጋር በጀልባው ውስጥ የነበሩት እንስሶች ብቻ ነበሩ። ባዶና ብቸኛ የሆነ ዓለም ቀረ።

በመጨረሻ ዝናቡ ቆመ፤ ቀስ በቀስ ውሀው እየጎደለ ሲሄድ በመጨረሻ ጀልባው በተራሮች መካከል አረፈ፤ ኖህም ከጀልባው ለመውጣት እንዲቻል መሬቱ ደርቆ እንደሆነ ለማወቅ ፈለገ፣ መስኮቱንም ከፈተና ቁራን ሰደደው፤ ቁራው ግን ሳይመለስ ስለቀረ እንደገና ርግብን ሰደዳት፤ ነገር ግን ደረቅ መሬት ገና ስላልነበረ ርግቧ ወደ ኖህ ስትመለስ ኖህ መልሶ አስገባት። እንደገና ሌላ ጊዜ ርግቧ በሄደች ጊዜ ከወይራ ዛፍ አረንጓዴ ቅጠል ይዛ ተመለሰች። በዚህ ጊዜ ኖህ መሬቱ በመድረቅ ላይ እንዳለ ሊወቀ፤ ለሦስተኛ ጊዜ ርግቧ ወጣችና እንደገና አልተመለሰችም። ወዲያውም ኖህ የደረቀውን መሬት ራሱ ተመለከተ።



ከዚያም እግዚአብሔር ለኖህ ሁላቸውም ከጀልባው ወጥተው በአዲሱ ዓለም ውስጥ በአዲስ መልክ ኑሮ መጀመር እንዳለባቸው ነገረው፡ እንስሶቹና ሰዎቹ በደረቁ መሬት ላይ ለመርገጥ ጓጉተው ከጀልባው ለመውጣት አንዱ በአንዱ ላይ ተረባረቡ፡ ይህ እንዴት ደስ የሚል ጊዜ ነበረ! ኖህና ቤተሰቡም እየሳቁና እየጮኹ በሩጫ ወጡ፡ ከዚያም እግዚአብሔር በደህና ስለጠበቃቸው አመሰገኑት።

ደግሞም ሥጋን በመጥበስ ለእግዚአብሔር ልዩ የሆነ የምስጋና ስጦታ ለማቅረብ ድንጋይ ከምረውና እንጨትን በላዩ ረብርበው መሠዊያን ሠሩ፡ ከዚያም ፀሐይ በኃይል በወጣች ጊዜ ውብ የሆነ ቀስተ ደመና እንደ መታጠቂያ በሰማይ ላይ ታየ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ዳግመኛ ምድርን ለማጥፋት ጎርፍ እንደማያመጣ ለኖህ ቃል ገብቶለት ስለነበረ ነው፡ ቀስተ ደመናውም እግዚአብሔር ለዘላለም የተስፋ ቃሉን እንደሚጠብቅ ሰዎች ሁሉ እንዲያዩ ምልክት ነበረ።





# የባቢሎን ግንብ

**ዘፍጥረት** 10–11

ከታላቁ ጎርፍ በኋላ ኖህና ልጆቹ መሬት አርሰው የወይን አትክልትን ተከሉ፤ እነርሱም ልጅችና የልጅ ልጅች ነበሩአቸው፤ ብዙም ሳይቆይ ሰዎች እጅግ ከመብዛታቸው የተነሣ አንዳንድ ቤተሰቦች ለእንስሶቻቸው መሰማርያ ለምለም ሣርን ለማግኘት መለየት ግድ ሆነባቸው፤


ሆኖም እስከዚያ ጊዜ ድረስ ሁሉም አንድ ዓይነት ቀላል ቋንቋ ይናገሩ ስለነበር እርስ በርሳቸው ይግባቡ ነበር፤ በሕብረት እያቀዱ በሕብረት ለመሥራት ይችሉ ነበር።

አንዳንዶቹ በባቢሎን ሜዳዎች ላይ መኖር ጀመሩ፡ ጡብን እየሠሩ እንዲጠነክርላቸው በእሳት ማቃጠልን ተማሩ፤ ደግሞም ሸክላውን /ጡቡን/ በአንድ ላይ ለማያያዝ በሬንጅ መጠቀምን ተማሩ፤ አሁን ደምበኛ ግምበኞች ሆኑ።

ከዕለታት አንድ ቀን አንዱ እንዲህ አለ፦ "ለራሳችን ከተማ እንሥራ፣ ደግሞም ከዚህ በፊት ተሠርቶ ያልታወቀ ረጅም ግንብን እንሥራ፤ በዚህም ዝነኞዎች እንሆናለን።" ሁሉም በዚህ ሃሳብ ተስማሙና በኃይል ይሠሩ ጀመር፡ የባቢሎንን ግንብ መሥራት ጀመሩ።

እግዚአብሔርም ሥራቸውን ተመለከተ፤ ግንቡ እያደር ከፍ ከፍ እያለ ሲሄድ አየ፤ የሰዎቹም ሃሳብ እያደገ መሄዱን አየ፤ ይህም ችግር እንደሚያመጣ ያውቅ ነበር፡ ሰዎች የሚያቅታቸው ነገር እንደሌለ ማሰብ ጀመሩ፡ እነርሱ አማልክት እንደሆኑ ማሰብ ጀመሩ።

ስለዚህ እግዚአብሔር ግንቡ እስኪያልቅ ድረስ መቆየት አልቻለም፡ ሰዎች መቼም የተለያየ ቋንቋ ከተናገሩ ሊግባቡ አይችሉም፤ አብሮ ለመሥራትም አስቸጋሪ ይሆናል፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ቋንቋቸውን ደበላለቀና በዓለም ላይ ወደተለያዩ ቦታዎች በታተናቸው።



ወደ ሰሜን፣ ወደ ደቡብ፣ ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ሁሉ ሄዱ። አንዳንዶቹ ከሚዲትራኒያን ባሕር በስተምሥራቅ በኩል ባለው ዳርቻና በደሴቶች ተቀመጡ።

አንዳንዶቹ ደግሞ በግብፅ አገርና በሌላው የአፍሪካ ክፍል ተቀመጡ፤ ሌሎቹም ወደ አሦርና ወደ አረብ አገር ሄዱ፤ ከኖህ የተወለዱት ቤተሰቦች በየአገራቸው ትልቅ ሕዝብ ሆኑ፤ እያንዳንዱም ሕዝብ የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪ ሆነ፤ ከዚያ በኋላ እንዲህ በቀላሉ በሕብረት ማቀድና መሥራት አልቻሉም፤ በኋላም ስለ ባቢሎን ግንብ በሚያወሩበት ጊዜ በድንገት እንዴት ቋንቋቸው እንደተደባለቀና እንደተለያየ ያስታውሱ ነበር።



# አብርሃምና ሎጥ

## ዘፍጥረት 11–13፣18–19

በከለዳውያን አገር በኡር ከተማ አብርሃም የሚባል ሰው ይኖር ነበር። የሚስቱም ስም ሣራ ነበር፤ ከዕለታት አንድ ቀን እግዚአብሔር ለአብርሃም እንዲህ አለው:–

"የኡር ከተማን ትተህ ሩቅ ወደ ሆነው ወደ ከነዓን አገር እንድትሄድ እፈልጋለሁ፤ ይህንን ከፈጸምህ የብዙ ሕዝብ አባት አደርግሃለሁ።"

ሆኖም አብርሃምና ሣራ ልጆች አልነበሯቸውም። ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ላይ ታመኑና ያላቸውን አደረጉ፤ የአብርሃምን ዘመድ ሎጥን እንዲሁም አገልጋዮቻቸውንና መንጋዎቻቸውን ሁሉ ይዘው ከኡር ተነሱ፤ ቤተሰባቸውን፣ ቤታቸውንና ጓደኞቻቸውን እንዲሁም በደምብ የሚያውቋቸውን ሰዎችና ሥፍራቸውን ትተው ወደማያውቁት አገር ሄዱ፤ ጉዞአቸው በቀስታና መንገዳቸውም ረጅም ቢሆንም በመጨረሻ ግን ደረሱ። ድንኳናቸውንም በኬብሮን አጠገብ ባለው በመምሬ ተከሉና ለብዙ ጊዜ አብረው በደስታ ይኖሩ ነበር። ዳሩ ግን ከብቶቻቸውና መንጋዎቹ እየበዙ ሲሄዱ ለሁሉም የሚበቃ ውሃና ሣር አልተገኘም፤ ከዚህ የተነሣ በአብርሃም ከብቶች ጠባቂዎችና በሎጥ ከብቶች ጠባቂዎች መካከል ፀብ ሆነ፤

ስለዚህ አብርሃምና ሎጥ ለመለያየት ወሰኑ፤

አብርሃም ሎጥ የሚፈልገውን እንዲመርጥ የመጀመሪያውን ዕድል ሰጠው፤ ሎጥም ከኮረብቶቹ በታች ያለውን ከሰዶም ከተማ አቅራቢያ የዮርዳኖስ ወንዝ ሸለቆ የሆነውን ልምላሜ ያለውን ቦታ መረጠና ወደዚያ ለመሄድ ወሰነ፤ በዚያ ቦታ ለመንጎቹ የሚሆን ብዙ ውሀና መልካም ሣር ያገኛል፤ ሎጥም ወደዚያ ሄደ፤ በዚህ ምክንያት አብርሃም ብዙ ውሀ በሌለበትና ሣሩም ስስና ደረቅ በሆነበት በኮረብታው አካባቢ መቀመጥ ግድ ሆነበት፤

ዳሩ ግን ሸለቆው መልካም ቢመስልም ሎጥ ያደረገው ምርጫ የተሳሳተ ነበር፤

በሰዶም የሚኖሩት ሰዎች ትዕቢተኞች ስስታሞችና ሰነፎች ነበሩ፣ ደግሞም ግትሮች፣ ጨካኞችና ፀብን የሚወዱ ነበሩ፤ በሰዶም አስጸያፊ ሥራ የሚሠሩ የነበረ ቢሆንም በዚህ የሚያዝንና ጸጸት የሚሰማው ሰው ፈጽሞ አልነበረም::

እግዚአብሔር ግን ትክክለኛ ፈራጅ ነው፤ ስህተት የሚያደርጉትን ሰዎች ዝም ብሎ አይመለከትም:: የሰዶም ከተማ ቅጣት የሚገባት ሆና ተገኘች::

ከዕለታት አንድ ቀን በቀትር ሰዓት አብርሃም በድንኳን ውስጥ አርፎ ሳለ ሦስት እንግዶች ወደ እርሱ ሲመጡ አየ፤ እርሱም ሰላምታ አቀረበላቸውና በድንኳኑ ውስጥ አርፈው ከእርሱ ጋር ምግብ እንዲበሉ ጋበዛቸው:: ሣራና አገልጋዮቹ ምግቡን ሲያዘጋጁ ታላቅ ችኮላና ጥድፊያ ሆነ፤ ትኩስ እንጀራ ጋግረው ጥጃም አርደው ከጠበሱ በኋላ ከወተትና ከአይብ ጋር ለእንግዶቹ አቀረቡላቸው::

ምግቡንም ከበሉ በኋላ ሰዎቹ የመጡበትን ምክንያት ተናገሩ፤ አብርሃምና ሣራ በዚህ ጊዜ በዕድሜ ቢሸመግሉም እግዚአብሔር ለእነርሱ መልካም ዜና ነበረው:: ብዙ ሳይቆዩ ያ ሲመኙት የነበረው ልጅ ሊወለድ ነው፤ እንዴት የሚያስደንቅና የሚያስደስትም ዜና ነው!







ዳሩ ግን ሰዎቹ በኋላ የተናገሩት ነገር አሳዘናቸው፤ ሎጥ አሁን የሚኖርበት ከተማ ሰዶም እንደምትጠፋ እግዚአብሔር ተናገረ:: በሰዶም ያሉት መልካም ሰዎች ሎጥና ቤተሰቡ ብቻ ነበሩ፤ ስለዚህ ሎጥ ሳይዘገይ ከዚያ እንዲሸሽ ለማስጠንቀቅ እግዚአብሔር መልእክተኞችን ላከ::

ዳሩ ግን የሎጥ ቤተሰቦች ከሰዶም ለመውጣት አልፈለጉም፤ ጊዜው ሲደርስ ግን የእግዚአብሔር መልእክተኞች እነርሱን ከከተማው እንዲወጡ አስቸኮሏቸው:: ገና ብዙ ሳይርቁ ታላቅ የሰማይ ስግምግም ሆነ፤ ምድሪቱ ተንቀጠቀጠች ተርገበገበች፤ በሰዶምና በአካባቢዋ ባሉት ከተሞችና መንደሮች ላይ እሳትና አመድ ዘነበ፤ አየሩ በአቧራ ተሞላ፤ ቢሆንም ግን የሎጥ ሚስት በፍጥነት መውጣት አልቻለችም:: ቆማ ስትመለከት ወዲያው ተገደለች፤ ሎጥና ሁለቱ ሴቶች ልጆቹ ብቻ አመለጡ:: እግዚአብሔር ሕይወታቸውን አተረፈው::

# የይስሐቅ ፈተና

**ዘፍጥረት** 21–22



እግዚአብሔር አብርሃምን ከኡር እንዲወጣ ሲነግረው ለታላቅ ሕዝብ አባት እንደሚሆን ቃል ገብቶለት ነበር፡ እርሱም ለአብርሃም ልጅ እንደሚሰጠውና የሰማይ ከዋክብት እንደማይቆጠሩ ሁሉ የእርሱም ትውልድ እንደማይቆጠር ተስፋ ሰጥቶት ነበር። ለብዙ ዓመታትም በየምሽቱ አብርሃም ወደ ሰማይ ከዋክብት እየተመለከተ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ያስብ ነበረ፡ በመጨረሻም አብርሃምና ሣራ ሸምግለው ተስፋ በቆረጡ ጊዜ ይስሐቅ ተወለደ። ሣራም ሕፃኑን ልጇን በተመለከተች ጊዜ በጣም ከመደሰቷ የተነሣ ሳቀች።

ዓመታት እያለፉ ሲሄዱ ይስሐቅ በቁመቱና በጥንካሬው አደገ፡ ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ሊፈትነው ፈለገ፣ "አብርሃም" ብሎ ጠራውና "በጣም የምትወደውን አንድ ልጅህን ወደ ሞርያም ተራራ ይዘህ እንድትሄድና በዚያ ለኔ መስዋዕት እንድታደርገው እፈልጋለሁ" አለው። አብርሃምም እነዚህን ጭካኔ የተሞላባቸውን ቃላት ማመን አስቸገረው። በውነት ከነዚያ ሁሉ የተስፋ ቃሎች በኋላ ልጁን እንዲሰዋው ፈልጎ ነውን? ቢሆንም አብርሃም ዘወትር እግዚአብሔርን



ማመንና ለእርሱም መታዘዝን ተምሮአልና በሚቀጥለው ቧት ጉዞአቸውን ጀመሩ፡ ይስሐቅ እንጨት ተሸክሞ አብርሃም ደግሞ ቢላዋና የእሳቱን ማያያዣ ፍም ይዞ ነበር።

ለሦስት ቀናት ተጓዙ፡ ጉዞአቸውን ሲጨርሱ አብርሃም ሊያደርግ ያለውን ነገር ማሰብ አቃተው፡ ሆኖም ለይስሐቅ ስለዚህ ነገር ምንም አልነገረውም፡ ወደ ተባለው ቦታ ሲቃረቡ ይስሐቅ እንዲህ አለ፣ አባዬ፣ "ለእግዚአብሔር መስዋዕት ለማቅረብ እንጨቱንና እሳቱን ይዘናል፣ የመስዋዕቱ በግ ታዲያ የት አለ?"

አብርሃምም ምራቁን ዋጥ አደረገና እንዲህ አለው፡– "የመስዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል።" ዳሩ ግን ወደ ቦታው እንደደረሱ መሰዊያ ከሠሩና እንጨቱን በላዩ ከረበረቡ በኋላ አብርሃም የይስሐቅን እጆች አሠረና በላዩ ላይ አጋደመው፡ ልጁንም ሊያርደው ቢላዋውን አነሣ፡

ዳሩ ግን በዚያችው ቅጽበት እግዚአብሔር እርሱን ጠራው፡ "አብርሃም! ተው፡! ልጁን አትንካው፡ ምን ያህል በእኔ እንደም ትታመን አሁን አውቄአለሁ፡ ትእዛዜን ሁሉ እንደምትፈጽም አውቃለሁ፡ ወደ ቁጥቋጦው ውስጥ ተመልከት፡ ቀንዱን የታሰረ በግ ታገኛለህ፣ እርሱን ሰዋው፡"

በዚህ ጊዜ አብርሃም በፍርሃት ላይ ያለውን ልጁን ለቀቀው፡ በምሥጋናና በታላቅ ደስታ በጉን አረዱና በመሰዊያው ላይ ጠበሱት፡ እግዚአብሔርም እጅግ ግሩም የሆኑትን የተስፋ ቃሎች በድጋሚ ተናገረው፡ ምክንያቱም አብርሃም በተፈተነ ጊዜ ለእግዚአብሔር ስለታዘዘ ነው፡



# ሚስት ለይስሐቅ


## ዘፍጥረት 24

ሣራ ሞተች፤ አብርሃምም አሁን በጣም አረጀ፤ ይስሐቅም ሚስት ማግቢያው ደረሰ፤ ዳሩ ግን በዚያ አካባቢ ካሉት ከከነአናውያን ሴቶች ማግባት የለበትም፤ ይስሐቅ ከራሱ ወገኖች ማግባት አለበት፤ አብርሃምና ቤተሰቡ አሁን የሚኖሩት በሩቅ አገር ሲሆን በእግሩ ለመጓዝም በጣም አርጅቶ ነበር፤ ስለዚህ ታማኝ የሆነውን አገልጋዩን ወደርሱ ጠራው፤

"ወንድሜ ናኮር ወደሚኖርበት ወደ ካራን ትሄዳለህ፤ ከዚያም ለልጄ ለይስሐቅ ሚስትን ትፈልግለታለህ፤" አገልጋዩም መለሰና "ልጃገረዲቱስ አልሄድም ብትለኝ ምን አደርጋለሁ፤ ይስሐቅን ወደዚያ ልውሰደውን?"ሲል ጠየቀ።

አብርሃምም መልሶ፣ "የለም በምንም ዓይነት ይህን አታድርግ፤ እግዚአብሔር ይህንን ቦታ ለዘሬ ለመስጠት ቃል ገብቶልኛል" አለው አገልጋዩም ሰዎችንና ግመሎችን እንዲሁም ለልጃገረዲቱና ለቤተሰቧ ስጦታን ይዞ ተነሣ፤ ጉዞውም በጣም ረጅምና አድካሚ ቢሆንም በመጨረሻ ግን ደረሰ፤ ከከተማው ውጭ በሚገኘው የውሀ ጉድጓድ አጠገብ ግመሎቹን አንበረከከ፤ ጊዜው ከሰዓት በኋላ ነበርና ሴቶችም ውሀ ለመቅዳት በዚያን ሰዓት ይመጣሉ፤ ለይስሐቅ ትክክለኛ ሚስት የምትሆነው የትኛዋ ትሆን?

አገልጋዩም ጌታው ሲያደርግ እንዳየው ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገረ፤ እንዲህም አለ "ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ ለጌታዬ ለአብርሃም የሰጠኸውን ተስፋ ጠብቅለት፤ ለይስሐቅም ሚስት ለመምረጥ የአንተ እርዳታ ያስፈልገኛል፤ ከልጃገረዶቹ ለአንዲቱ ከእንስራሽ ውሀ አጠጭኝ እላታለሁ፤ "እርሷም 'ለአንተና ለግመሎችህም ውሀ እሰጣለሁ' የምትለኝ ለይስሐቅ ትክክለኛዋ ሚስት ትሁን።"





እርሱም ፀሎቱን ገና ሳይጨርስ አንዲት ውብ ልጃገረድ እንስራዋን በጀርባዋ ተሸክማ ስትመጣ አየ፤ እርሷም እንስራዋን ከሞላች በኋላ እርሱ ውሀ አጠጭኝ አላት፤ እርሷም ፈጥና እንስራዋን ሰጠችውና የፈለገውን ያህል ጠጥቶ ከረካ በኋላ ለግመሎቹ ሁሉ ውሀ ሰጠቻቸው።

ይህም እርሱ አስቀድሞ የጠየቀው ምልክት ስለሆነ አንድ የወርቅ ቀለበትና ሁለት የወርቅ የእጅ አምባር አወጣና ለልጃገረዲቱ ሰጣት፤ ከዚያም ስሟን ጠየቃትና በዚያች ሌሊት እርሱና ከእርሱ ጋር ያሉት ሰዎች በአባቷ ቤት ማደር ይችሉ እንደሆነ ጠየቃት።

እርሷም እንዲህ አለች፣ "ስሜ ርብቃ ይባላል፤ አባቴ ባቱኤል ይባላል፤ አያቴም ናኮር ይባላል፤ "አገልጋዩም "እግዚአብሔር ወደ ጌታዬ ዘመዶች ልኮኛል" አለና እግዚአብሔርን ስላደረገለት እርዳታ አመሰገነ፤ ርብቃም ሰውዬውን በዚያው ትታ ያገኘችውን ስጦታ ለማሳየትና የሆነውን ሁሉ ለቤተሰቧ ልትነግር ሮጠች፤ ወንድሟ ላባም ይህን በሰማ ጊዜ እንግዳውን ለመቀበልና ሰላምታ ለመስጠት በፍጥነት ሄደ፤

ወዲያውም ለግመሎቹ መብል ተሰጠና ሰዎቹም ከታጠቡ በኋላ መልካም ትኩስ ምግብ ሊበሉ ተቀመጡ፣ ዳሩግን የአብርሃም አገልጋይ ለምን እንደመጣ ሳይናገር ተቀምጦ ሊበላ አልፈለገም፤ከዚያም እርሱ ስለአብርሃምና ስለይስሐቅ እንዲሁም እነርሱን እግዚአብሔር





እንዴት እንደባረካቸው ተናገረ። በውሃ ጉድጓዱም አጠገብ የፀለየውን ፀሎትና እግዚአብሔርም እንዴት እንደመለሰለት ነገራቸው፤ ከዚያም ርብቃ ከእርሱ ጋር እንድትሄድና ለይስሐቅ ሚስት እንድትሆነው ፈቃዳቸው መሆኑን ጠየቃቸው።

ባቱኤልና ላባ እንዴት እምቢ ሊሉ ይችላሉ? ነገሩ በግልጽ የእግዚአብሔር ዓላማ ነው፣ ስለዚህ የጋብቻ ስጦታው ከቀረበ በኋላ በአንድነትና በደስታ ምግብ በሉ፣ በነጋታው የአብርሃም አገልጋይ ወደ ቤቱ ለመመለስ ተነሣ፣ ርብቃም ምንም እንኳን ከማታውቃቸው ሰዎች ጋርና ወደማታውቀው አገርና ቤት ቢሆንም አብራ ለመሄድ ተስማማች።

አንድ ቀን ወደ ምሽት አካባቢ ይስሐቅ የሄዱትን ሰዎች ሲጠብቅ ሳለ ግመሎች ሲመጡ አየ፣ ሰዎቹም የሆነውን ታሪክ ለመንገር ጓጉተው ነበር፣ ይስሐቅ ግን በደምብ አላዳመጠም፣ ይመለከት የነበረው ለእርሱ ሙሽራ ልትሆን ከዚያ ሩቅ ቦታ የመጣችውን ውብ ልጃገረድ ብቻ ነበረ፣ መጠባበቁም አበቃና ይስሐቅ ርብቃን ሚስት እንድትሆነው ወሰዳት፣ ወደዳትም።



# ያያዕቆብ ታሪክ

ዘፍጥረት 27–28

ዓመታት አለፉ፣ ይስሐቅና ርብቃም ኤሳውና ያዕቆብ የተባሉ ሁለት መንታ ወንዶች ልጆች ወለዱ፣ ልጆቹ በተወለዱም ጊዜ እርስ በርሳቸው የሚዋጉ የሁለት ሕዝቦች አባቶች እንደሚሆኑ እግዚአብሔር ተናገረ፤ ታላቅዬው ኤሳው የታናሽ ወንድሙ የያዕቆብ አገልጋይ ይሆናል አለ፤

ኤሳውም ባደገ ጊዜ ጎበዝ አዳኝ ሆነ፣ ወደ ተራሮች መሄድን ይወድ ነበር፣ የዱር አውሬዎችን አድኖ ወደ ቤት እያመጣ አባቱ በጣም የሚወደውን ጣፋጭ ወጥ ይሠራ ነበር፣ ያዕቆብ ግን ከዚህ የተለየ ነበር፣ ዝምተኛ ሰው ነበር፣ ብዙውን ጊዜ እቤት ይውል ነበር፣ ስለዚህ ርብቃ ትወደው ነበር፣



## ውሽቱ

ይስሐቅ ባረጀ ጊዜ ዓይኖቹ ደክመው ነበር፤ በዚያን ዘመን አንድ አባት ለሞት ሲቃረብ ለበኵር ልጁ የእግዚአብሔርን በረከት የመጠየቅ ልማድ ነበር፤ ይስሐቅም ለኤሳው በረከቱን ለመስጠት ጊዜው እንደደረሰ አወቀ፤ አስቀድሞ ግን ኤሳው ከዱር አድኖ ሥጋ እንዲያመጣና ጥሩ ወጥ እንዲሠራለት ላከው፤ ርብቃም ይስሐቅ ለኤ ሳው የተናገረውን ከሰማች በኋላ በረከቱን ያዕቆብ መውሰድ እንዳለ በት በልቧ አሰበች፤ ይስሐቅ ዓይኑ ፈዞ ነበር፤ ያዕቆብም ኤሳው ነኝ ብሎ ቢቀርብ ይስሐቅ ፈጽሞ ሊያውቅ አይችልም፤



ስለዚህ ኤሳው ገና በአደን ላይ እያለ ርብቃ ከሁለት የፍየል ግልገሎች እጅግ የጣፈጠ ልዩ ወጥ ሠራች፤ ከዚያም የያዕቆብ ለስላሳ ሰውነት የኤሳውን ፀጉራማ ሰውነት እንዲመስል በያዕቆብ ክንዶችና አንገት ላይ የፍየሎቹን ቆዳ አለበሰችው፤ ያዕቆብም የወንድሙን ልብሶች ለበሰና ምግቡን ይዞ ወደ አባቱ ገባ፤ የምግቡ ጣፋጭ ሽታና የፍየሎቹ ቆዳ ስሜት ይስሐቅን አታለለው፤ ዳሩ ግን ድምፁ የሌላ ሰው እንደሆነ ጠርጥሮ ነበር፤

"በእውነት አንተ ኤሳው ነህን?" ብሎ ጠየቀው፤ ያዕቆብም "ነኝ" ሲል መለሰ። ስለዚህ ይስሐቅ ለበኵር ልጅ የሚገባውን ታላቅ በረከት እንዲሰጠው ወደ እግዚአብሔር ፀለየ። ኤሳው ግን ከዱር ሲመጣ እውነቱ ተገለጠ፤ ዳሩ ግን ምን ያደርጋል፣ ዘገየ፣ በረከቱ



ተሰጥቶአል፤ ኤሳውም በያዕቆብ እጅግ ስለተናደደ ርብቃ ይገድለዋል ብላ ፈራች፤ ስለዚህ ሚስት በማግባት ሰበብ ያዕቆብን ወደ ካራን እንዲልከው ይስሐቅን አግባባችው።

## ሕልሙ

ያዕቆብ ወደ ሰሜን በፍርሃት ብቻውን ተጓዘ፤ ፀሐይም ስትጠልቅ ወደ አንድ ባዶ ድንጋያማ ሸለቆ ደረሰ፤ በዚያም ድንጋይን ትራስ አድርጎ ለመተኛት ተጋደመ፤ ባንቀላፋም ጊዜ በሕልሙ አንድ ረጅም መሰላል ወደ ሰማይ ተዘርግቶ መላእክትም በላዩ ሲወጡና ሲወርዱበት አየ፤ በላዩም እግዚአብሔር ቆሞ ያዕቆብን ሲያነጋግረው ነበር፤ "የተኛህበትን ምድር ለአንተና ለዘርህ እሰጣለሁ" አለው፤ ደግሞም "እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፣ በሄድክበትም ሁሉ እጠብቅሃለሁ፣ ወደዚህችም ምድር እመልስሃለሁ" አለው። ያዕቆብም በነቃ ጊዜ ምንም እንኳ የሰማው የሚያጽናኑ ቃላት ቢሆኑም በጣም ፈርቶ ነበር። የሰማው የእግዚአብሔር ድምፅ እንደሆነ እርግጠኛ ነበር፤ ያዕቆብም ለእግዚአብሔር ስዕለት ተሳለ፤ እንዲህም አለ፦ "ከእኔ ጋር ከሆንክና ከጠበቅኸኝም፣ ወደዚህም ምድር በደህና ከመለስኸኝ አንተ አምላኬ ትሆናለህ።"



## ያዕቆብ እኩያውን አገኘ


በመጨረሻ ያዕቆብ ወደ እናቱ አገር ደረሰ፤ ስለ አጎቱ ስለ ላባ ለመጠየቅ አስቦ በአንድ የውሀ ጉድጓድ አጠገብ አረፈ፤በዚያም አንዲት ልጃገረድ መንጋዋን ውሀ ልታጠጣ መጣች። እርሷም የላባ ልጅ ራሄል የምትባለው ዘመዱ ነበረች፤ ማንነቱንም በነገራት ጊዜ ያዕቆብ ከደስታው ብዛት የተነሣ አለቀሰ፤

ላባም እንደ ቤተሰብ አድርጎ ተቀበለው፤ ያዕቆብም ለላባ ሲያገለግል አንድ ወር ሆነው፤ ከዚያም ላባ ያዕቆብን ደመወዙ ምን ያህል እንደሚሆን ጠየቀው፤ ያዕቆብም "ልጅህን ራሄልን እንዳገባት ከፈቀድህልኝ ለሰባት ዓመት አገለግልሃለሁ" አለው።

ላባም በዚህ ተስማማ፤ ያዕቆብም ራሄልን ከመውደዱ የተነሣ ሰባቱ ዓመታት እንደ ሰባት ቀናት ሆኑለት፤ ዳሩ ግን የሠርጉ ቀን ሲደርስ ላባ ያዕቆብን በማታለል ታላቅ እህቷን ልያን ሰጠው፤ ለዚህም ድርጊት በአገራቸው ባሕል ታላቂቱ ከታናሽቱ እህቷ በፊት ማግባት አለባት የሚል ምክንያት ሰጠ፤ በድጋሚም ያዕቆብ ራሄልን ቢያገባት ላባ ፈቃደኛ ሆነ፤ ዳሩ ግን በድጋሚ ሌላ ሰባት ዓመት ያለ ደመወዝ ለአጎቱ ማገልገል ነበረበት።

ስለዚህ ያዕቆብ ሁለት ሚስቶች ስለነበሩት በቤቱ ውስጥ ደስታ አልነበረም፤ ያዕቆብ ራሄልን ከልያ አብልጦ በመውደዱ ልያ ደስተኛ አልነበረችም። ልያ ግን ልጆች ነበሩአት፣ ራሄል ደግሞ ምንም ብትጓጓ ልጅ አልነበራትም። ከዓመታት በኋላ ልያ ስድስት ወንዶችና







አንድ ሴት ልጅ ነበራት፤ ከዚያም በኋላ በመጨረሻ ራሄል አንድ ወንድ ልጅ ወለደች፣ ስሙንም ዮሴፍ አለችው፤

## ወደ አገር ጉዞ

በዚህ ጊዜ ያዕቆብ ወደ ቤቱ ለመመለስ ይመኝ ነበር፤ ዳሩ ግን በያዕቆብ ምክንያት ባለፀጋ ስለሆነ አጎቱ ላባ ሊለቅቀው አልፈለገም።

"ከእኔ ጋር ቆይ የምትፈልገውንም ያህል እከፍልሃለሁ" አለው። ይህ ለያዕቆብ መልካም ዕድል ነበር፤ ያዕቆብም ተስማማ፤ ደመወዜ ጥቋቁሮቹ በጎችና ፍየሎች እንዲሁም ዝንጉርጉርና ነጠብጣብ ያለባቸው ይሁኑ አለ፤ ላባም ያዕቆብን ሊያታልለው ሞከረ፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ስለረዳው የእርሱ መንጋዎች እየበዙ ሄዱ፤ ያዕቆብ ባለፀጋ ሆነ፤ ዳሩ ግን የላባ ልጆች ይጠሉት ጀመር፤

ላባ ለመሄድ እንደማይፈቅድለት አወቀ፣ ስለሆነም አጎቱ በጎች ለመሸለት እስኪሄድ ድረስ ጠበቀ፤ ከዚያም የኤፍራጥስን ወንዝ አቋርጦ ከሚስቶቹና ከልጆቹ፣ ከአገልጋዮቹና ከመንጋዎቹ ጋር ኮበለለ፤ ላባም ተከተለው፣ ይሁን እንጂ እንዲመለስ ሊያግባባው አልቻለም፤

ያዕቆብ ወደ ቤቱ ወደ ከነዓን ጉዞውን ቀጠለ፤ እየተቃረቡ ሲሄዱ በይበልጥ ፍርሃት ፍርሃት አለው፤ ኤሳው አሁንም በእርሱ ላይ እንደተቆጣ ይሆንን? ከኤሳው ጋር እርቅ ለማድረግ በፊቱ መልክተኞችን ላከ፤ ዳሩ ግን መልእክተኞቹ ኤሳው ከ400 ሰዎች ጋር ወደ እርሱ እየመጣ መሆኑን ነገሩት፤ ያዕቆብም የእግዚአብሔርን እርዳታ ለመነ፤ እንዲህ ሲልም ፀለየ "እግዚአብሔር ሆይ ተመለስ ያልከኝ አንተ ነህ፤ የአንተ ምህረት ፈጽሞ የሚገባኝ ሰው አይደለሁም፤ ከኤሳው ቁጣ አሁን አድነኝ፤" ለኤሳውም ስጦታ ለማቅረብ ብዙ

በጎችንና ፍየሎችን፣ ግመሎችን፣ ከብቶችንና አህዮችን መረጠ፤ ከእነዚህም ጋር አገልጋዮቹን ወደ ፊት ላከ፤ ከዚያም በኋላ እርሱ ሚስቶቹና ልጆቹ የያቦቅን ወንዝ ሸለቆ ተሻገሩ::

በዚያ ሌሊት ያዕቆብ ብቻውን በፍርሃት ሳለ አንድ እንግዳ ነገር ሆነ፤ አንድ ሰው መጥቶ ሌሊቱን ሙሉ እስኪነጋ ድረስ ይታገለው ነበር፤ ያዕቆብ ማን እንደሆነ አላወቀውም፣ ዳሩ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣ አወቀ፤ ያዕቆብም የእግዚአብሔርን በረከት ካላገኘ በስተቀር ሊለቅቀው አልፈለገም፤

ከዚያች ሌሊት በኋላ ያዕቆብ ያነክስ ነበር፤ ዳሩ ግን የእርሱ ስም ያ በፊት ወንድሙን ያታለለው ያዕቆብ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት ስለተገናኘ እስራኤል ተብሎ ተጠራ፤

ፀሐይም በወጣች ጊዜ ያዕቆብ ኤሳውና ተከታዮቹ ወደ እርሱ ሲመጡ አየ፤ እርሱ ችግር ይገጥመኛል ብሎ ፈርቶ ነበር፤ ዳሩ ግን ኤሳው ሊገናኘው ሮጠና አቀፈው፤ የቀድሞው ጥላቻ በአሁኑ የግንኙነት ደስታ ተረሣ፤ ቤተሰቦቹም ሲሰበሰቡ ኤሳው "እነዚህ እነማን ናቸው?" ብሎ ጠየቀ፤ ደግሞም "በመንገድ ያገኘኋቸው መንጋዎች ምንድናቸው? " አለ፤

ያዕቆብም ሲመልስ" መንጋዎቹ ለአንተ ስጦታ ናቸው፤ እባክህን ተቀበል፤ ምክንያቱም የአንተን የፍቅር አቀባበል በፊትህ ላይ ስመለከት የእግዚአብሔርን ፊት እንዳየሁ ቆጥሬዋለሁና ነው" አለው::






# ዮ ሴ ፍ ና ወ ን ድ ሞ ቹ

ዘፍጥረት 37–50

ያዕቆብ አሥራ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት፤ እነርሱም ሮቤል፣ ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ይሳኮር፣ ዛብሎን /የልያ ልጆች/፤ ጋድና አሴር /የልያ አገልጋይ የዘለፋ ልጆች/፣ ዳንና ንፍታሌም /የራሄል አገልጋይ የባላ ልጆች/ ደግሞም ዮሴፍና ብንያም /የራሄል ልጆች/ ናቸው::

ያዕቆብ ዮሴፍን ከሌሎች አብልጦ ይወደው ነበር፤ ይህ ችግር እንደሚያስከትል ማወቅ ነበረበት፤ ራሄል ብንያም እንደተወለደ ሞተች:: ያዕቆብም ራሄልን በጣም ይወድ ነበር:: በዚህ ምክንያት የእርሷን ልጆች ከሌሎች አብልጦ መውደድ ግድ ሆነበት፤ ከዚህም በላይ አድልዎ ያደርግ ነበር:: ዮሴፍን በጣም አሞላቀቀው፤ ልዩ የሆነ ኮትም ሰጠው፤ ይህ ግን ለበኵር ልጁ ለሮቤል የሚገባ ነበር::

ይህ አድራጎቱ በወንድሞቹ ዘንድ ቅንዓትን ስላሳደረ ዮሴፍን በጣም ጠሉት፤ ከዚህ የባሰ ችግር መጣ፣ ምክን ያቱም ዮሴፍ በሕልሙ ወንድሞቹ ሁሉና አባቱም ለእርሱ ሲሰግዱለት አየ፤ ዮሴፍ ስለ ሕልሙ ራሱን ከፍ በማድረግ በተናገረ ጊዜ አባቱ እንኳን ተቀየመው::



ከዕለታት አንድ ቀን ወንድሞቹና መንጋዎቹ ደህና መሆናቸውን እንዲጠይቅ ያዕቆብ ዮሴፍን ወደ መስክ ላከው:: እነርሱ ዮሴፍ ወደ እነርሱ ሲመጣ ባዩ ጊዜ ሊገድሉት ተማከሩ፤ ሮቤል ግን ሊያድነው ስለፈለገ በዚያን ጊዜና በዚያ ቦታ እንዳይገድሉት ተከላከለ::

## ባሪያ ሆኖ ተሸጠ

በዚህ ደረቅ ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት አላቸው እነርሱም ተስማሙ፤ ሮቤል ግን በጎች ሊጠብቅ ከዚያ በሄደ ጊዜ ጥቂት ነጋዴዎች በዚያ ሥፍራ ወደ ግብጽ አገር ያልፉ ነበር፤ በዚህ ጊዜ ሌሎቹ ወንድሞች ዮሴፍን በሃያ ብር ሸጡት፤ ሮቤልም ሲመለስ ሊያገኘው አልቻለም፤ ወንድሞቹም የዮሴፍን ኮት ወሰዱና በደም ለወሱት፤ ይህንንም ወደ ቤት ወስደው ለአባታቸው አሳዩት፤ ያዕቆብም ጨካኝ አውሬ በጫጭቆታል ብሎ በማሰብ መራራ ለቅሶ አለቀሰለት፤ ሊጽናናም አልቻለም።



በዚህ መካከል ዮሴፍ ጶጢፋር ለሚባል ለአንድ የግብፅ ንጉሥ ሚኒስቴር በባርነት ተሸጠ ነበር። ዮሴፍ በሰው አገር ባሪያ ቢሆንም ብቻውን አልነበረም። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበር። ጶጢፋርም በዚህ አዲስ አገልጋይ በጣም ከመደሰቱ የተነሣ በመላው ቤተሰቡና በሥራው ሁሉ ላይ አለቃ አድርጎ ሾመው።

ዮሴፍም መልከ መልካም ስለነበረ የጶጢፋር ሚስት በፍቅር ተያዘች፤ እርሱ ግን ለጌታው ታማኝ በመሆኑ ከእርሷ ጋር በፍቅር ሊተኛ አልፈለገም፤ ከዚህ በኋላ የጶጢፋር ሚስት በጣም ተናደደችና በዮሴፍ ላይ ለባሏ በውሸት ዮሴፍ አነቀኝ ብላ ተናገረች፤



## በንጉሡ ወህኒ ቤት

ጶጢፋርም በጣም ተቆጣ፤ ዮሴፍንም በንጉሡ ወህኒ ቤት ወረወረው፤ ጻሩ ግን አሁንም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረ፤ የወህኒ ቤቱ ኃላፊ በጣም ታማኝ አድርጎ ስለቆጠረው በሌሎቹ እስረኞች ላይ አለቃ አደረገው፤ ከእስረኞቹ አንዱ የንጉሡ ጠጅ አሳላፊ ሲሆን ሌላው ደግሞ የንጉሡ የእንጀራ ቤት አላፊ ነበር።

አንድ ሌሊት እነዚህ ሁለት ሰዎች ሕልምን አለሙ፤ በነጋታው ዮሴፍ ምግባቸውን ሲያቀርብላቸው በጣም አዝነው አገኛቸው፤ እነዚህ ሕልሞች ምን ይሆኑ? በግብፅ አገር በዚያን ዘመን ሕልም እንደ ቀላል ነገር አይታይም ነበር፤ ማንኛውም ሕልም ትርጉም ነበረው፤ ዮሴፍም "የሕልምን ትርጉም የሚገልጽ እግዚአብሔር ብቻ ነው" አለ። ከዚያም ጠጅ አሳላፊውና የእንጀራ ቤት አላፊው ሕልማቸውን ለዮሴፍ ሲነግሩት እግዚአብሔር ለዮሴፍ ትርጉሙን ገለጸለት።

ጠጅ አሳላፊው ያየው ሕልም፣ ሦስት ቅርንጫፎች ያሉት የወይን ዛፍ ነበር፤ ደግሞም የወይን ፍሬ ለቅሞ በንጉሡ ዋንጫ ውስጥ ከጨመቀ በኋላ ለንጉሡ ሲሰጥ አየ፤ ዮሴፍም "በሦስት ቀን ውስጥ ንጉሡ ነፃ ይለቅህና ወደ ቀድሞ ሥራህ ይመልስሃል፤ በዚያን ጊዜ እባክህ ስለ እኔ ለንጉሡ ነግረህ ከዚህ እሥራት እንድታስወጣኝ" አለው። ጠጅ አሳላፊው ተስፋ ሰጠው፤



የእንጀራ ቤት አሳፊውም በሕልሙ ሦስት የዳቦ ቅር ጫቶችን በራሱ ላይ ተሸክሞ ለንጉሡ የሚሆን ብስኩት ሞልቶበት አየ፤ ዳሩ ግን ወፎች ይበሉት ነበር።


ዮሴፍም እንዲህ አለው "በሦስት ቀን ውስጥ ንጉሡ በነፃ ከወህኒ ይለቅሃል፤ ዳሩ ግን አንገትህን ይቆርጠዋል።" ሁሉም ነገር ዮሴፍ እንደተናገረው ሆነ፤ ጠጅ አሳላፊው ግን ለዮሴፍ የገባውን ቃል ረሳው።

## የንጉሡ ሕልም

ከሁለት ዓመታት በኋላ ንጉሡ አንድ አስገራሚ ሕልም አየ። ዳሩ ግን ማንም ሊተረጉመው አልቻለም፤ በዚህ ጊዜ የጠጅ አሳላፊው ዮሴፍን አስታወሰና ዮሴፍ ከወህኒ ቤት ተጠርቶ መጣ፤ ንጉሡም ሕልሙን ነገረው።

በሕልሙም ንጉሡ በዓባይ ወንዝ አጠገብ ቆሞ ሳለ ሰባት ወፋፍራም ላሞች ከወንዙ ሲወጡ አየ፤ ከዚያም በኋላ የከሱ ላሞች ወጡና እነዚህ የከሱ ላሞች ወፍራ ሞቹን ላሞች ዋጡአቸው! እግዚአብሔርም የሕልሙን ትርጉም ለዮሴፍ አሳየው፤





ዮሴፍም ለንጉሡ አለ "ሰባት የጥጋብ ዓመታት ይመጣሉ፣ ከዚያም በኋላ ሰባት የረሃብ ዓመታት ይሆ ናሉ አንተም ብልህ ከሆንክ በክፉዎቹ ዓመታት ሕዝብህ እንዳይራብ ከፈለግህ በመልካሞቹ ዓመታት እህልን ታከማቻለህ።"

ንጉሡም የሕልሙን ፍቺ ስላገኘ በጣም ደስ አለው፤ ዮሴፍ በእርግጥ የእግዚአብሔር ሰው መሆኑ ታወቀ፤ ለሚሰበሰበውም እህል ከእርሱ የተሻለ ሰው አይገኝም፤ ስለዚህ ንጉሡ የራሱን የወርቅ ቀለበት

በዮሴፍ ጣት ላይ፣ የወርቅ ሰንሰለትም በእርሱ አንገት ላይ አጥልቆለት በመላው የግብፅ ምድር ከንጉሡ በታች ሁለተኛ አዛዥ አደረገው። 

ከሰባት ዓመታት በኋላ ዮሴፍ እንዳለው እህል ሊበቅል ስላልቻለ በብዙ አገሮች ምንም የሚበላ ነገር ጠፋ። ዳሩ ግን በግብፅ ዮሴፍ ጎተራውን ከፍቶ ለሕዝቡ እህል ይሸጥ ነበር።

በከነአንም የዮሴፍ አባትና ወንድሞቹ የሚበሉት እህል አልነበራቸውም፤ በመጨረሻ ያዕቆብ ከብንያም በቀር ልጆ ቹን ሁሉ ወደ ግብፅ ለመላክ ወሰነ፤ አሥሩም የያዕቆብ ልጆች በግብፅ አገር በገዥው ፊት ቆመው እህል ለመግ ዛት ፈቃድ ሲጠይቁ ከብዙ ዓመት በፊት የጠፋው ወንድ ማቸው መሆኑን ማንኛቸውም ሊያውቁ አልቻሉም። ዮሴፍ ግን ማን እንደሆኑ በአንድ ጊዜ አወቀ፤ አሁንም እንደ ቀድሞው ጨካኝ መሆናቸውን ለማወቅ ፈለገና በቁጣ ተመለከታቸው። "ሰላዮች ናችሁ" አለና በወህኒ ቤት አስገባቸው፤ ከሦስት ቀን በኋላ ለቀቃቸው፤ ደግሞ በሚቀጥለው ጊዜ ብንያምን ይዘው ለመምጣት ቃል እንዲገቡ አደረጋቸው፤ እንደ ቃላቸውም ያደርጉ እንደሆነ ለማወቅ ስምዖንን በመያዣ ስም አስቀረው፤ ወንድሞቹም ለእህሉ የከፈሉትን ገንዘብ በከረጢታቸው ውስጥ እንዲመልሱላቸው ዮሴፍ አሽከሮቹን አዘዘ።

ወንድሞቹም ከረጢታቸውን ሲከፍቱ ገንዘቡን ባገኙት ጊዜ በጣም ፈሩ፤ እያዘኑም እህሉን ይዘው ወደ ከነአን ተጓዙ፤ በሚቀጥለው ጊዜ ብንያምን ይዘው መሄድ ይኖርባቸዋል፤ ዳሩ ግን ከትንሹ ልጅ እንዲለይ ያዕቆብን እንዴት ሊያግባቡት ይችላሉ? ምግቡ ባለቀ ጊዜ ግን ሌላ አማራጭ ጠፋ፤ ብንያም ከእነርሱ ጋር ካልሄደ በረሃብ ማለቃቸው ነው።

እንደገናም በግብፅ ገዥ ፊት ሲቆሙ ዮሴፍ ብንያምን ባየው ጊዜ እንባውን መቆጣጠር አልቻለም፤ ወንድሞቹም በዮሴፍ ፊት ተንበረከኩ፤ ዮሴፍም "ሽማግሌው አባታችሁ እንዴት ነው? ይህስ ትንሹ ወንድማችሁ ነውን?" አለ። የዮሴፍ አገልጋዮች ምግብ ከአዘጋጁ በኋላ የዮሴፍ ወንድሞች ለመብላት ተቀመጡ፤ ምግቡም በቀረበ ጊዜ ብንያም ከሌሎቹ አምስት እጅ የሚበልጥ ቀረበለት፤ ዳሩ ግን አሁንም ገና ዮሴፍ ማንነቱን አልነገራቸውም።



በነጋታው በከረጢቶቻቸው እህል ሲሞሉ ዮሴፍ የራሱን የብር ዋንጫ በብንያም ከረጢት ውስጥ እንዲያስቀምጡት አሽከሮቹን አዘዛቸው::

ወንድሞቹ ግን ገና ብዙ ሳይርቁ የዮሴፍ አሽከሮች ደረሱባቸው፡ የዮሴፍን ዋንጫ የወሰደውን "ሌባ" እየፈለጉ ነበር፡ የብንያም ከረጢት በተከፈተ ጊዜ የጠፋው ዋንጫ ሲወጣ ወንድሞቹ በፍርሃት ተንቀጠቀጡ፡ ወደ ከተማውም ተመለሱና ሁሉም በዮሴፍ እግር ሥር ወደቁ፡







ዮሴፍም ሲፈትናቸው "ዋንጫው የተገኘበት ሰው ለእኔ ባሪያ ይሆናል፤ ሌሎቻችሁ መሄድ ትችላላችሁ" አላቸው:: ወንድሞቹ ግን ሊሰሙት አልቻሉም:: ይህኛው ልጅ ደግሞ ከእርሱ መለየቱን ለአባታቸው ለመንገር እንደማይቻላቸው አወቁ::

ይሁዳ እንዲህ አለ "ብንያም ከእኛ ጋር ካልሄደ አባታችን በሀዘን ይሞታል፤ እኔም በደህና እንድመልሰው ቃል ገብቻለሁ፤ እኔ በእርሱ ፋንታ ባሪያ እሆናለሁ፤" ዮሴፍ ይህን በሰማ ጊዜ ወንድሞቹ አስቀድሞ በእርሱ ላይ ባደረጉት ነገር በእውነት እንደተጸጸቱ አወቀ፤ አሽከሮቹ ንም ከክፍሉ እንዲወጡ ካደረገ በኋላ እንባውን አፈሰሰ፤

እርሱም "እኔ ዮሴፍ ነኝ፤ አባቴ ገና በሕይወት አለን?" አለ፤ ሁሉም በፊታቸው ላይ ሀፍረት ይታይ ነበር። በእርግጥ አሁን ዮሴፍ ብድሩን ሊመልስ ይችል ነበር፤ ምን ያድርጋቸው?

ዳሩ ግን ዮሴፍ እንዲህ አላቸው "አትፍሩ፤ የሁላችንንም ሕይወት ለማዳን እኔን ወደዚህ የላከኝ እግዚአብሔር ነው፤ በተጨማሪ ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የእህል ምርት አይኖርም፤ ብዙዎችም በረሃብ ይሞታሉ፤ ወደቤታችሁ ተመልሳችሁ የቀሩትን ቤተሰባችሁን አምጡና ከእኔ ጋር በጌሴም ምድር ትቀመጣላችሁ፤"

ደግሞም ሁሉንም አቀፋቸውና እንባው በፊቱ ላይ ይወርድ ነበር፤ ስለዚህ ያዕቆብና የዮሴፍ ወንድሞች ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው አሽከሮቻቸው፣ ከብቶቻቸውና መንጋዎቻቸው ሁሉ ከነአንን ትተው ወደ ግብፅ ሄዱ። ዮሴፍም ያዕቆብ ከንጉሡ ጋር እንዲገናኝ ወደ ቤተ መንግሥት ወሰደው፤ ከዚያም በኋላ ሁሉም መልካም በሆነችው በጌሴም ምድር ተቀመጡ።





# ሙሴ የእግዚአብሔርን ጥሪ ሰማ

ዘፀአት 1–4



ከብዙ ዘመን በኋላ የያዕቆብ ዘር የሆኑት እስራኤላውያን ብርቱና ኃይለኛ ሕዝብ ሊሆኑ ቻሉ፤ ግብፃውያንም ይፈሩአቸው ጀመር። አዲስ ንጉሥም ነግሦ ስለነበር በአስቸኳይ አንድ እርምጃ ለመውሰድ ወሰነ፤

እስራኤላውያንን ባሪያ አደረጋቸው፤ ጨካኝ የሆኑ አሠሪዎች የንጉሡን ከተሞች ለመገንባት የሚውሉ ጡቦችን እንዲሠሩ አስገደዱአቸው፤ በኃይልና በጭቆና ከማለዳው እስከ ምሽት ድረስ ይሠሩ ነበር፤ ቢሆንም ግን ቁጥራቸው እየበዛ ሄደ፤

ስለዚህ ንጉሡ ማንኛውም እስራኤላዊ ወንድ ሕፃን ሲወለድ ወደ ዓባይ ወንዝ እንዲጣል ትእዛዝ ሰጠ፤

በዚህን ጊዜ ዮካብድ የምትባል እስራኤላዊት ሴት አንድ ልጅ ወለደች፤ ከዚህ በፊትም አሮን የሚባል ወንድ ልጅና ማርያም የምትባል ሴት ልጅ ነበሩአት፤ የአሁኑ ልጅ ደግሞ ወንድ መሆኑን ባየች ጊዜ በጣም ፈራች፤ ለሦስት ወራትም በቤት ውስጥ ደበቀችው፤ ዳሩ ግን ሕፃናት

ፀጥ ብለው ብዙ ለመቆየት አይችሉም፤ ምን ማድረግ ነበ
ረባት? አንድ አሳብ መጣላት፤ ከሸምበቆ አንድ ቅርጫት
ሠራችና ውሀ እንዳያስገባ በሬንጅ ለቀለቀችው፤ ሕፃኑንም
በውስጡ አስቀመጠችው፤ ከዚያም ቅርጫቱን ወስዳ
በወንዙ ዳርቻ ባለው በሸምበቆው ውስጥ አኖረችው፤
ማርያምንም እንድትጠብቀው ነገረቻት፤



ወዲያውም ዮካብድ እንደገመተችው የንጉሡ ልጅ
ገላዋን ልትታጠብ ወደ ወንዙ መጣች፤ ቅርጫቱንም ባየች
ጊዜ አገልጋይዋን ልካ አስመጣችው፤ ክዳኑንም ሲከፍቱት
በሕይወቷ ካየቻቸው ሁሉ የበለጠ ውብ ሕፃን በውስጡ
ነበረ፡፡ እርሱም ይጮህ ነበር፤ ልዕልቲቱም እርሱ እስራ
ኤላዊ ሕፃን እንደሆነ አወቀች፡፡ ዳሩ ግን ልጅ ስላልነበ
ራት እንደ ልጇ አድርጋ ልታሳድገው ወሰነች፤ ስሙንም
ሙሴ አለችው፤



ልዕልቲቱም ዘወር ስትል በአጠገብዋ ማርያምን
አየች፤ እርሷም ሕፃኑን የምታሳድግ ሞግዚት ላምጣልሽ
አለቻት፤ ያለጥርጥር ማርያም ያመጣቻት ሞግዚት የልጁ
እናት ነበረች፤

ስለዚህ ሙሴ ከግብፃውያን የሚገኘውን ትምህርት
ሁሉ እየተማረ በንጉሡ ቤተ መንግሥት አደገ፤ ዳሩ ግን
እስራኤላዊ መሆኑን ፈጽሞ አልረሳም፤ ስለዚህ ግብፃውያን
አሠሪዎች በወገኖቹ ላይ የሚያደርጉትን ጭካኔ ማየት
እጅግ አሳዘነው፤

ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ግብፃዊ እስራኤላዊውን
በጅራፍ ሲገርፈው አየ፤ ሙሴም በሰውዬው ላይ ተነሳበ
ትና ገደለው፤ አሁን ያደረገውን ነገር ንጉሡ ስለሚሰማ
ሕይወቱ በአደጋ ላይ መሆኑን አወቀ፤ ስለዚህ ሙሴ
ለመዳን ግብፅን ትቶ ወደ በረሃ ሸሸ፡፡

በዚያም በምድያም ምድር በእረኝነት ሥራ ለብዙ
ጊዜ ተቀመጠ፤ በግብፅ አገር ደግሞ የእስራኤላውያን
ችግር እየተባባሰ ሄደ፤

ከዕለታት አንድ ቀን የአማቱን በጎች ሲጠብቅ ያልተ
ለመደ ትርኢት ተመለከተ፤ በመቃጠል ላይ የሚመስል
አንድ ቁጥቋጦ ነበር፤ ግን እሳቱ አይበላውም ነበር፤
ሙሴም በቅርብ ሊመለከት ሄደ፤ "አትጠጋ፣ የቆምህበትም
ቦታ ቅዱስ ስለሆነ ጫማህን አውልቅ" የሚል ድምፅ ሰማ፤
ሙሴም በጣም ፈራ፤ ድምፁም እንደገና መጣ፤ "እኔ አባ
ቶችህ የሚያውቁኝና የሚያመልኩኝ አምላክ ነኝ፤ የሕዝቤን
የእስራኤልን ክፉ ስቃይ አይቻለሁ፤ አንተም ወደ ግብፅ
ንጉሥ ሄደህ ሕዝቤን ነፃ ታወጣለህ፤ ወደ እኔም ታመጣቸ
ዋለህ፤" ሙሴም መልሶ "እኔ የምላቸው ምንድን ነው?
የማደርገውስ ምንድን ነው? እነርሱም አይሰሙኝም፤ እባክ
ህን ሌላ ሰው ላክ" አለው፡፡ እግዚአብሔርም፣ "የለም፣
እኔ መርጬሃለሁ፤ በአንተ ፈንታ እንዲናገር ወንድምህን
አሮንን ውሰድ፤ እኔም ተአምራትን እንድታደርግ ቃልንና
ኃይልን እሰጥሃለሁ፤ እኔ ሕያው አምላክ ነኝና" አለው፡፡



# ፈርኦን እምቢ አለ

ዘጸአት 5–14

ሙሴና አሮን በግብፅ ንጉሥ በፈርኦን ፊት ቆሙ፤ እንዲህም አሉ፦"የምናቀርበው ጥያቄ አለን፤ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር በምድረ በዳ በዓል ያደርግ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ" ይላል

ንጉሡም መልሶ "የእናንተን አምላክ አላውቅም፣ እርሱ ለኔ ምንድነው? እስራኤላውያንንም አልለቅም" አለ፤ ንጉሡም ተቆጣ:: እንዲህም አለ፦ "ከአሁን ጀምሮ ጡብ ለመሥራት ጭቃ የሚያቦኩበትን ጭድ ማንም እንዳይሰጣቸው፣ ራሳቸው ሄደው ይፈልጉ፤ ደግሞም በፊት ይሠሩት ከነበረው የጡብ ቁጥር ምንም እንዳይጎድል፤"

ይህ በጣም አስፈሪ ነገር ነው፤ ሙሴም ተስፋ ቆርጦ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ::

እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፣ "በግብፅ ንጉሥ የማደርገውን አሳይሃለሁ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ፈርኦንም ሕዝቤን እንዲለቅ አደርገዋለሁ:: እኔ ነፃ አወጣቸዋለሁ፤ አንተም ከግብፅ አገር ታወጣቸዋለህ፤ ወደ ንጉሡ እንደገና ሂድ፤ የተናገርሁትንም ለመፈጸም እምቢ ካለ በግብፅ ላይ አስከፊ ችግር እንደማመጣበት ንገረው፤ በዚህም ግብፃውያን ሁሉ እኔ እውነተኛ አምላክ እንደሆንኩ ያውቃሉ::"






ሙሴና አሮንም እንደገና በንጉሡ ፊት ቆሙ፤ ንጉሡም "በእውነት እናንተ ከእግዚአብሔር ከሆናችሁ ተአምራትን አሳዩኝ" አላቸው::

ስለዚህ አሮን የያዛትን ጠንካራ በትር ወደ ምድር ሲጥላት እባብ ሆነች፤ ዳሩ ግን የግብፅ አስማተኞችም ተመሳሳይ ነገር ስላደረጉ ንጉሡ ሙሴንና አሮንን አባረራቸው፤

ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት እርምጃን ወሰደ፤ አስከፊ ነገሮች መፈጸም ጀመሩ፤ በየጊዜው ግን እግዚአብሔር አስቀድሞ ንጉሡን አስጠነቀቀ፤ ንጉሡ ግን አላመነም፤ ሊሰማም አልፈለገም፤



በመጀመሪያ የዓባይ ወንዝ ውሀ ደም መሰለ፤ ሽታውም ከረፋና ዓሣዎቹ ሁሉ ሞቱ፤ ከአንድ ሳምንት በኋላ አገሩ በሙሉ እንቁራሪት ብቻ ሆነ፤ ንጉሡም ሙሴ እንዲያስወግድለት ለመነ፤ ዳሩ ግን አሁንም ሕዝቡን አልለቀቀም::

ቀጥሎም በረሮና ዝምብ ይርመሰመስ ጀመር:: እነርሱም እስራኤላውያን ከሚኖሩበት ከጌሴም ምድር በስተቀር በሁሉ ቦታ ነበሩ፤ ፈርኦንም "መሄድ ትችላላችሁ" ካለ በኋላ እንደገና ሀሳቡን ለወጠ፤ ከዚያ በኋላ ከጌሴም በስተቀር በየቦታው ከብቶች ይሞቱ ጀመር፤ አሁንም ንጉሡ እምቢ አለ፤ እንደገና አስማተኞቹ እንኳን ሳይቀሩ ሁሉም በሚያሰቃይ ቁስል ተመቱ፤ አሁንም ንጉሡ እምቢ አለ፤ ሙሴና አሮን እንደገና በፊቱ ቆሙ፤ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ኃይሌን አይተሃል፤ እስራኤላውያንን ካልለቀቅህ ገና ወደፊት የሚመጣ ችግር አለ፤ ነገ በረዶ ይሆናል!'" አሉት::





እንደዚያ ያለ በረዶ ታይቶ አይታወቅም፣ ሰብሉን ሁሉ ደመሰሰና ከብቶቹንም በሜዳ ላይ ገደላቸው፣ በረዶውም ከጌሴም በስተቀር በሁሉ ቦታ ወረደ፣ ቀጥሎም ያገኘውን ሁሉ የሚበላ የአንበጣ መንጋ መጣ፤ ከዚያም በኋላ ድቅ ድቅ ጨለማ ለሦስት ቀናት ሆነ፣ ዳሩ ግን ንጉሡ አሁንም ገና ከእግዚአብሔር ጋር ይከራከር ነበር፤ ሕዝቡን ለመልቀቅ አልፈለገም፣ ከዚህ በኋላ ከሁሉም የበለጠው አስከፊ ነገር ሆነ፤ በአንድ ሌሊት ከንጉሡ ልጅና አልጋ ወራሽ ጀምሮ እስከ ተራው የባሪያ ልጅ ድረስ የእያንዳንዱ ቤተሰብ የበኵር ልጅ ሞተ፤ በጌሴም ምድር ግን እስራኤላውያን ደህና ነበሩ፤ እግዚአብሔር የሚያደርጉትን ነግሮአቸው ነበር፤

በዚያች ሌሊት እያንዳንዱ እስራኤላዊ ቤተሰብ ጠቦትን አርዶ በቤታቸው የበር ማዕዘን ላይ ደሙን ቀብቶ ነበር፤ ጠቦቱንም ጠብሰው ከቅጠላቅጠልና በአስቸኳይ ያለ እርሾ ከተጋገረ አፍለኛ ቂጣ ጋር በሉት፤ ሞትም የእነርሱን ቤት "አለፈው::"/ የአስራኤል ልጆችም ለዘላለም በያመቱ ይህንን የፋሲካ ልዩ ምግብ የሚበሉብትና እግዚአብሔር እንዴት እንደአዳናቸው የሚያስታውሱት በዚህ ምክንያት ነው::/



በሚቀጥለው ቀን ግብፃውያን እስራኤላውያንን ከመካከላቸው ለማስወገድ ብዙ መቆየት አልፈለጉም፣ እንዲያውም የወርቅና የብር ጌጣጌጥ እንዲሁም ጥሩ ጥሩ ልብሶች ይዘው እንዲሄዱ ሰጡአቸው፤ ቢሆንም ንጉሡ አሁንም ሊከለክላቸው ሞከረ፤ እነርሱ ጉዞ እንደ ጀመሩ የጦር ሠራዊቱን ጠራ፤ ወታደሮቹም በፈጣን ሰረገሎቻቸው ላይ ተቀመጡና እስራኤላውያንን ማባረር ጀመሩ፡

እስራኤላውያኑ በሀይቆቹና በረግረጋማው ጠረፍ አካባቢ ሲደርሱ ግብፃውያኑ ከኋላቸው ደረሱባቸው፤ ከፊት ለፊታቸው ውሀ ነበር፤ ከኋላቸውም ወታደሮች ነበሩ፡ ሕዝቡም እጅግ ፈሩ፡

ዳሩ ግን ሙሴ እጁን ሲዘረጋ እግዚአብሔር የምሥራቅን ነፋስ አመጣ፤ ሌሊቱን በሙሉ በነፈሰ ጊዜ እስራኤላውያኑ በደህና ይሻገሩ ዘንድ በውሀው መካከል ደረቅ መንገድን አበጀ::

ዳሩ ግን ግብፃውያኑ ሊከተሉአቸው ሲሞክሩ ውሀው እንደገና ስለተመለሰ የንጉሡ የጦር ሠራዊት በሙሉ በባህር ሰጠመ፤ በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር ሕዝቡን በማዳን ከግብፅ ምድር አውጥቶ ወደ ነፃነት መራቸው::

# መና በበረሃ

**ዘፀአት** 16 – 17፤ **ዘኍልቁ** 11 እና 20

የእስራኤል ሕዝቦች ከግብፅ ምድር አመለጡ፤ አሁን ባሪያዎች አይደሉም፣ ነፃ ሆነዋል፤ የሙሴና የአሮን እህት ማርያም ከበሮ ወሰደችና በደስታ የሚጨፍሩትንና የሚዘፍኑትን ሴቶች ትመራ ጀመር፤

"ለእግዚአብሔር ዘምሩ ታላቅ ድል አድርጎአልና፡ ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጥሎአልና" አሉ።



ዳሩ ግን ብዙ ሳይቆይ በግብፅ አገር የነበሩበትን ክፉ ባርነት ረሱ፤ የእነዚያን ክፉ አሠሪዎች ጅራፋቸውን ረሱ፤ የሚያስቡት በግብፅ ይበሉት የነበረውን ምግብ ብቻ ሆነ፤ ዓሣውን፣ የፍራፍሬ ጭማቂውን፣ ነጭ ሽንኩርቱን፣ ቀይ ሽንኩርቱንና ዱባውን! በዚያ በበረሃ ምን ይገኛል? ስለዚህ ማጉረምረም ጀመሩ፤ በሙሴና በአሮንም ላይ ተነሱባቸው። እንዲህም አሉ፣ "በዚህ በምድረ በዳ በረሃብ ከምንሞት በግብፅ አገር ሆነን ብንሞት ይሻል ነበር።"

እግዚአብሔርም ማጉረምረማቸውን ሰማና ለሙሴ ተናገረው፤



"የፈለጉትን እንደምሰጣቸው ለሕዝቡ ንገራቸው፡ ኣይወታቸውን አድኜአለሁ፤ ምግብ እሰጣቸዋለሁ፡ ዛሬ ማታ ሥጋ ያገኛሉ። ከነገ ጀምሮም በየማለዳው ልዩ ዓይነት እንጀራ ያገኛሉ፤ ዓርብ ግን የተለየ ይሆናል። ይኸውም በእረፍቴ ሰንበት ቀን ማንም እንዳይሠራ ዓርብ ቀን ለሁለት ቀናት የሚበቃ እሰጣችኋለሁ።" ሙሴም



እግዚአብሔር ያለውን ለሕዝቡ ከነገራቸው በኋላ በእርግጥም በዚያች ምሽት በፀሐይ መጥለቂያ ጊዜ ድርጭት የሚባሉ ብዙ የወፎች መንጋ በድንኳናቸው ዙሪያ አረፉ፤ ስለዚህ ሰዎቹ ሥጋ አገኙ።

በነጋታውም ጤዛው በፀሐይ ሲደርቅ እግዚአብሔር የሰጣቸው ልዩ እንጀራ በሰፈሩ ዙሪያ በምድሩ ላይ ነበረ፤ በዚያ እንደ አመዳይ ነበረና ሰዎቹ ፀሐይ ሳያቀልጠው ቶሎ ሰበሰቡት፤ ስሙንም "መና" አሉት፤ እርሱም በማር እንደተጋገረ ብስኩት ጣፋጭ ነበረ፤ በምድረ በዳ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር በየቀኑ መናን ሰጣቸው፤ ፈጽሞ አልተራቡም። ዳሩ ግን ሌሎች ችግሮች ነበሩ፤ በምድረ በዳ ፀሐዩ ያቃጥላል፣ ውሀም አልነበረም፤ ስለ ዚህ ሰዎቹ እንደገና አጉረመረሙ፤

"ስማ ሙሴ፣ ውሀ ስጠን፣ እዚህ ያመጣኸን በውሀ ጥም እንድንሞት ነውን?" አሉ። ሙሴም እንደገና ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፣

"በትርህን ውሰድና ዓለቱን ምታው፤ በዚህ ጊዜ የሚፈልጉትን ያህል እንዲጠጡ ለሁሉም የሚበቃ ውሀን ታገኛለህ።


አሁንም እግዚአብሔር እንደተናገረው አደረገ፣ ውሀም ከዓለቱ ውስጥ ወጣ፤ ሰዎቹ እግዚአብሔርን በመፈተናቸው ቢሳሳቱም እግዚአብሔር አልተዋቸውም፤

ለአርባ ዓመታት ያህል እግዚአብሔር ለሕዝቡ በምድረ በዳ ተጠነቀቀላቸው፤ የገባውን የተስፋ ቃል ሁሉ ፈጸመላቸው፤ በእርሱ ላይ መደገፍንና እርሱን ማመንን ሊያስተምራቸው በየቀኑ ምግብንና ውሀን ሰጣቸው።



## የእግዚአብሔር አሥሩ ትእዛዝ

ዘፀአት 19–24፤ 32–34



ሙሴ እግዚአብሔር እንዳዘዘው የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ዳርቻ በምድረ በዳው ውስጥ ወደ ሲና ተራራ አመጣቸው፤ መንገዱን እየመራቸው እግዚአብሔር ከፊታቸው ይሄድ ነበር፤ ሕዝቡ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር እንደሆነ ያውቁ ነበር፤ ምክንያቱም ከፊት ለፊታቸው ቀኑን ሙሉ በደመና ምስል፣ ሌሊት ደግሞ በእሳት ምስል ስለነበረ ነው። ወደ ሲናም በደረሱ ጊዜ በተራራው ሥር ድንኳን ተከሉ፤

እግዚአብሔርም በሙሴ በኩል ሕዝቡን ተናገረ፤ እንዲህ ሲል፦ "ከግብፅ አገር በሰላም አወጣኋችሁ፤ እናንተ ለኔ የተለዩ ሕዝቦች እንድትሆኑ እፈልጋለሁ፤ ትእዛዜን ትፈጽማላችሁን?" ሕዝቡም በአንድ ድምፅ "አዎን" አሉ፤

ከዚያም በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖራቸው ግንኙነት ልብሳቸውን ማጠብና ሠፈራቸውንም ማጽዳት ጀመሩ፤ እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፦ "ከነገ ወዲያ ሁሉም ሰው እንዲያየኝ በሲና ተራራ ላይ እወርዳለሁ"

በሦስተኛውም ቀን በተራራው ላይ መብረቅና ብርሃን እንዲሁም ጥቅጥቅ ያለ ደመና ሆነ፤ ሕዝቡም ተንቀጠቀጡ፤ እግዚአብሔር በቅርብ እንዳለ አወቁ።

ሙሴና አሮን ብቻቸውን ወደ ተራራው ሲወጡ ሕዝቡ ሊጠብቋቸው የሚገባውን አሥሩን ታላላቅ ትእዛዛት ሰጣቸው፤ እርሱም እንዲህ አላቸው:-

"እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ እኔን ብቻ አክብር አምልከኝም፤
"ሌሎች አማልክትን አታድርግ፤ አትስገድላቸውም
"ስሜን በክብር ያዝ
"ሰባተኛውን የእረፍት ቀን ጠብቅ
"አባትህንና እናትህን አክብር
"ሰውን አትግደል
"ባልና ሚስት ለእርስ በርሳችሁ ታማኝ ሁኑ፤ ወደ ሌላ ሴት ወይም ወንድ አትሂዱ፤
"አትስረቅ
"ውሸት አትናገር "የሌላውን ሰው ሀብት አትመኝ

እነዚህ የእግዚአብሔር አሥሩ ትእዛዛት ናቸው፤እነዚህ ትእዛዛት በተለያዩ ሁኔታዎች እንዴት በተግባር እንደሚተረጎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው፤ ሙሴም ለሕዝቡ ገለጸላቸው፤ ሕዝቡም ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ ተስማሙ፤ እግዚአብሔርም እነዚህን ሕዝቡ ይጠብቋቸው ዘንድ በድን ጋይ





ቅርጽ ጽላት ላይ እንደሚጽፋቸው ተናገረ፤ ሙሴም እነዚህን ለመቀበል ወደ ተራራው ወጣ። ሙሴ በተራራው ላይ በጣም ስለዘገየ ሕዝቡ ትእግሥት በማጣት ተቆጡ ለአሮንም እንዲህ አሉት:- "ከግብፅ ምድር ያወጣን ሙሴ ምን እንደነካው አናውቅም፤ ስለዚህ የሚመራን ሌላ አምላክ ሥራልን"

አሮንም ሕዝቡ የጆሮአቸውን ወርቅ እንዲሰጡት ጠየቀ፤ እነዚህንም በእሳት አቅልጦ የግብፅን አማልክት የሚመስል የወርቅ በሬ ሠራ፤ መሠዊያም ሠርቶ ድግሥ አደረገ፤ ሕዝቡም እንዲህ አሉ:-"ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን አምላክ ነው" እያሉ በታላቅም ድምፅ ይዘፍኑና ይጨፍሩ ነበር። እግዚአብሔርም ሕዝቡ እንዲህ በቀላሉ ቃላቸውን በማፍረሳቸውና ወደ ሌሎች አማልክት በመመለሳቸው ተቆጣ። ሙሴም ከተራራው ሲወርድ ሕዝቡ የሚያደርጉትን ባየ ጊዜ ተቆጣ፤

ትእዛዛቱ የተጻፉባቸውንም የድንጋይ ቅርጾች /ጽላቶች/ በምድር ላይ ወረወረና አደቀቃቸው። የወርቁንም በሬ ዱቄት እስኪሆን አደቀቀው፤ እርሱም፣ "አስከፊ ነገርን አድርጋችኋል" አለ፤ ቢሆንም ሙሴ ሕዝቡን አሁንም ይወድ ነበር፤ እግዚአብሔር ይቅር እንዲላቸውና ሁለተኛ ዕድል እንዲሰጣቸው ለመነ ስለዚህ እግዚአብሔር ትእዛዛቱን እንደገና ጻፈ። በዚህ ጊዜ ሙሴ ከተራራው ሲመለስ ምንም የወርቅ በሬና ድግሥ አልነበረም፤ ሙሴም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሲያስተምራቸው ሕዝቡ ያደምጡ ነበር፤ በመጨረሻም በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ስምምነቱ ወይም "ኪዳኑ" ታተመ።



# የእግዚአብሔር ልዩ ድንኳን

**ዘፀአት 25–30፤ ዘሌዋውያን**

እግዚአብሔር ለሙሴ በሲና ላሉት ሕዝቦቹ የሚሆን ብዙ ሕጎችን ሰጠው፤ እነዚህም ሕጎች ስለ መልካምና ክፉ፣ ስለጤንነት እንዲሁም ስለቅጣት የሚናገሩ ሕጎች ናቸው፤ እርሱም ሊኖራቸው ስለሚገባው ሥነ ምግባር፣ በመካከላቸው ስላለው ግንኙነት እንዲሁም እርሱን የሚያ መልኩበትንና የሚያገለግሉበትን መንገዶች ነገራቸው፤ እግዚአብሔር መልካም ነው፤ ትክክለኛና እውነተኛ በሆነ ነገር ሁሉ ደስ ይለዋል፤ ክፋትንና ስህተትን ሲያይ ይጠ ላል፤ በዚያን ዘመን በእስራኤላውያን ዙሪያ የነበሩ ሀገሮች የሚከተሉአቸው ሃይማኖቶች ብዙ ስህተቶች ነበራቸው። ብዙ አማልክትን ያመልኩ ነበር፤ በግብግቦ እያሳበቡ ይሰክሩ ነበር። ሴቶቻቸውን ያሰቃዩአቸው ነበር፤ አስማትን ይለማመዱ ነበር፤ እንዲያውም ልጆቻቸውን እያረዱ ለጣ ኦት መስዋዕት ያቀርቧቸው ነበር፤ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ሁሉ ጠላ፤ እንዲህም አለ:–

"እነዚህ ሕዝቦች በክፉ ሥራቸው አሳዝነውኛል፤ የእነርሱን ልማድ አትከተሉ፤ እናንተ ለእኔ የተቀደሳችሁ ናችሁ።" ስለዚህ እግዚአብሔር የሚፈልገውን የግብግቦ፤ የመስዋዕትና የአምልኮ ሥርዓት ለሙሴ ነገረው፤ ሙሴም ለሕዝቡ ገለጸላቸው። እግዚአብሔር እንዲህ አለ:–



"እኔ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር እንደምሆን ቃል ገብቻለሁ፤ ስለዚህ እንደ ራሳችሁ ያለ ልዩ ድንኳን /ማደሪያ/ ሥሩልኝ፤ እርሱም ከፍየል ቆዳ ሆኖ ጠርዙ በቀጭን ሀር የተዘመዘመ ይሁን፤ ቀጭን ሀሩም ቀይ፣ ጃኖና ሰማያዊ ሆኖ ክንፍ ባላቸው እንስሳት ምስል ያጌጠ ይሁን፤ በድንኳኑም ዙሪያ ለመስዋዕት የሚሆን አደባባይ አድርጉ፤ በድንኳኑም ውስጥ በመጋረጃ የተከለሉ ሁለት ክፍሎች አድርጉ፤

"በመጀመሪያው ክፍል ከካህናት በስተቀር ማንም አይ ገባም፤ በዚህ የድንኳኑ ክፍል የወርቅ መሰዊያ፣ ጠረጴዛና ሰባት መብራቶች ያሉበት መቅረዝ ታኖራላችሁ።

"የውስጠኛው ክፍል ለእኔ የተለየ ይሆናል፤ በዚህ ውስጥ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ በማስተሰሪያው ቀን ሊቀ ካህናቱ ለሕዝቡ ኃጢአት ለማስተሰረይ ይገባል፤

ደግሞም ከግራር እንጨት አንድ ሳጥን /የቃል ኪዳን ታቦት/ በወርቅ ለብጣችሁ ትሠሩና በእኔ ልዩ ክፍል ውስጥ ይቀመጣል። በውስጡም አሥሩ ትእዛዞቼ የተጻ ፉባቸውን የድንጋይ ቅርጾች /ጽላቶች/ ታስቀምጣላችሁ። መክደኛውንም ከንጹህ ወርቅ ሥርታችሁ በላዩ ላይ ክንፋቸው የተዘረጋ ከወርቅ የተሠሩ ሁለት እንስሶች ታደርጋላችሁ። እኔም በዚህ ቦታ ነው ከእናንተ ጋር የምገናኘው።"





ሰዎቹም እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ አደረጉ፤ እነርሱም በደስታ ወርቃቸውንና ዕንቁዎቻቸውን፣ ብሩንና ነሐሱን፣ ሐሩንና የእንስሳ ቆዳዎቹን ለእግዚአብሔር ድንኳን ሥራ ሰጡ፡፡ ለመብራትም ዘይትን፣ ለሚቃጠል ሽታም ቅመማ ቅመምን አመጡ፤ለዚህ ሥራም ጥበብ ያላቸው ሠራተኞች መፍተልና መሸመን፣ ማለስለስና መወልወል፡ የከበረ ድንጋይን መቅረጽ፣ ወርቁንና ብሩን መቀጥቀጥና ማስተካከል ተያያዙት፡፡


የእግዚአብሔርም ድንኳን በራሱ ፕላን ተሠርቶ በጣም ያማረ ሆነ፡፡ ሥራውም ከተፈጸመ በኋላ ድንኳኑን ደመና ሸፈነው፣ የእግዚአብሔርም ክብር ሞላው፡ ይህም እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ለመሆን መምጣቱን የሚያሳይ ምልክት ነበረ፡ እግዚአብሔርም አሮንን የመጀመሪያው ሊቀካህን እንዲሆንና ለበዓላቱና ለመስዋዕቶቹ አላፊ እንዲሆን መረጠው፡፡ ልጆቹም ካህናትና ሌዋውያን በመሆን ረዱት፡ /ሌዋውያን የያዕቆብ ልጅ የሌዊ ዘሮች ናቸው/

ሙሴም ለሕዝቡ...? ምንም እንኳን እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ቢሆንና በፍቅር ወደ እርሱ እንዲመጡ የሚፈልግ ቢሆንም ያለ አንድ ነገር ወደ እርሱ መቅረብ አይችሉም፡፡ እግዚአብሔር ፍጹምና መልካም ነው፡ ምንም ነገር ማንም ቢሆን ጉድለት ያለበት ወይም በኃጢአት የተበላሸ በእርሱ ዘንድ ሊኖር አይችልም፡፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር የእርሱ ፍጹም በጎነት የጎደለው ነው፡፡



ኃጢአትም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ግድግዳ ይሆናል፤ የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ በመጣስ የሚከፈለው የኃጢአት ዋጋ ሞት ነው፤ እግዚአብሔር ግን ሕዝቡን ስለወደደ ስህተት የፈጸመው ወንድ ወይም ሴት እንዳይሞት በእነርሱ ፈንታ የጠቦትን ወይም የግልገልን ሞት ተቀበለ፡፡ በዚህም ሕዝቡ የኃጢአታቸውን ዋጋ እየከፈሉ በፍቅር ወደእርሱ ለመቅረብ እንዲችሉ አደረገ፡፡ አሮን፣ ካህናቱና ሌዋውያኑ ለመስዋዕቶቹ ማለትም ለኃጢአት መስዋዕቶች፣ ለበደል መስዋዕቶችና ለሰላም መስዋዕቶች ኃላፊዎች ሆኑ፡፡ በዓመት አንድ ጊዜ በማስተሰረያው ቀን አሮን ራሱንና ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ለማስታረቅ ልዩ መስዋዕትን ለመላው ሕዝብ ያቀርብ ነበር፡፡ ደግሞም እግዚአብሔር ቅዳሜን /ሰባተኛውን ቀን/ የእረፍት ሰንበት አድርገው እንዲጠብቁት ሕዝቡን አዘዘ፡፡ እግዚአብሔርም ዓለምን በስድስት ቀን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አረፈ፡፡ ሕዝቡም ደግሞ ሰባተኛውን ቀን የእረፍት ቀን አድርገው በመጠበቅና የእግዚአብሔርን በጎነት በማስታወስ ዕረፍት ማድረግ አለባቸው፡፡*


ደግሞም እግዚአብሔር ለተለዩ ጉዳዮችና በዓመቱ ውስጥ ለተለዩ ጊዜያት የሚሆኑ በዓላትን ሰጣቸው፡፡ በፀደይ ወራት ከግብፅ ምድር መውጣታቸውን የሚያስታውሱበት የፋሲካና የቂጣ በዓል ነበረ፡፡



በበጋው መጀመሪያ አካባቢ የእህል የበኵራት በዓል ነበረ። በመከር ወራት ደግሞ፣ በጥሩምባና በድንኳን በዓላት ይደሰታሉ። እነዚህ እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲያደርጉ ያዘዛቸው ነገሮች ናቸው። ይህም እግዚአብሔር የሚፈልገው ዓይነት አምልኮ ነበረ። እነርሱም ወደ ድንኳኑ በተመለከቱ ጊዜ እግዚአብሔር በቅርብ እንዳለ ያስታውሱ ነበር፤ በሰንበትም እግዚአብሔር ዓለምንና በውስጧ ያለውን ሁሉ እንደፈጠረ ያስታውሱ ነበር።

በበዓላት ቀን እግዚአብሔር ያደረገላቸውን በጎ ነገር ሁሉ በማስታወስ በሕብረት የተለየ ምግብን በመብላት ይደሰቱ ነበር። መስዋዕቶቹ ደግሞ የራሳቸውን ኃጢአትና የእግዚአብሔርን ቅድስና የሚያስታውሱአቸው ሲሆኑ በተጨማሪም በወዳጅነት ወደ እርሱ ለመቅረብ ያስቻላቸውን ፍቅሩን ያስታውሱ ነበር።

*አይሁዶች አሁንም ቅዳሜን እንደ ሰንበት ይጠብቁታል፤ ክርስቶስ ግን እሁድ ቀን ከሞት ስለተነሣ ክርስቲያኖች ይህንን ቀን የተለየ ቀን አድርገው ይጠብቁታል።





# አመፅ

**ዘኍልቁ** 13–14፤ 17፣21



እስራኤላውያን እግዚአብሔር ሕጉን ከሰጣቸው ቦታ ከሲና ተራራ በምድረ በዳው ውስጥ በከነአን ዳርቻ ወዳለው ወደ ሰሜን ተጓዙ፤ ይህም እግዚአብሔር የሰጣቸው የተስፋው ምድር ነው። በቃዴስ ሳሉ ከአስራ ሁለቱ ነገዶች /ከአሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ዘሮች/ አንድ አንድ ሰው መርጠው ምድሪቱን እንዲሰልሉ ላኩአቸው። ይህ ወቅት ወይን የሚያፈራበት ወቅት ነበረ፤ ከአርባ ቀንም በኋላ ተመልሰው መጡ፤ ከእነርሱም ሁለቱ ትልቅ የወይን ፍሬ ዘለላ ተሸክመው ነበር፤ እነርሱም እንዲህ አሉ፣

"ከነአን መልካም ምድር ናት፤ ተመልከቱ ይህን ይዘን የመጣነውን ወይን፤ በለስና ፖም! ዳሩ ግን ምን ያደርጋል ከተሞቹ ጠንካሮች፣ ሰዎቹም እጅግ ግዙፎች ናቸው፤ የምንሄድ ከሆነ እንደ አንበጣ ይጨፈልቁናል፤" ሰዎቹም ይህን በሰሙ ጊዜ ተስፋ ቆረጡ፤ እንዲህም አሉ፦ "ከግብፅ ለምን ወጣን እንደገና እንመለስ፤" ከሰላዮቹ ሁለቱ የሆኑት ኢያሱና ካሌብ ግን እንዲህ አሉ፦"እነዚህ የሚሉትን አትፍሩ፤ ከነአን መልካም ምድር ናት፤ እግዚአብሔርን ለምን ትረሳላችሁ? እርሱ ከእኛ ጋር ከወጣ የሚያስፈራን ነገር የለም፤ ምድሪቱን ይሰጠናል፣ በእግዚአብሔር ላይ አታምጹ።"

ሰዎቹ ግን ለመስማት አልፈለጉም። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፣

"እናንተ እኔን የምታምኑኝ መቼ ነው? ለእናንተ ያደረግሁትን እንዴት እንዲህ ቶሎ ትረሳላችሁ? እንግዲህ እኔን ለማመን እምቢ ስላላችሁ በግብፅ አገር ተአምራቴን ያዩት ሰዎች ሁሉ እስኪሞቱ ድረስ በምድረ በዳ ለአርባ ዓመታት ትንከራተታላችሁ፤ ይህም ከኢያሱና ከካሌብ በስተቀር ነው፤ እነርሱ በእኔ ስለታመኑ ምድሪቱን እስኪወርሱ በሕይወት ይኖራሉ፤"

ሕዝቡም ይህንን በሰሙ ጊዜ ልባቸው አዘነ፤ አንዳንዶቹ ግን አሁንም የእግዚአብሔርን ቃል አላመኑም። እግዚአብሔር ቢከለክላቸውም ከነአናውያንን ለመውጋት ወጡ፤ ዳሩ ግን ተመቱ፤!

ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ሕዝቡ በምድረ በዳ መኖር ሰለቻቸው፤ በመሪዎቻቸውም ላይ አጉረመረሙና ተነሱባቸው፤ በሰፈሩ ውስጥ በገሃድ አመፅ ተነሣ፤ እንዲህም አሉ፦ "ሙሴና አሮን በእኛ ላይ ምን መብት አላቸው"

ሙሴም መልሶ እንዲህ አለ፦ "ለዚህ ሕዝብ መሪ የሚሆነውን እግዚአብሔር ይወስን፤ እያንዳንዱ ነገድ መሪ ይምረጥና ስሙን በለውዝ በትር ላይ ይጻፍበት፤ አሮንም ለራሱ ነገድ ለሌዋውያን መሪ ይሆናል፤ ዛሬ ማታ አሥራ



ሁለቱን የለውዝ በትሮች በእግዚአብሔር ድንኳን ውስጥ እናስቀምጣለን፤ የእርሱም በትር ያበበችለት ሰው እግዚአብሔር የመረጠው መሪ ይሆናል።"

እነርሱም ሙሴ እንዳለው አደረጉ፤ በነገውም ጧት በአሮን በትር ላይ እምቡጥና አበባ የበሰለም ለውዝ ነበረበት፤ ሌሎቹ ግን ባዶ ነበሩ፤ በዚህ ጊዜ አመፀኞቹ ፀጥ አሉ።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ አሮን ሲሞት እንደገና ማጉረምረም ጀመሩ፤ "ከግብፅ ለምን ወጣን በዚህ ምግብና ውሀ የለም፤ በየቀኑ መና መብላት ሰለቸን፤"

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር አመፀኞቹን ቀጣቸው፤ መርዛማ እባቦች ወደ ሠፈሩ ገቡና ብዙ ሰዎች ሞቱ፤ ከዚያም በኋላ የቀሩት ወደ ልባቸው ተመለሱ፤ እንዲህም አሉ፦

"ስማ ሙሴ፣ በእግዚአብሔር ላይ በመናገራችን በጣም ተሳስተናል፤እባቦችን እንዲያስወግድልን እርሱን ለምንልን"

ሙሴም ሲጸልይ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፦

"የነሐስ እባብን ሠርተህ ሕዝቡ እንዲያዩት በእንጨት ላይ ስቀለው፤ የተነከሱት ሁሉ የተሰቀለውን የነሐስ እባብ ብቻ ይመልከቱ፤ በሕይወትም ይኖራሉ፤" ስለዚህ እግዚአብሔርን በማመን እርሱ እንደተናገረው ያደረጉት ሁሉ ዳኑ።



ኢያሱ 2

# ረአብና ሰላዮቹ

አርባ ዓመታት አለፉ፤ ሙሴም ሞተና በእርሱ ቦታ የመሪነቱን ቦታ እንዲወስድ እግዚአብሔር ኢያሱን መረጠ፤ የተስፋይቱንም ምድር ከነአንን የሚወርሱበት ጊዜ ደርሶአል፤ እስራኤላውያንም ከዮርዳኖስ ወንዝ ራቅ ብለው ከኢያሪኮ ከተማ ፊት ለፊት ሰፍረዋል፤ ኢያሱም ከወንዙ ማዶ ሁለት ሰላዮች ላከ፤

እንዳይጠረጠሩም ሌሊቱን ረአብ በምትባል በአንዲት ሴተኛ አዳሪ ቤት አደሩ፤ ዳሩ ግን የኢያሪኮ ንጉሥ ስላወቀ እነርሱን ለመያዝ ሰዎችን ላከ፤ ረአብ ግን ሰላዮቹን በቤቱ ጣራ ላይ እንዲደርቅ ባሰጣችው የተልባ እግር ሥር ደበቀቻቸው። የንጉሡም መልእክተኞች በመጡ ጊዜ ሰላዮቹ ሄደዋል ብላ ነገረቻቸው።



ከዚያም ወደ ሰላዮቹ ሄዳ እንዲህ አለቻቸው፦ "እግዚአብሔር ይህችን ምድር ለእስራኤላውያን እንደሰጠ አውቃለሁ፤ ከግብፅም ምድር እንዴት እንዳወጣችሁ በሰማን ጊዜ ሁላችንም ፈርተናል፤ ከተማይቱን በወሰዳችሁ ጊዜ እኔንና ቤተሰቤን እንድታድኑን ቃል ግቡልኝ"

ሰዎቹም መልሰው "ሕይወታችንን አድነሻል፤ እኛ ያደረግነውን ለማንም ካልነገርሽ ቃል እንገባልሻለን" አሏት። ረአብ የምትኖረው ከከተማው አጥር ጋር ተጋጥሞ በተሠራ ቤት ውስጥ ነበር። ስለዚህ ሰዎቹን በመስኮት በገመድ አውርዳ ለቀቀቻቸው። እነርሱም ወሬውን ለኢያሱ ለመንገር አመለጡ፤ ከመሄዳቸው በፊት ግን ከተማዋን ሊማርኩ በመጡ ጊዜ የእርስዋ ቤት የትኛው እንደሆነ ለማወቅ እንዲችሉ በመስኮትዋ በኩል ቀይ ክር እንድታንጠለጥል ለረአብ ሰጡአት።



# ኢያሪኮ የምሽግ ከተማ

ወቅቱ የፀደይ ወራት ነበር፤ በሰሜን በኩል በተራሮቹ ላይ ያለው በረዶ ስለቀለጠ የዮርዳኖስ ወንዝ ሞልቶ ወደ ውጭ እየፈሰሰ ነበር። የእስራኤል ሕዝቦችም ወንዙን ለመሻገር ተዘጋጅተዋል፤ በወንዙ ላይ ድልድይ ወይም ቀላል መሻገሪያ ቦታ አልነበረም፤ እግዚአብሔር ግን የሚሻገሩበት ጊዜ አሁን መሆኑን ነግሮአቸዋል፤ ካህናቱም የእግዚአብሔር ትእዛዛት ያሉበትን ታቦት ተሸክመው ከፊት ለፊት ነበሩ፤ ሕዝቡም የሚሆነውን ነገር ለማየት ይጠባበቁ ነበር።

ካህናቱም ወደ ወንዙ መግባት ሲጀምሩ አንድ የሩቅ ድምፅ ተሰማ። ከዚያም የውሀው ከፍታ ዝቅ አለ፤ የወንዙም ዳርቻ አፈር ተደረመሰና ወንዙን ገደበው፤ ውሀውም ወደላይ ተከመረ፤ እስራኤላውያን ግን በኢያሪኮ ፊት ለፊት በወንዙ ላይ በደረቅ መሬት ተሻገሩ፤ በዚህ ዓይነት ከግብፅ ምድር ያወጣቸው አምላክ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሊያስገባቸው እንደገና ኃይሉን አሳየ፤

ሰዎቹም በደህና በተሻገሩ ጊዜ ከወንዙ ውስጥ አሥራ ሁለት ድንጋዮችን /ለእያንዳንዱ ነገድ አንድ አንድ ድንጋይ/ ይዘው ተሻገሩ፤ ከወንዙም ዳርቻ ላይ ከመሩአቸው።

እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፦ "እነዚህ ድንጋዮች ምልክቶች ይሁኑ፤ በሚመጡት ዘመናትም ልጆቻችሁ ባዩአቸው ጊዜ በእንዴት ያለ ድንቅ ሥራ ወደዚህ ምድር እንዳመጣችኋቸው ትነግሩአቸዋላችሁ።"




ከዚያም በኋላ ውሀው ግድቡን በመጣስና ወንዙን በመሙላት እንደ ቀድሞው ተርፎ ይፈስስ ጀመር፤ የተደረገውን ነገር አመልካች የሆነው የድንጋዩ ክምር ብቻ በዚያው ቀረ።

እስራኤላውያንም በኢያሪኮ አጠገብ ሠፈሩ፤ የፋሲካ በዓልም ደርሶ ነበር፤ በሚቀጥለው ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ ከተስፋይቱ ምድር ከከነአን በተገኘ እህል ዳቦን ጋገሩ፤ ከዚያም ቀን ጀምሮ አንዳችም "መና" አልነበረም። ምክንያቱም የምድረ በዳ ጉዞአቸው አለቀ፤ አሁን በምድሪቱ ፍሬ ሊደሰቱ ይችላሉ።

ኢያሪኮ ረጅም ታሪክ ያላት ከተማ ነበረች፤ ብዙ ስፋት ባላቸው የግምብ አጥሮች የተከበበች ነበረች። እስራኤላውያን እዚያ በደረሱ ጊዜ የከተማዋ በሮች ተዘግተውና ተቆልፈው ነበር። በእስራኤላውያን ምክንያት ማንም መግባትና መውጣት አይችልም ነበር።


እግዚአብሔር ለኢያሱ ተናገረው፦"ኢያሪኮ የእናንተ ነች፤ ከተማዋን፣ ንጉሡንና ታላላቅ ሰዎቿን አሳልፌ እሰጣችኋለሁ፤ የምታደርጉት ይህንን ነው፦ ለስድስት ቀናት በተከታታይ በከተማዋ ዙሪያ በቀን አንድ ጊዜ ትዞራላችሁ፤ ሰባት ካህናት ጥሩምባ እየነፉ ታቦቱን በተሸከሙት ሰዎች ፊት ይሄዳሉ፤ የቀሩት በፀጥታ ይጓዛሉ።



"በሰባተኛው ቀን ብቻ በከተማይቱ ዙሪያ ሰባት ጊዜ ትዞራላችሁ፤ ጥሩምባውም በተነፋ ጊዜ ሰዎቹ በታላቅ ድምፅ ይጮኻሉ፤ የከተማዋም አጥር ይፈርሳል፤ ኢያሪኮም የእናንተ ትሆናለች።"

ኢያሱም ለሕዝቡ ትእዛዙን አስተላለፈ። እነርሱም ልክ እግዚአብሔር እንደተናገረው አደረጉ፤ በሰባተኛው ቀን በከተማዋ ዙሪያ ሰባት ጊዜ ተጓዙ፤ ጥሩምባውም ተነፋ፤ ኢያሱም ለሕዝቡ እንዲህ አለ "እግዚአብሔር ከተማዋን ስጥቶናልና ጩኹ!"

እነርሱም ታላቅ ጩኸት ሲጮኹ የከተማዋ አጥር ፈረሰ፡ ከዚያም ገቡና ከተማዋን ወረሱ፤ ሰላዮቹ ቃል ከገቡላት ከረአብና ከቤተሰብዋ በስተቀር ማንም አልዳነም፡ እነርሱም ብርንና ወርቅን፣ ነሐስንና ብረትን ለእግዚአብሔር ድንኳን ግምጃ ቤት ወሰዱ። ከዚያም ከተማይቱን በእሳት አቃጠሏት። በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር ለሕዝቡ በከነአን የመጀመሪያውን ድል ሰጣቸው። የኢያሱም ዝና በአገሩ ሁሉ በመስፋፋቱ ሰው ሁሉ ይፈራው ነበር።







# እስራኤል በተስፋይቱ ምድር


ኢያሱ 7–9፤ 14:24

ኢያሪኮን እንዲያጠፉአት እግዚአብሔር ለሕዝቡ ተናግሮ ነበር፤ አንዳችም ነገር ለራሳቸው እንዳይወስዱ ከልክሎ ነበር፤ ዳሩ ግን አካን የሚባል አንድ ሰው ትእዛዝ አፈረሰ። አንድ ቆንጆ ካባና ጥቂት ወርቅና ብር ለራሱ ሠረቀ። ማንም አላየውም ነበር። እግዚአብሔር ግን አውቆአል። ስለዚህ የእስራኤል ሰዎች በጋይ ወዳለው ምሽግ ሲጓዙ ተመቱ፤ ለእግዚአብሔር ካልታዘዙ በስተቀር ከእነርሱ ጋር በመሆን ድልን ሊሰጣቸው አይችልም። አካን ተቀጣ፤ ኢያሱም ጋይን ለማጥቃት እንደገና ተዘጋጀ፤ በዚህ ጊዜ ከተማይቱን በድንገት እንዲወስድ እግዚአብሔር ነገረው።

ኢያሱም ግልጽ የሆነ ዕቅድ አወጣ። በዚያች ሌሊት ምርጥ የሆኑትን ጥቂት ሰዎች ከከተማዋ ራቅ ብለው እንዲደበቁ ላካቸው። በሚቀጥለው ቀን ማለዳ ወታደሮቹን ወደ ከተማይቱ በር ወሰዳቸው፤ የጋይም ሰዎች ለመዋጋት ሲወጡ ኢያሱ የጠላትን ወታደሮች ከከተማዋ ለማስወጣት አስቦ የራሱን ሰዎች ተመልሰው ወደኋላ እንዲሸሹ አዘዛቸው።

ከዚያም ኢያሱ ለተደበቁት ሰዎች ምልክት ሰጣቸው። እነርሱም በቀጥታ ወደ ከተማዋ ገቡና በእሳት አቃጠሏት። ኢያሱና ሰዎቹም ጭሱን ባዩ ጊዜ ተመለሱ፤ የጋይም ወታደሮች በሁለቱ የእስራኤላውያን ኃይሎች መካከል ተያዙ።





በአቅራቢያውም ባለው በገባዖን የሚኖሩ ሕዝቦች ኢያሪኮን እንዳጠፏትና የጋይንም ሰዎች እንዳሸነፉአቸው ሰሙ፤ እነርሱም ለመሞት አልፈለጉም፤ ግን ኢያሱን ለሰላም በምን ዓይነት ሊያግባቡት ይችሉ ይሆን?

ከጥቂት ቀናት በኋላ ኢያሱ ጥቂት የደከሙ መንገደኞች ወደ ሰፈሩ ሲመጡ ተመለከተ፤ ጫማቸው ያለቀ ልብሳቸውም የተቦጫጨቀ ነበር።

ኢያሱም "እናንተ እነማን ናችሁ፤ ከወዴትስ መጣችሁ?" አላቸው። እነርሱም የመጣነው ከሩቅ አገር ነው፤ "እግዚአብሔር ከግብፅ እንዴት እንዳወጣችሁ ስለሰማን ከእናንተ ጋር እርቅ ለማድረግ መጣን፤ እንጀራችን እንዴት እንደሻገተ ተመልከቱ፤ መንገድ ስንጀምር ትኩስ ነበር፤ ልብሳችንም እንደምታዩት በጉዞ ላይ አለቀ" አሉ።

ኢያሱና ሕዝቡም ከሰዎቹ የወዳጅነት ስምምነት አድርገው ቃላቸውን ለመጠበቅ ተስማሙ፤ ከሦስት ቀን በኋላ ግን የደከሙ የመሰሉት መንገደኞች የመጡት በቅርብ ካለችው ከገባዖን እንደሆነ አወቁ፤! እነርሱም በጣም ተናደዱ፡ ዳሩ ግን ቃላቸውን ጠበቁ።

በዚህ መካከል ላይ በከነአን አገር ባሉ በተለያዩ ከተማዎች ያሉት ነገሥታት ኃይላቸውን አስተባብረው በአንድነት ጠላትን ለመግጠም ተዘጋጁ።

ኢያሱም በደቡብና በሰሜን በተደረጉት ሁለት የውጊያ ዘመቻዎች ወታደሮቹን መራ፤ ታላላቅ ድልንም አገኙ። ጥቂት በጥቂት እስራኤላውያን የተስፋይቱን ምድር ከነአ ንን ድል አደረጉ። ዳሩ ግን ሁሉንም የጠላት ሕዝቦች ለማስወጣት አልቻሉም።

ካሌብ ከዚህ በፊት ከኢያሱና ከሌሎቹ አሥር ሰላዮች 
ጋር ሆኖ ምድሪቱን ለሙሴ ሊሰልል ሄዶ ነበር፤ አሁን የሰማንያ አምስት ዓመት ሽማግሌ ሆኖአል። ዳሩግን አሁንም ገና ጠንካራና ጎበዝ ነበር። በእግዚአብሔርም ይታመን ነበር። እርሱም ለኢያሱ እንዲህ አለው፣ "እነዚህ ግዙፍ ሰዎች ያሉበትን ተራራማውን አገር ስጠኝ፤ እኔም በእግዚ አብሔር ኃይል አባርራቸዋለሁ።"

ስለዚህ ኢያሱ የኬብሮንን ከተማ ሰጠው፤ ካሌብም ግዙፎቹን ሰዎች አስወጣቸው፤!

ኢያሱም የከነአንን ምድር ከፋፈለ፤ እያንዳንዱ ነገድ የራሱን መሬት አገኘ። እስራኤላውያንም ተቀምጠው ምድሪቱን ማረስ ጀመሩ።

እያሱም በሽመገለ ጊዜ ሕዝቡን ሁሉ አንድ ላይ ሰበሰበ፤ እንዲህም አለ፣

"እግዚአብሔር ቃል የገባልንን መልካም ነገሮች ሁሉ ሰጥቶናል፤ ተስፋው ሁሉ ተፈጽሞልናል፤ አሁን ደግሞ እናንተ ቃላችሁን በመጠበቅ ተስፋ ትሰጣላችሁን? እርሱን ታመልካላችሁን?"

ሕዝቡም መልሰው "እርሱ አምላካችን ነውና እርሱን እናመልካለን" አሉ፤ ኢያሱም በሕይወት እስካለ ድረስ ቃላቸውን ጠበቁ።



# የጌዴዎን ሦስት መቶ ሰዎች

መሳፍንት 6 – 7

ዓመታት አለፉ፡ ኢያሱም ሞተና ሕዝቡ ወዲያውኑ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ሁሉ ረሱ፡ እግዚአብሔርን ብቻ ለማምለክ የገቡትን ቃልም ረሱ። በአካባቢአቸው ያሉትን የአህዛብ አማልክት ማምለክ ጀመሩ።

ከዚያም በኋላ በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምሥራቅና በምዕራብ ያሉት ጠላቶቻቸው ችግር ይፈጥሩባቸው ጀመር። እስራኤላውያንም ወደ ልባቸው እየተመለሱ ለእርዳታ ወደ እግዚአብሔር በጮሁበት ጊዜ ሁሉ ጠላቶቻቸውን የሚመልሱ ኀበዝ መሪዎችን ላከላቸው። ከነዚህም መካከል፣

ኀቶንያል ናዖድ ሰሜጋር
ዴቦራና ባርቅ ጌዴዎን. . . . . . .. ናቸው።

በጌዴዎን ጊዜ ችግር የፈጠሩት ምድያማውያን የተባሉት የምድረ በዳ ወራሪ ነገዶች ነበሩ፡ እነዚህም በግመሎች ላይ የተቀመጡ እንደ አንበጣ መንጋ ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ነበር። የእስራኤላውያንን በጎች ከብቶችና አህዮች ይወስዱባቸው ነበር። እህላቸውንም ይበሉባቸው ነበር። የእስራኤልም ሕዝቦች ወደ እግዚአብሔር ጮኹ። እግዚአብሔርም መልእክተኛውን ወደ ጌዴዎን ላከ፡ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡– "ከምድያማውያን እጅ እስራኤልን እንድታድን እልክሃለሁ።"

ጌዴዎንም ልቡ ትር ትር አለ፡ ብዙ መተማመኛ ፈለገ፡ ምልክትንም ጠየቀ። "እንዲህም አለ፣ ጥቂት የበግ ፀጉርን በመሬት ላይ አስቀምጣለሁ፡ በነገውም ጧት በሜዳው ላይ ጤዛ ሳይኖር በፀጉሩ ላይ ብቻ ጤዛ ካለ እስራኤልን እንደምታድን የምትልከኝ መሆኑን አውቃለሁ።"





በማግሥቱም ጧት ከጠጉሩ የጨመቀው ውሀ በትልቅ ጎድጓዳ ሳህን ሞላ። መሬቱ ግን ደረቅ ነበረ፡ ዳሩ ግን አሁንም እንደገና ምልክትን ጠየቀ፡ በዚህ ጊዜ ግን መሬቱ ጤዛማ፣ ጠጉሩ ግን ደረቅ እንዲሆን ነበር። እግዚአብሔርም እንደገና የፈለገውን ምልክት ሰጠው።

ስለሆነም ጌዴዎን ለውጊያ ሕዝቡን ጠራ፡ እርሱና የጦር ሠራዊቱም ከምድያማውያን ሠፈርና ከሸለቆው ባሻገር በሐሮድ ምንጭ አጠገብ ሠፈሩ።

እግዚአብሔር ግን እንዲህ አለ፡– "በጣም በዝታችኋል፡ ፍርሃት ያለበት ማንም ሰው ወደ ቤቱ እንዲሄድ ንገር" ሃያ ሺህ ወደ ቤታቸው ሄዱ! አሥር ሺህ ብቻ ቀሩ። እግዚአብሔርም እንደገና አሁንም ገና ብዙ ናቸው፡ ወደ ታች ወደ ውሀው አውርዳቸውና በእፍኛቸው እየቀዱ፣ እንደ ውሻ በምላሳቸው የሚጠጡትን በጉልበታቸው ተንበርክከው ከሚጠጡት ለያቸው" አለው።

በእጃቸው የጠጡት ሦስት መቶ ብቻ ነበሩ። እግዚአ ብሔርም ሌሎቹን ሁሉንም ወደ ቤታቸው እንዲሄዱ ንገራ. ቸው። በሦስት መቶው ብቻ ድልን እሰጥሃለሁ" አለው።



በዚያች ሌሊት ጌዴዎን የምድያማውያንን ሠፈር አቃጠለ፤ ሰዎቹንም በሦስት ቡድን ከፈላቸው። እያንዳንዱ ሰው ቀንደ መለከትና /ጥሩምባ/ በውስጡ የችቦ መብራት ያለበት ማሰሮ ያዘ፤ ሰዎቹም በጠላት ሠፈር ዙሪያ ቦታቸውን ያዙ። ከዚያም ጌዴዎን ምልክት ሲሰጥ በድንገት ሁሉም በአንድነት ጥሩምባቸውን እየነፉ ማሰሮውን ሰበሩት፤ በዚህ ጊዜ የሚያስደነግጥ ድምፅና የሚያንፀባርቅ ብርሃን ሆነ፤ እነርሱም "የእግዚአብሔርና የጌዴዎን ሰይፍ" ብለው ጮሁ፤ በዚህ ጊዜ ጠቅላላው የጠላት ሠራዊት እጅግ ደንግጠው እግሬ አውጭኝ በማለት በረሩ፤ አንዳንዶቹ ከፍርሃት የተነሣ እርስ በርሳቸው ተጋደሉ፤ የቀሩትን ደግሞ የጌዴዎን ሰዎች ከሌሎች እስራኤላውያን ጋር በመሆን አባረሩአቸው።

ስለዚህ ጌዴዎን ምድያማውያንን አሸነፋቸው፤ ምድሪቱም ከእነርሱ ለአርባ ዓመታት አረፈች።

# ጉልበተኛው ሳምሶን



*መሳፍንት* 13 – 16

ምንም እንኳን እግዚአብሔር ሕዝቡን ሁልጊዜ በየጊዜው ያዳናቸው ቢሆንም እነርሱ ወዲያውኑ ይረሱት ነበር። የአካባቢአቸውን የአህዛብን አማልክት የአየርና የጦርነት አማልክት የመሳሰሉትን አመለኩ። ብዙ ሳይቆዩም እንደገና በችግር ውስጥ ገቡ። ከሁሉም በላይ አብዛኛውን ጊዜ ችግር የመጣባቸው በደቡብ ምዕራብ በኩልካሉት ከፍልስጥኤማውያን ነበር። እነርሱም ለአርባ ዓመታት እስራኤላውያንን ገዙአቸው።

ከዕለታት አንድ ቀን እግዚአብሔር በጾርዓ ወደሚኖር ማኑሄ ወደሚባል ሰውና ወደ ሚስቱ መልእክት ላከ፤ እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፦ "ወንድ ልጅን ትወልዳለህ እርሱም ባደገ ጊዜ እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን እጅ ያድናል።"

ማኑሄና ሚስቱ ከተጋቡ ጀምሮ ለብዙ ዓመታት ልጆች አልነበሩአቸውም፤ ስለዚህ በዚህ ዜና በጣም ተገረሙ፤ ዳሩ ግን በጊዜው ልጁ ሲወለድ በጣም ደስ አላቸው፤ ስሙንም ሳምሶን አሉት፤ ፀጉሩንም ፈጽሞ አይላጩትም ነበር፤ ይህም ሳምሶን በልዩ መንገድ ለእግዚአብሔር የተለየ መሆኑን የሚገልጽ ምልክት ነበር። ስለዚህ ሳምሶን አደገና በጣም ጠንካራ ሆነ።

ከዕለታት አንድ ቀን ሳምሶን በወይን አትክልት ውስጥ ሲሄድ ሳለ አንበሳ በላዩ ላይ ወጣበት፤ ሳምሶንም አንበሳውን በባዶ እጁ አነቀና ጣለው፤ ከዚያም እግዚአብሔር የተለየ ኃይል ለእርሱ እንደሰጠው ስላወቀ ይህንን ኃይል ፍልስጥኤማውያንን ለማጥቃት ይጠቀምበት ጀመር።





ወዲያው ሁሉም ሰው ስለ እርሱ ይናገር ነበር። "የፍልስ ጥኤማውያንን እህል እንዴት እንዳቃጠለ ሰምታችኋልን? የተለኮሱ ችቦዎችን በቀበሮዎች ጭራ ላይ አስሮ በለቀቃ ቸው ጊዜ እህሉን አቃጠሉት። "ሳምሶን በእጁ ምንም የጦር መሣሪያ ሳይኖር በአህያ መንጋጋ ብቻ አንድ ሺህ ፍልስጥኤማውያንን እንደገደለ ሰምታችኋለን?"

"ከጋዛ እንዴት እንዳመለጠ ሰምታችኋልን? በሩን ከሁለቱ ምሰሶዎች ጋር ከመሬት ነቅሎ ተሸከመው።" ". . . ሰምታ ችኋልን?" እያሉ ይነጋገሩ ነበር። ፍልስጥኤማውያን በቁጣ ጥርሳቸውን ነከሱ፣ ሳምሶንንም ለመግደል ተነሱ፤! ሳምሶን ደሊላ ከተባለች ከአንዲት የፍልስጥኤም ቆንጆ ሴት ጋር በፍቅር ተጠመደ፣ ይህም ለጠላቶቹ መልካም ዕድል ሆነ፣ እርስዋም "የምትወደኝ ከሆነ የኃይልህን ምስጢር ምን እንደሆነ ንገረኝ" እያለች በየቀኑ ትጨቀጭቀው ነበር። /የፍልስጥኤማውያን ነገሥታት ትክክለኛውን መልስ ካገ ኘች 1100 ብር እንደሚ ሰጧት ቃል ገብተውላት ነበር/ በመጀመሪያው ሳምሶን አታለላት።"በሰባት እርጥብ ጠፍር ብታስሪኝ እንደ ማንኛውም ሰው ደካማ እሆናለሁ።" "ረጅም ፀጉሬን ከድር ጋር ጎንጉኚው". . . አላት።





ዳሩ ግን በመጨረሻ በጣም ስላደከመችው እውነቱን ነገራት፣ እንዲህም አላት፡- "ፀጉሬ ተቆርጦ አያውቅም፣ ይህም ለእግዚአብሔር የተለየሁ ለመሆኔ ምልክት ነው፣ ኃይሌም የተገኘው ከእርሱ ነው።" ደሊላም እንቅልፍ እስኪወስደው ድረስ ራሱን አሻሸችው። ከዚያም ለፍልስጥ ኤማውያን አሳልፋ ሰጠችው፤ ፍልስጥኤማውያንም መጥ ተው ፀጉሩን ሲቆርጡት የሳምሶን ኃይል ጠፋ፣ ዓይኑንም አውጥተው በሰንሰለትም አስረው ወደ ጋዛ ከተማ አመ ጡት። በዚያም በእስር ቤት እህል እንዲፈጭ አስገደ ዱት። ጊዜው አለፈ። የሳምሶንም ፀጉር እንደገና አደገ። አሁን ኃይሉ የእርሱ እንዳልሆነ በእርግጥ አወቀ። እግዚአብሔር ለተለየ ጉዳይ ይህን ኃይል ሰጥቶት ነበር።

ፍልስጥኤማውያን ለአምላካቸው ለዳጎን ክብር ግብዣ አድርገው ነበር። ሳምሶንንም በዳጎን ቤተመቅደስ አግብ ተው ይቀልዱበት ነበር። ብዙ ሰዎችም በዚያ ቦታ ተሰብስ በው ነበር። ሳምሶንም ወደ እግዚአብሔር እየጸለየ ቤቱን የተሸከሙትን ሁለት ምሶሶዎች በእጁ ይዞ በሙሉ ኃይል ገፋቸው።

የቤቱም ግምብ ተናደና በውስጡ ያሉትን ሰዎች ሁሉ ገደላቸው። ይህም የሳምሶን የመጨረሻውና ከፍተኛው ተግባር ነበር።







# ሩት ከቤትዋ ወጣች

ሩት

በተራራማዋ በትንሿ በቤተልሄም ከተማ ሰው ሁሉ ተርቦ ነበር:: የነበረው ሰብል ሁሉ ደርቆ ነበር አቤሜሌክም ለሚስቱ ለኑኃሚን አንድ ቀን እንዲህ አላት:- "የምንበላው ምግብ የለንም፤ የሚያስፈልገውን ጓዝ ጠቅልይ፣ ነገ ልጆቹን ይዘን እንሄዳለን::"

ኑኃሚንም "ወዴት ነው የምንሄደው?" ብላ ጠየቀች:: አቤሜሌክም መልሶ፣ "ከዮርዳኖስ ባሻገር ወደ ሞአብ እንሄዳለን፣ በዚያ ብዙ የሚበላ አለ" አላት::

ስለዚህ አቤሜሌክና ኑኃሚን ከሁለት ወንዶች ልጆቻቸው ጋር በሞአብ ምድር ሊኖሩ ሄዱ::

ልጆቹም አደጉና ኦርፋና ሩት የተባሉ ሁለት ሞአባውያን ልጃገረዶችን አገቡ:: አቤሜሌክም ሞተ:: ከአሥር ዓመታት በኋላም ሁለቱ የኑኃሚን ወንዶች ልጆች ደግሞ ሞቱ:: እርስዋም ብቻዋን ቀረች::

ከዚያም በቤተልሄም የነበረው ትልቁ የረሃብ ዘመን አልፎአል የሚል ዜና መጣ:: ኑኃሚንም ወደ አገርዋ ለመመለስ ውሳኔ አደረገች::

ሩትም ይህን ሁሉ መንገድ ብቻሽን አትሄጅም አለቻት:: ኦርፋም እንደዚሁ አለች:: ስለዚህ ኦርፋና ሩት ቤታቸውን ትተውና ኑኃሚንን ተከትለው ወደ ቤተልሄም ጉዞ ጀመሩ::

ዳሩ ግን በመንገድ ላይ እነርሱ እንዲመለሱና እንደገና ባል እንዲያገቡ ኑኃሚን ልታግባባቸው ሞከረች:: እነርሱ ከእርስዋ ለመለየት አልፈለጉም:: እርስዋ ግን የግድ አለቻቸው:: ኦርፋ ኑኃሚን ደህና ሁኚ ብላ ስትስማት አለቀሰች:: ሆኖም ወደ ቤቷ ተመለሰች:: ሩት ግን ለመመለስ እምቢ አለች:: እንዲህም አለቻት:- "እንድተውሽ አታስገድጂኝ፡ ወደ ሄድሽበት ሁሉ እሄዳለሁ፤ ሕዝብሽ ሕዝቤ ይሆናል፤ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል::" ስለዚህ ሩትና ኑሃሚን በአንድነት መንገዳቸውን ቀጠሉ::









በሚያዝያ ወር ወደ ቤተልሄም ደረሱ፤ ገበሬዎቹም ገብስ አጨዳ ጀምረው ነበር:: የኑኃሚንም የቀድሞ ጓደኞች እንደገና ስላዩአት በጣም ተገረሙ:: ኑኃሚን ግን አዝና ነበር:: በመጨረሻ ወደ ቤትዋ መጣች::ግን ባሏና ልጆችዋ ሞተዋል::

ኑኃሚንና ሩት በጣም ድሆች ነበሩ:: ሩት በየቀኑ ወደ እህል ማሳዎች ትሄድ ነበር:: ከእህል አጫጆች በስተኋላ እየሄደች የወደቀውን ቃርሚያ ትለቅም ነበር:: ማታ ማታም ዳቦ ለመጋገር ትፈጨው ነበር:: እርስዋ አታውቅም ነበር እንጂ ቃርሚያ ትለቅምበት የነበረው ሰብል የኑኃሚን ዘመድ የሆነ የአንድ ባለጠጋ ሰው ነበረ:: ስሙም ቦኤዝ ይባል ነበር::

አንድ ቀን ቦኤዝ ባያት ጊዜ "ያች ማን ናት?" ብሎ ጠየቀ፤ ሠራተኞቹም መልሰው "ከኑኃሚን ጋር የመጣችው እንግዳ ልጅ ናት፤ ከማለዳ ጀምራም ያለ እረፍት ስትለ ቅም ውላለች" አሉት:: ቦኤዝም ለሩት "ከሠራተኞቼ ጋር በዚሁ ቆዪ፤ ውሀም ቢጠማሽ ከተሞላው እንስራ ጠጪ፤ ለኑኃሚን ያደረግሽውን ቸርነት ሰምቻለሁ፤ ከእርሷ ጋርም ለመምጣት ዘመዶችሽን እንደተውሽ ሰምቻለሁ እግዚአብሔር ዋጋሽን ይስጥሽ" አላት::

በዚያም ምሽት ወደ ቤቷ ስትመለስ ሩት የሆነውን ሁሉ ለኑኃሚን ነገረቻትና ኑኃሚንም በጣም ተደሰተች:: ቦኤዝም ጥሩ ሰው እንደሆነ ታውቅ ነበር:: ሩትም እር ሱን እንድታገባው ፈለገች::



በዚያን ዘመን በእስራኤል አገር አንድ ሰው ሲሞት የቅርብ ዘመዱ የሟቹን ቤተሰብ መጠበቅ ነበረበት፣ ኑኃሚንም በዚህ መብት በመጠቀም ቦኤዝ ሩትን እንዲያገባ ልትጠይቀው ፈለገች። እርስዋም ቦኤዝ እህሉን ከሌቦች ለመጠበቅ ሌሊቱን በአውድማው አጠገብ እንደሚያድር አወቀች። እርስዋም ቀኑ ሲጨልም በምስጢር ሩትን ወደ እርሱ ላከቻት።

ቦኤዝም ለሩት እንዲህ አላት፤"እሺ ማለቴን ለኑኃ ሚን ንገሪአት። እኔ አገባሻለሁ። ዳሩ ግን ከኔ ይበልጥ የቀረበ ዘመድ አለ። አስቀድሞ እርሱን መጠየቅ አለብኝ።"

በሚቀጥለው ቀን ቦኤዝ የኑኃሚንን የቅርብ ዘመድ በከተማው በር አጠገብ አገኘው። ይህ ሰውዬ የራሱ ቤተ ሰብ ስለነበረው ሩትን ለማግባት አልፈለገም። ስለዚህ ጉዳዩ አለቀ። ቦኤዝ ሩትን አገባት።

ሩትም ወንድ ልጅ በወለደች ጊዜ በቤተልሄም ከተማ እንደ ኑኃሚን የተደሰተ ሰው አልነበረም።

# የሐና ሕፃን



1ኛ ሳሙኤል 1 – 6

በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ባሉት ኮረብታዎች በአርማቴም መንደር ሕልቃና የሚባል አንድ ሰው ነበረ፡ እርሱም ሁለት ሚስቶች ነበሩት። አንዲቷ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆች የነበሩአት ፍናና የምትባል ስትሆን፣ ሌላዋ ደግሞ ምንም ልጅ ያልነበራት ሐና የምትባል ነበረች።

ሐና ምንም እንኳን ባልዋ በጣም የሚወዳት ቢሆንም በዚህ ምክንያት በጣም ታዝን ነበር።

ሕልቃናም እግዚአብሔርን ለማምለክ በየመቱ ቤተሰቡን ይዞ ወደ ሴሎ ይሄድ ነበር። በኋላም በእግዚአብሔር ቤት በደስታ በአንድነት ምግብ ይበሉ ነበር። በልጆች የተከበበችውም ፍናና ብቸኛ የነበረችውን ሐናን ታፌዝባትና ሐዘኗን ታባብስባት ነበር።

ምግቡንም ከበሉ በኋላ ሐና ከሌሎቹ ተለይታ ሄደች። ችግርዋን ሁሉ በመናገር ልቧን በእግዚአብሔር ፊት አፈሰሰች። እንዲህም አለች:–

"ወንድ ልጅን ብትሰጠኝ ዕድሜውን በሙሉ የአንተ አገልጋይ እንደሚሆን ቃል እገባለሁ።"

እግዚአብሔርም ሁልጊዜ ጸሎትን እንደ ሚሰማ እርስዋንም ሰማት። ካህኑ ኤሊ ግን ሲመለከታት የሰከረች መሰለው። እርሷም:–
"እባክህን በክፉ ዓይን አትመል ከተኝ፣ እኔ አልሰከርሁም፡ ግን በጣም ያዘንሁ ሰው ነኝ" አለችው፡ ሁሉንም ነገር ነገረችው።





ኤሊም "በሰላም ሂጂ፣ እግዚአብሔርም የተመኘሽውን ልጅ ይስጥሽ" አላት። ስለዚህ ሐና እንባዋን ጠርጋና ተጽናንታ ወደ ቤቷ ሄደች።

እግዚአብሔርም ፀሎትዋን መለሰ፤ ቆንጆ የሆነ ወንድ ልጅንም ሰጣት፤ ስሙንም ሳሙኤል አለችው፤ እርስዋም እንዲህ አለች፡- "ለአቅመአዳም ሲደርስ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ወደ ሴሎ እወስደዋለሁ፤ በገባሁት ቃል መሠረት ዕድሜውን በሙሉ በዚያ ይሆናል።" እንደተናገረችውም አደረገች፤ ለካህኑ ለኤሊም እንዲህ አለችው፡- "የፀለይሁበት ልጅ ይኸው፤ እርሱን እግዚአብሔር ነው የሰጠኝ፤ አሁንም እኔ መልሼ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ፤ አንተም እባክህ ጠብቀውና ለእግዚአብሔር ሥራ አሠልጥነው።"

ከጥቂት ቀናትም በኋላ ቤተሰቡ ሳሙኤልን ትተው ወደ ቤታቸው ወደ አርማቴም ተመለሱ፤ ሐና ከሕፃን ልጇ መለየቷ ምን ያህል ከባድ እንደሚሆንባት እግዚአብሔር አወቀ፤ ስለሆነም ከጊዜ በኋላ በፍቅር የምትንከባከባቸው ሦስት ወንዶች ልጆችና ሁለት ሴቶች ልጆችን ሰጣት። በዓመት አንድ ጊዜ ሴሎ ሲሄዱ ሐና ሳሙኤልን አየችው፤ የሠፋችለትንም አዲስ ልብስ ወሰደችለት። እርሱም ጥሩ ልጅ እየሆነ ስለሄደ ሁሉም ሰው ይወደው ነበር።



ኤሊ አሁን ሸመገለ። ብዙ ሳይቆይ የእርሱ ልጆች የእግዚአብሔር ቤት ኃላፊዎች ይሆናሉ፤ ዳሩ ግን የኤሊ ልጆች እንደ አባታቸው አልነበሩም፤ እግዚአብሔርን የማይወዱና የማያከብሩ ራስ ወዳዶች ነበሩ፤ እግዚአብሔርም ለኤሊ እንደዚህ ያሉ ሰዎች እርሱን በክህነት ሊያገለግሉ እንደማይችሉ አስጠነቀቀው፤ እንዲህም አለው፡-

"ፈቃዴን የሚያደርግና ለእኔ ታማኝ የሚሆን ካህን እኔ እመርጣለሁ" አንድ ሌሊት ሳሙኤል በእግዚአብሔር ቤት ተኝቶ ነበር። ከእንቅልፉ ብንን አለና ነቃ፤ አንድ ሰው ይጠራው ነበር! ሳሙኤልም ወደ ኤሊ ሮጠ፤ዳሩ ግን ሽማግሌው ካህን አልጠራውም ነበር፤ እንደገናም ተጠራ፤ እርሱም "ጠርተኸኛል፤ ይኸው መጣሁ" አለ። ግን ኤሊ አልጠራውም። በኋላም ሽማግሌው ካህን ሳሙኤልን የጠራው እግዚአብሔር እንደሆነ አወቀ። ስለዚህ ለሦስተኛ ጊዜ ድምፁ "ሳሙኤል! ሳሙኤል!"ብሎ ሲጣራ ልጁ ኤሊ እንደነገረው መለሰ። "ባሪያህ ይሰማልና ተናገር" አለ።

እግዚአብሔርም፣ "የኤሊን ልጆች እቀጣቸዋለሁ፤ ከእርሱ ቤተሰብ ወደፊት ማንም ለእኔ ካህን አይሆንም" አለው፤

በማግስቱ ጧት እግዚአብሔር ምን እንዳለው ኤሊ ሲጠይቀው ሳሙኤል ሊነግረው አልፈለገም፤ ሽማግሌው ግን እንዲነግረው አስገደደው።እያዘነም ልጁ የሚነግረውን አዳመጠ። እርሱም፣ "እግዚአብሔር መልካም የመሰለውን ያድርግ" አለ።



ከጥቂት ቀናት በኋላ የእስራኤል ሕዝብ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ተዋጉ፤ እስራኤላውያን በመሸነፍ ላይ ስለነበሩ የእግዚአብሔር ትእዛዛት ያሉበትን ታቦት ለማስመጣት ወደሴሎ መልእክት ላኩ፤ በጦርነቱ መልካም ዕድልን ያስገኝልናል ብለው አሰቡ! የኤሊም ልጆች ወደጦር ሠፈሩ አመጡት።

ዳሩ ግን ምንም አልጠቀማቸውም፤ ፍልስጥኤማውያን ታላቅ ድልን አገኙ። ታቦቱን ማርከው የኤሊንም ሁለት ልጆች ገደሉ።

ኤሊ በአሁኑ ጊዜ በጣም አርጅቶ ዓይኖቹም ደክመው ነበር። ይህን አሳዛኝ ወሬ በሰማ ጊዜ ወደቀና አንገቱ ተሰበረ።

ፍልስጥኤማውያን በድል አድራጊነት ወደ ከተማቸው ወደ አዛጦን ተመለሱ፤ የእግዚአብሔርንም ታቦት በአምላካቸው በዳጎን ቤተ መቅደስ በምርኮ ስም አስቀመጡት።

በማግሥቱም የዳጎን ሐውልት በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በግምባሩ ተደፍቶ ነበር። እንደገና መልሰው በቦታው አስቀመጡት፤ ሆኖም በማግስቱ ጧት እንደገና ተደፍቶ እንዲያውም ተሰባብሮ ነበር።




ከዚያም በኋላ በከተማቸው ውስጥ መቅሰፍት ወርዶ ሕዝቡ እጅግ ፈርተው ነበር፤ እነርሱም፣ "ይህ የእስራኤል አምላክ ሥራ ነው፤ ታቦቱን ማስወገድ አለብን" አሉ። ስለዚህ ወደ ጋዛ ላኩት፤ ከጋዛም ወደ አስቀሎና ላኩት። በነዚያም መቅሰፍቱ ወረደባቸው። ፍልስጥኤማውያንም የሚያደርጉትን አጥተው ተጨነቁ። ካህናቶቻቸውንና አስማተኞቻቸውንም አማከሩ።

እነዚያም አዋቂዎች፣ "ታቦቱን ከስጦታ ጋር መልሳችሁ ወደ እስራኤል ላኩ፤ ከዚያም ትድናላችሁ፤ በግብፃውያን ላይ እግዚአብሔር ያደረገውን አታስታውሱምን?" አሏቸው።

ስለዚህ ታቦቱን በሠረገላ ላይ አስቀምጠው ሠረገላውን ሁለት ላሞች እንዲጎትቱት ጠመዱአቸው ፡፡ የሚሆነውንም ለማየት ይጠባበቁ ነበር። ላሞቹ እንደ ሠለጠኑ ጥንድ በሬዎች ሆኑ፤ ቀጥ ብለው ወሰኑን ተሻግረው በእስራኤል ወዳለችው ወደ ቤትሳሚስ ሄዱ። የመንደሩም ሕዝብ የእግዚአብሔር ታቦት ሲመለስ አይተው እንዴት ተደሰቱ!

ከዚያም በኋላ ፍልስጥኤማውያን የእስራኤል አምላክ ክብር የሚገባው እንደሆነ አወቁ።



# ንጉሥ አንጋሹ ሳሙኤል

1ኛ ሳሙኤል 8 – 10፣ 15 – 16

ኤሊ ሞተ:: እግዚአብሔርም ካህን እንዲሆንለትና ለእስራኤል ሕዝብ መንገዱን እንዲያስተምርለት ሳሙኤልን መርጦ ነበር:: ሳሙኤልም እግዚአብሔርን ይወድና ይታዘዝም ነበር::

ዳሩ ግን የሳሙኤል ልጆች ከኤሊ ልጆች የተሻሉ አልነበሩም:: ባለጌዎችና ስስታሞች ነበሩ:: ስለዚህ ሕዝቡ ወደ ሳሙኤል መጡ፤ እንዲህም አሉ፣ "አንተ ሸምግለሃል፤ ልጆችህም እኛን እንዲመሩን አንፈልግም፤ ስለዚህ እንደ ሌሎች ሕዝቦች ንጉሥ አንግሥልን::"

ሳሙኤል በዚህ ሃሳብ ፈጽሞ አልተደሰተም:: እግዚአብሔርም አልተደሰተም! እውነተኛው የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር ራሱ ነበር፡ ከግብፅ ምድር ያወጣቸውና ሕጉንም የሰጣቸው እርሱ ነበር:: አሁን ደግሞ እርሱን **መናቃቸው ነው::**

ሳሙኤልም እንዲህ አላቸው:–"እንደ ሌሎች ሕዝብ ንጉሥ ፈልጋችኋል፤ ዳሩ ግን ንጉሣችሁ እንዲህ ያደርግባችኋል፤ ልጆቻችሁን ወታደር ያደርጋል፤ እናንተም የእርሱ ገበሬ ዎችና የጦር መሣሪያ ሠሪዎች ትሆናላችሁ፤ ከእናንተም ምርጥ የሆኑትን ከብቶችና እህል እንዲሁም መሬታችሁን ይወስዳል፤ እናንተም ባሪያዎቹ ትሆናላችሁ:: ነገሥታት እንደዚህ ናቸው:: ንጉሥም በመፈለጋችሁ ትፀፀታላችሁ::"

ሕዝቡ ግን አይሆንም አሉ፤ ንጉሥ እንዲገዛቸውና በጦርነት እንዲመራቸው ፈለጉ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር "የፈለጉትን አድርግላቸው፤ ንጉሥን ስጣቸው" አለው:: የእስራኤልም የመጀመሪያ ንጉሥ ሳኦል የሚባል ያማረ፣ ቁመተ ረጅምና መልከ መልካም ሰው ነበረ:: ሳሙኤል መጀመሪያ ሲያገኘው የጠፉትን የአባቱን አህዮች እየፈለገ ነበር፤ እግዚአብሔርም ለሳሙኤል "ሕዝቤን የሚገዛው ይህ ነው" አለው፤ ሳሙኤልም በዚያን ዘመን እንደ ነበረው ልማድ አደረገ፤እርሱም እግዚአብሔር ሳኦልን እንደመረጠውና ለንጉሥነት የሚያስፈልገውን ሁሉ እንደሰጠው





ለማሳየት የወይራ ዘይት የሞላበትን ማሰሮ ወስዶ በሳኦል ራስ ላይ አፈሰሰው፤ ለመጀመሪያ ሳኦል መልካም ንጉሥ ነበር፤ ኀበዝም ነበር፤ ሕዝቡንም በጦር ሜዳ እየመራ ድል ያደርግ ነበር፤ በጣምም የተወደደ ነበር፤ ኋላ ግን ኩራተ ኛና ግትር እየሆነ መጣ፤ ሳሙኤልንም አይሰማም ነበር፤ ለእግዚአብሔርም አልታዘዝ አለ፤ አንድ ቀን እግዚአብ ሔር ለሳሙኤል እንዲህ አለው:–

ሳኦል ከእንግዲህ ንጉሥ አይሆንም፤ የእርሱን ምትክ መርጫለሁ፤ ወደ ቤተልሄም ሂድና አዲሱን ንጉሥ ቀባው፤ እርሱም ከእሴይ ልጆች አንዱ ነው፤ ዳሩ ግን ይህን በምስጢር ያዘው::" ሳሙኤልም ለሳኦል በጣም አዘነ፤ ግን ሳኦል እንደማይሻሻል አወቀ፤ ስለዚህ ወደ ቤተልሄም ሄደ፤ እርሱም ለእግዚአብሔር ልዩ መስዋዕት ለማቅረብ እንደመጣ ተናገረ፤ እሴይንና ልጆቹንም ወደግብዣው ጠራ፤

እሴይም ረጃጅም ጠንካሮችና መልከ መልካም የሆኑትን ሰባት ልጆቹን ይዞ መጣ፤ ሳሙኤልም እያንዳንዳቸውን በየተራ ባነጋገራቸው ጊዜ "በእውነት እግዚአብሔር የመረጠው ይህኛው ነው" በማለት አሰበ፤ ዳሩግን እግዚአብሔር ሁሉንም "አይደለም! " አለ::


"መልኩን አትይ፣ እኔ የማየው ውስጡን ነው፣ መልካም፣ ፍቅር ያለውና ርህሩህ መሆኑን ነው የማየው" አለው። ሳሙኤልም እሴይን "ሌሎች ልጆች አሉህን?" ሲል ጠየቀው፤

እሴይም፣ "አዎን የመጨረሻው ልጅ አለ ግን በዱር በጎች እየጠበቀ ነው" አለው፤

ሳሙኤልም "እንዲመጣ ንገረው፤ እርሱ ካልመጣ ግብዣውን አንጀምርም" አለው፤ ስለዚህ እሴይ ዳዊትን ልኮ አስመጣው፤

ዳዊትም ፀመጣ ጊዜ እግዚአብሔር ለሳሙኤል "ይህኛው ነው" አለው፤ ሳሙኤልም ይዞት የመጣውን የወይራ ዘይት ወስዶ በዳዊት ራስ ላይ አፈሰሰው፤ ከግብዣውም በኋላ ሳሙኤል ወደ ቤቱ ሄደ።

ዳዊትም በቤተልሄም ኮረብቶች አካባቢ የአባቱን በጎች መጠበቁን ቀጠለ፣ ዳሩ ግን ከዚያ ቀን ጀምሮ እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ ከዳዊት ጋር ነበረ።





# እረኛው ልጅና ግዙፉ

1ኛ ሳሙኤል 16 – 17

ዳዊት ቀኑን ሙሉ በኮረብቶቹ ላይ የአባቱን በጎች ይጠብቅ ነበር፤ አንዳንድ ጊዜ ከመንጋው መካከል አንድ በግ ይጠፋና ዳዊት ፈልጎ ያመጣው ነበር፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የተራበ ተኩላ፣ ድብ ወይም አንበሳ ከመንጋው አንዱን ሊወስድ ይመጣ ነበር፤ በዚህ ጊዜ ዳዊት አውሬውን ለማባረርና በጎቹን ለማዳን በነበረው ኃይልና ጥበብ ሁሉ ይጠቀም ነበር።

አብዛኛውን ጊዜ ግን በጎቹን ብዙ ለምለም ሣር ወደ ሚገኝበት መስክ ከመውሰድና ከማስማራት በስተቀር ብዙ የሚያደርገው ነገር አልነበረም።

ሆኖም ዳዊት አይሰለችም ነበር፤ በወንጭፍ ድንጋይ ውርወራ አነጣጣሪ ለመሆን ይለማመድ ነበር፤ ደግሞም ራሱ የደረሳቸውን መዝሙሮች በመዘመር በገና ይጫወት ነበር፤ በሙዚቀኛነት ስሙ የታወቀ መሆን ጀመረ፤! ሰዎችም ቆመው ያዳምጡት ነበር፤ የዚህ ልጅ አጨዋወት የተለየ ነበር።



በዚህ መካከል ላይ በቤተ መንግሥት አንድ ችግር ነበር፣ ንጉሥ ሳኦል ደስተኛ አልነበረም፣ ሳሙኤልም ወደ እርሱ ሳይሄድ ብዙ ቆየ፣ እግዚአብሔርም ራቀው፣ ሁሉም ነገር የተበላሸ ሆነ፣ የሳኦል ስሜት ይበልጥ እየጨለመ መጣ፣ አንድ ነገር መደረግ ነበረበት፣ ከአሽከሮቹ አንዱ "ንጉሡ የሚያስፈልገው ሙዚቃ ነው፣ ሙዚቃ ያረጋጋውና ችግሩን እንዲረሳ ያደርገዋል" አለ።

ሌላውም፣ "ለዚህ የሚስማማውን ሰው አውቃለሁ" አለ፣ እንግዲህ ዳዊት ቤተ መንግሥት የመጣው በዚህ ምክንያት ነው፣ የእርሱ ሙዚቃ ከማንኛውም መድኃኒት የተሻለ ሆነ፣ የሳኦል የተረበሸ አእምሮ እረፍት አገኘ፣ ወዲያውም ተሻለውና ዳዊትም ወደ ቤቱ ተመለሰ።

ከዚያም የእስራኤላውያን የቀድሞ ጠላቶች የሆኑት ፍልስጥኤማውያን ወደ ሰሜን እየመጡ ናቸው የሚል ወሬ መጣ፣ እነርሱም በዔላ ሸለቆ ሰፈሩ፣ ከሸለቆው በአንደኛው በኩል የፍልስጥኤማውያን ሠራዊት በሌላው በኩል ደግሞ የእስራኤላውያን ሠራዊት ሠፍረው ነበር፣ በመካከልም ትንሽ ወንዝ ነበረች፣ ፍልስጥኤማውያን ድብቅ መሣሪያ ነበራቸው! ስሙም ጎልያድ የተባለ ቁመቱ አሥር ጫማ የሚሆን ግዙፍ ሰው ነበረ፣ የጦሩም እጀታ የሰው ክንድ ያህል ውፍረት ነበረው፣ በየቀኑ ጎልያድ እየጮኸና እየፎከረ በትምክህት ወዲያና ወዲህ ይንጎራደድ ነበር።

"ከእስራኤል ዋንኛው ጎበዝ የት አለ? ጎበዝ ከሆነ ይምጣና ይግጠመኝ" ይል ነበር። ግን ማንም አልሞከረ ውም፣ ሁሉም በጣም ፈርተውት ነበር፣ ከዳዊት ወንድሞች ሦስቱ በሳኦል ሠራዊት ውስጥ ወታደሮች ነበሩ፣ ዳዊትም ምግብ እንዲወስድላቸውና ደህንነታቸውን እንዲጠይቅ ይላክ ነበር፣



አንድ ቀን ልክ ጎልያድ በሚፎክርበት ጊዜ ደረሰ፣ ዳዊትም "የሕያው እግዚአብሔርን ሠራዊት የሚገዳደር ይህ ሰው ማን ነው እኔ ሄጄ እዋጋዋለሁ" አለ። ወታደሮቹም ሳቁበት፣ ሳኦል ግን ይህን በሰማ ጊዜ ዳዊትን ላከበት፣ እርሱም "አንተ ገና ልጅ ነህ፣ ከዚህ ታላቅ ጦረኛ ጋር ምን ዕድል ፈንታ አለህ" አለው።

ዳዊትም መልሶ "በጎቼን ሊያጠቃ የመጣውን አንበሳና ድብ መትቼአለሁ፣ እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ ከእኔ ጋር እንደነበረ አሁንም ከእኔ ጋር ይሆናል" አለ። ንጉሡም መልሶ "መልካም፣ ሂድ እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር ይሁን" አለው። ለዳዊትም የራሱን ሰይፍ ሰጥቶ የራሱን ጥሩር አለበሰው፣ ዳዊት ግን ይህን ለብሶ መራመድ እንኳን አቃተው፣! እርሱም፣ "ይህን ለብሼ መዋጋት አልችልም" አለ፣ አውልቆም አስቀመጠው፣ የራሱን የእረኛ በትርና ወንጭፉን ብቻ ያዘ፣ ከሸለቆውም አምስት ለስላሳ ድንጋዮችን ወስዶ በቦርሳው ውስጥ አስቀመጠ፣ ከዚያም ጎልያድን ሊዋጋ ሄደ፣ ወደ እርሱም ሲመጣ ባየው ጊዜ ጎልያድ ጎኑ እስኪሰነጠቅ ድረስ ሳቀበት። እየፎከረም ለእስራኤላውያን "የእናንተ ጎበዝ ይኸ ነውን?" አላቸው።







ዳዊት ግን "ዛሬ አንተን እግዚአብሔር በእጄ አሳልፎ ይሰጥሃል፤ ከዚያም ሰው ሁሉ በእስራኤል አምላክ እንዳለ ያውቃል" አለው:: ከቦርሳውም አንድ ድንጋይ ወስዶ በወንጭፉ ውስጥ አስቀመጠ፤ ድንጋይዋም እንደ ሮኬት በረረች፤ ጎልያድንም የራስ ቅሉ እስኪበሳ ድረስ ግንባሩን በኃይል መታችው፤

ዳዊትም ወደ እርሱ ሮጦ የጎልያድን ሰይፍ መዝዞ እራሱን ቆረጠው፤ በዚህ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን በታላቅ ድምፅ ከጮኹ በኋላ ተመልሰው ሸሹ:: እስራኤላውያንም በሙሉ ኃይል ተከተሉአቸው፤ ጦርነቱም በድል ተጠናቀቀ::

# ዳዊትና የንጉሡ ወንድ ልጅ



1ኛ ሳሙኤል 18 – 31

ዳዊት በጎልያድ ላይ ያገኘው ድል ዝነኛ አደረገው:: ሳኦልም በቤተ መንግሥት እንዲቀመጥ ወሰደው::

ንጉሡም፣ "ልጄን ያገባል" አለ፤ የሳኦል ልጅ ዮናታን ደግሞ ዳዊትን በጣም ወደደው፤ ወዳጅነታቸው የፀና ሆነ፤ ከዚያም እስከ መጨረሻው ጓደኞች እንዲሆኑና በምንም ዓይነት እንዳይከዳዱ ተማማሉ፤

ዳዊትም ከጦር ሠራዊቱ ተቀላቀለና ዝነኛ ወታደር ሆነ:: በጣም የተወደደም ነበር:: ሰዎቹ እርሱን በማሞገስ ይዘፍኑ ስለነበር ሳኦል ቀናበት፤ ዳዊት የሳኦልን ልጅ ሜሮብን አጭቶ ነበር፤ ንጉሡ ግን የሠርጉን ቀን አስተላለፈው::

ከዕለታት አንድ ቀን ዳዊት በገና በመጫወት ላይ ሳለ ሳኦል ጦር ወረወረበት፤ ይህም ገና የችግሩ መጀመሪያ ነበር::

ሳኦል ለዳዊት የገባውን ቃል አፍርሶ ሜሮብን ለሌላ ሰው አጋባት፤ ታናሽ ልጁ ሜልኮል ግን ዳዊትን እንደ ወደደችው በሰማ ጊዜ ዳዊትን ለመግደል መልካም አጋጣሚ ያገኘ መሰለው፤



እርሱም "ለጋብቻው ስጦታ አያስፈልግም፤ የምፈልገው
የሁለት መቶ ፍልስጥኤማውያን ሬሳ ብቻ ነው" አለ።
ይህም በተንኮል የታቀደ ነበር፤ ምክንያቱም ፍልስጥኤማ
ውያን ዳዊትን እንደሚገድሉት ሳኦል እርግጠኛ ስለነበረ
ነው። ዳሩ ግን ዳዊት የንጉሡን ትእዛዝ ፈጸመና ሜልኮ
ልን አገባት።

ዮናታን ግን ይኽ ሁሉ ሤራ አስጠላው፤ እርሱም
ለዳዊት ሳኦል ሊገድለው እንደሚፈልገው ካስጠነቀቀው
በኋላ ንጉሡ ሀሳቡን እንዲለውጥ ስለ ዳዊት ለመነው፤
ሳኦልም ተስማምቶ ነበር፤ ዳሩግን እንደገና ቃሉን ለወጠ።

አንድ ምሽት ዳዊት በገናውን በመጫወት ላይ እያለ
የሳኦል ጦር በጆሮው አጠገብ አልፋ በግድግዳው ላይ ተሰ
ካች፤ በዚህ ዓይነት በቤተ መንግሥት መኖር ለሕይወቱ
አስጊ ሆነ።

አንድ ሌሊት ሜልኮል ዘበኞቹ ሳያዩ ዳዊትን በቤታ
ቸው መስኮት በገመድ አውርዳ እንዲያመልጥ ረዳችው።
ዮናታንና ዳዊትም በሀዘን ተለያዩ፤ ዳግመኛ መገናኘት
አልተቻላቸውም፤

ከዚያ ወዲያ ዳዊት ሸፍቶ በኮረብቶች ውስጥ ይኖር
ጀመር፤ ሰዎችንም አሰባስቦ ምግባቸውን እየፈለጉ ከቦታ
ወደ ቦታ ይዘዋወሩ ነበር፤ ሕይወታቸው ከአደጋ የራቀ
አልነበረም፤ አንዳንድ ጊዜ የሳኦል ሰዎች እየመጡባቸው
ለማምለጥ የተቸገሩበት ጊዜ ነበር። ዳሩ ግን እግዚአ
ብሔር ከዳዊት ጋር በመሆን የሚነግሥበት ጊዜ እስኪ
ደርስ ድረስ ይጠብቀው ነበር።





አንድ ጊዜ ሳኦል ብቻውን መሣሪያም ሳይይዝ ዳዊትና
ተከታዮቹ በተደበቁበት ዋሻ በር አጠገብ መጣ፤ ዳዊት
በቀላሉ ሊገድለው ይችል ነበር፤ ዳዊት ግን ሊጎዳው
አልፈለገም።

በተለያየ ጊዜ ሰዎች ለንጉሡ ዳዊት የተደበቀበትን
ሥፍራ እየነገሩት እርሱም ዳዊትን ፍለጋ ይመጣ ነበር፡
አንድ ጊዜ ከሠራዊቱ ጋር በዚፍ ምድረ በዳ ሰፈረ፤
በሌሊትም ዳዊትና ሁለት ተከታዮቹ የሳኦልን ጠባቂ
በቀስታ አልፈው ሳኦል ወደ ተኛበት ቦታ ደረሱ፤ ጦሩም
በአጠገቡ በመሬት ላይ ተሰክቶ ነበር፤ የዳዊትም ሰዎች
"ግደለውና ከችግርህ ተገላገል፤ እግዚአብሔር በእጅህ
ሰጥቶሃል" ብለው ሹክ አሉት።

ዳዊት ግን "እግዚአብሔር ንጉሥ አድርጎ የቀባውን ፈጽሞ
አልገድልም፤ እግዚአብሔር በፈለገ ጊዜ ይሙት" አለ።
የሳኦልንም ጦርና ውሀ መጠጫውን ይዘው ከሠፈሩ ሲሄዱ
ማንም አላያቸውም፤ ርቀው ከሄዱ በኋላ ዳዊት ሠፈሩ
ሁሉ በድንጋጤ እስኪነቃ ድረስ በታላቅ ድምፅ ጮኸ።
እንዴት ጎበዝ ጠባቂዎች ናችሁ! ንጉሡን በደምብ አትጠ
ብቁምን? ተመልከቱ፣ የእርሱ ጦር ይኸው!"አላቸው።



ሳኦልም የዳዊት ድምፅ መሆኑን አወቀ፡ ዳዊትም ሕይወቱን አተረፈው፡ ሳኦል ዳዊትን እንደዚህ በማስቸገሩ በጣም አፈረ፤ ስለዚህ ለጊዜው ተወት አደረገው፡ ዳሩ ግን አልቆየም፡፡

አሁን ዳዊት በእስራኤል አገር የትም ቢሆን በሰላም ሊኖር አልቻለም፤ ስለዚህ ጺቅላግ በምትባል በፍልስጥ ኤማውያን ከተማ ስደተኛ ሆነ፡፡ የፍልስጥኤማውያን ወገን እንደሆነም ለማስመሰል ሞከረ፡፡ እንዲያውም ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤል ጋር ለመዋጋት ወደ ሰሜን ሲጓዙ አብሮ ሄደ፤ እነርሱም በሱነም ከሰፈሩ በኋላ



በጣም አስከፊ ጦርነት በጊልቦዓ ተራራ ተካሄደ፡፡ በዚያም ቀን ዮናታን ከሌሎቹ የሳኦል ልጆች ጋር ሞተ፡ ንጉሡም በመጥፎ ሁኔታ ስለቆሰለ ከነሕይወቱ በጠላት ከመማረክ ብሎ በገዛ ራሱ ሰይፍ ላይ ወድቆ ሞተ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ፍልስጥኤማውያን አገኙትና ራሱን ቆረጡት፤ ሬሳውንም በቤትሳን አጥር ላይ አንጠለጠሉት፤ ዳሩ ግን ኀበዞች ሰዎች መጥተው ከዚያ አወረዱትና በሥነ ሥርዓት ቀበሩት፡፡

ሀገሩ በሞላ ሀዘን አደረገ፤ ዳዊትም ወሬውን በሰማ ጊዜ በሀዘን ተሞላ፤ ድምፁንም ከፍ አድርጎ በሀዘን፡-

"ሳኦልና ዮናታን የተወደዱና የተስማሙ
በሕይወታቸውና በሞታቸው አልተለያዩም፤
ኃያላን በጦር ሜዳ እንዴት ወደቁ" አለ፡፡

ዳዊትም የመጨረሻ መራራ ለቅሶ አለቀሰ፡፡



# ንጉሥ ዳዊት ሺህ ዓመት ይንገሥ!

2ኛ ሳሙኤል

ጥሩምባ ተነፋ፡ ሕዝቡም በታላቅ ድምፅ ጮኹ፡ "ዳዊት በእስራኤል ላይ ንጉሥ ይሁን፡ ንጉሥ ዳዊት ሺህ ዓመት ይንገሥ!" አሉ፡፡

የሽፍትነት ጊዜ አለፈ፡ ዳሩ ግን የዳዊት ችግር አላ ለቀም የቀድሞው ንጉሥ የሳኦል ተከታዮች ከእርሱ ጋር ተዋጉ፡ ፍልስጥኤማውያንና ሌሎችም የቀድሞ ጠላቶች ተመልሰው ሊመጡ ይጠብቁ ነበር፡ ከዚህም በላይ በመን ግሥቱ ግዛት መካከል ያለችው ኢየሩሳሌም በከነአናውያን ነገድ ተይዛ ነበር፡፡ ዳዊት የኢየሩሳሌምን ምሽግ ከብቦ የያዘበትና ዋና ከተማው ያደረገበት ቀን ታላቅ ታሪካዊ ዕለት ነበር፤

በመጨረሻ ሰላም ሆነ፡ አሁን ዳዊት ለረጅም ጊዜ ሲመኘው የነበረውን ሊያደርግ ነው፡ የእግዚአብሔር ሕግ ያለበትን ቅዱሱን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም እንዲያመጡት ትእዛዝ ሰጠ፡፡

ይህ ዕለት ምን ዓይነት የዝማሬ፣ የጭፈራና የድግሥ ዕለት ይሆን! ንጉሥ ዳዊት በጣም ከመደሰቱ የተነሣ ከሌ ሎቹ የበለጠ ይጨፍር ነበር፤ አሁን ኢየሩሳሌም የእርሱ ዋና ከተማ ብቻ አልነበረችም፡ የእግዚአብሔርም ከተማ ነበረች፡፡ ዳዊት ጥሩ ንጉሥ ነበር፡ ኀበዝ ወታደር ከመሆ ኑም በላይ የአገር መሪነት ብቃትና የተፈጥሮ ስጦታም ያለው ሰው ነበር፡ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆችም ነበ



ሩት። ሕዝቡ ሁሉ ይወደው ነበር። እንደ ንጉሥ ሳኦል ትእቢተኛና ታዛዥነት የጎደለው አልነበረም፤ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነ፤ ቢሆንም ግን ነገሮች የተበላሹበት ጊዜ ነበር።

## የድሀው ሰው በግ

ከዕለታት አንድ ቀን በፀደይ ወራት ከቀትር በኋላ ሠራዊቱ ከአሞናውያን ጋር ለውጊያ በሄዱበት ጊዜ ንጉሥ ዳዊት ንፋስ ለመቀበል ወደ ቤተ መንግሥቱ ሰገነት ላይ ወጣ፤ ወደ ታችም ሲመለከት እጅግ በጣም የተዋበች ቆንጆ ሴት አየ፤ እርሱም "ያች ማን ነች" ብሎ ጠየቀ፤ "የኦርዮ ሚስት ቤርሳቤህ ናት" የሚል መልስ አገኘ።

ኦርዮም የዳዊት ጎበዝ ወታደር ሲሆን የንጉሡን ጦር ነት ሊዋጋ ሄዶ ነበር፤ ዳዊት ግን ይህንን ሁሉ አላሰበም፤ አሽከሮቹም ቤርሳቤህን ወደ ቤተ መንግሥት እንዲያመጡአት አዘዘና ከእርስዋ ጋር ተኛ።







ከጥቂት ሳምንታትም በኋላ ቤርሳቤህ ለንጉሡ አርግዣለሁ ብላ ላከች። የዳዊት ልጅ መሆኑ ነው። ባልዋ ኦርዮ ይህንን ቢሰማ ምን ይሆናል? ዳዊት በአስቸኳይ አንድ ነገር ማድረግ ነበረበት፤ ለጦር አዛዡም እንዲህ ሲል መልእክት ላከ፦

"ኦርዮን ወደጦሩ ግንባር ውሰደውና እንዲሞት አድርግ" አለ፤ ይህ ሁሉ የሆነው በምስጢር ነበር፤ ዳዊት ማንንም አላወቀም ብሎ አሰበ። ዳሩ ግን እግዚአብሔርን መርሳቱ ነበር። ኦርዮም ሞተ፤ ዳዊትም ቤርሳቤህን አገባት። ወንድ ልጅም ተወለደ፤ ዳዊት ምስጢሩ አይታወቅም ብሎ አሰበ፤ ከዕለታት አንድ ቀን ናታን የሚባል የእግዚአብሔር መልእክተኛ ለንጉሡ አንድ ታሪክ ሊነግር መጣ። እንዲህም አለ፦ "አንድ ጊዜ ሁለት ሰዎች ነበሩ፤ አንዱ ባለጠጋ፣ አንዱ ደግሞ ድሀ ነበር። ባለጠጋው ብዙ በጎችና ከብቶች ነበሩት። ድሀው ግን አንዲት በግ ብቻ ነበረችው። እርስዋም እንደ ቤተሰቡ ነበረች ባለጠጋው ሰው እንግዳ መጣበትና በግ ሊያርድለት ፈለገ፤ ዳሩ ግን ከራሱ በጎች መንጋ አንዱን በማረድ ፈንታ የድሀውን አንዲት በግ ወስዶ አረደና ለእንግዳው አቀረበለት።

ታሪኩም ዳዊትን በኃይል አስቆጣው፤ ሰው እንዴት እንደዚህ ጨካኝ ይሆናል? አለ። ከዚያም በኋላ ዝምታ ሆነ፤ በመቀጠልም ናታን እንደገና እንደ ጦር የሚዋጋ ቃል ተናገረ፤ እንዲህም አለ፦

"ያ ሰው አንተ ነህ፡ እግዚአብሔር ንጉሥ አድርጎህ የተመኘኸውን ሁሉ ሰጠህ፡ ዳሩ ግን የኦርዮንን ሚስት ወስደህ እርሱንም ለሞት ዳረግኸው፡ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ አይቶአል፤ ንጉሥ ስለሆንክ እንዲህ ያለ ነገር ሠርተህ የምታመልጥ አይምስልህ፡ በአንተ ኃጢአት ምክንያት ሕፃኑ ልጅ ይሞታል።"

ዳዊት እጅግ ፈራ፡ ባደረገውም ስህተት በጣም አዘነ፡ ዳሩ ግን የሕፃኑን ሕይወት ሊያድን አልቻለም፡ ሕፃኑ ሞተ፡ ዳዊት ቤርሳቤህን አጽናናት፡ እግዚአብሔርም ሌላ ልጅ ሰጠው፡ ስሙንም ሰሎሞን አሉት፡

ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት ንጉሡ ብዙ ነገሮችን አደረገ፡ ብዙ ጦርነቶችን ተዋጋና መንግሥቱም ጠነከረ፡ ዳሩ ግን ከሁሉም በላይ ለእግዚአብሔር ቤት ለመሥራት ፈለገ፡ ይህ ግን አልሆነም። እግዚአብሔር "ይህ የሰሎሞን ሥራ ነው" አለው።

ስለዚህ የዳዊት ድርሻ ሰሎሞን ሥራውን እንዲጀምር ፕላኑን መንደፍ፡ ብዙ ወርቅ፣ ብር፣ ነሐስ፣ ብረት፣ እንጨትና ክቡር ድንጋዮች ማዘጋጀት ነበር፡ ስለዚህ የቤተ መቅደሱን አገልግሎት በተለይም ሙዚቃውን ለማዘጋጀት ለብዙ ሰዓቶች ይሠራ ነበር። ምክንያቱም ዳዊት ሙዚቃ የሚወድና ብዙ መዝሙሮችንም የጻፈ ነበር። አንዳንዶቹ የዳዊት መዝሙሮች በመጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ያሉት ናቸው።

## አመፅ

አዎን! ዳዊት በእርግጥ ታላቅ ንጉሥ ነበር፡ ዳሩ ግን በቤተሰቡ ውስጥ የነበረው ነገር ከዚህ የተለየ ነበር፡ የመንግሥቱ ጉዳይ ተከናወነለት፤ ግን የራሱን ልጆች መቆጣጠር አልቻለም። ለዚህ ድክመቱም ብዙ ዋጋ ከፍሎአል። ሰው ሁሉ የንጉሡን ወጣትና መልከ መልካም ልጅ አቤሴሎምን ይወድ ነበር። ለእርሱ ግን ተወዳጅ መሆን ብቻ አልበቃ ውም፡ አቤሴሎም ንጉሥ ለመሆን ፈለገ፡ በአባቱም ላይ አድማ አድርጎ በኬብሮን ስብሰባ በማድረግ ንጉሥነቱን አሳወጀ፡ ከዚያም ወደ ዋና ከተማዋ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ዳዊት ሕይወቱን ለማዳን መሸሽ ግድ ሆነበት። ከዚያም የእርስ በርስ ጦርነት ሆነ።



የዳዊት ብልህ አማካሪ የነበረው አኪጦፌልም ከአቤሴሎም ጋር ስለተባበረ ለዳዊት ነገሩ ሁሉ ጨለማ ሆነበት፡ እግዚአብሔር ግን አልረሳውም ነበር፡ ዳዊትን ይወደውና በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ይጠብቀው ነበር፡ አሁንም እየጠበቀው ነበር።

የዳዊት ታማኝ ወዳጅ የሆነው ኩሲ ከአቤሴሎም ወገን የሆነ በመምሰል የአቤሴሎምን እቅድና ፕላን ሁሉ በምስጢር ለንጉሡ ይልክ ነበር።

በአኪጦፌል ምክር መሠረት አቤሴሎም ዳዊትን ተከትሎ በድንገት በመያዝ ፈንታ ትንሽ እንዲቆይ ኩሲ አቤሴሎምን አግባባው፤ ይህም ዳዊት ወታደሮቹን ለማሰባሰብ እንዲችል ጊዜ ሰጠው።

ከባድ ጦርነት ከተደረገ በኋላ የዳዊት ሠራዊት አሸነፈ፤ አቤሴሎምም በተቻለው ፍጥነት ሸሸ፤ ዳሩ ግን የተቀመጠበት በቅሎ በዛፍ ሥር ሲያልፍ ራሱ በዛፉ ቅርንጫፍ ተያዘ፡ በዚያም የዳዊት ወታደሮች አገኙት፤ ሕይወቱም እንዲተርፍ ንጉሡ የሰጠውን ግልጽ ትእዛዝ በመተላለፍ ወታደሮቹ ገደሉት። ዳዊትም ወሬውን በሰማ ጊዜ መቋቋም አልቻለም፡ እያለቀሰም እንዲህ አለ፦

"ኦ ልጄ አቤሴሎም፤ ምነው እኔ በአንተ ፈንታ በሞትሁ፤ ኦ ልጄ አቤሴሎም!"





ስለዚህ ታላቁ የድል ቀን በሀዘን ተደመደመ፤

ዳዊትም ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ አመጻኞቹን ቀጣቸው፤ ለዙፋኑም ሌላ ተቀናቃኝ አልነበረም። ዳሩ ግን ከአቤሴሎም አመፅና ሞት በኋላ ንጉሡ እያረጀና እየደከመ መሄዱ ተሰማው፤ ሕዝቡም ከንጉሡ ልጆች ማንኛው የወደፊቱ የእስራኤል ንጉሥ እንደሚሆን ለማወቅ ይጠይቁት ጀመር።



# ጠቢቡ ሰሎሞን

1ኛ ነገሥት 3፤ 4፤ 10

ንጉሥ ዳዊት ሸምግሎና ደክሞ ነበር። በእርሱም ምትክ የሚነግሰውን ሰው ለመወሰን ችግር ነበር፤ አቤሴሎም ስለሞተ የዳዊት ተከታዩ ልጅ አዶንያስ ዙፋኑን ለመውረስ ጠየቀ።

ዳዊት ግን ሌላ እቅድ ነበረው፤ እርሱም ወደ ካህኑ ሳዶቅ፣ ወደ ነቢዩ ናታንና ወደ ዘበኞቹ አለቃ ወደ በናያስ መልእክት ላከ፤ እንዲህ ሲል፦

"እኔ ስሞት ሰሎሞን ንጉሥ ይሆናል፤ በእኔ በቅሎ ላይም ተቀምጦ ወደ ግዮን ምንጭ ይሄዳል፤ ሳዶቅና ናታንም ንጉሥ አድርገው ይቀቡታል፤ እናንተም ቀንደ መለከት እየነፋችሁ 'ንጉሥ ሰሎሞን ሺህ ዓመት ይንገሥ' ትላላችሁ።"

ስለዚህ ሳዶቅ፣ ናታን፣ በናያስና የንጉሡ ዘበኛ ዳዊት እንዳለው አደረጉ፤ ሰሎሞን ንጉሥ መሆኑ ታወጀ፤ ቀንደ መለከቱ ተነፋ፤ ሕዝቡም ሁሉ፣ "ንጉሥ ሰሎሞን ሺህ ዓመት ይንገሥ!" ብለው ጮኹ።

ከዚያም በኋላ ዋሽንት እየነፉና በደስታ እየጮኹ ወደ ከተማው አመጡት። ዳዊት ለሰሎሞን የመጨረሻ ትእዛዝ ሰጠው፤ እንዲህም አለው፣ "ኀበዝ ንጉሥ ሁን፤ እግዚአብ



ሔርን ተከተል፣ ትእዛዙንም ጠብቅ። ከዚያም ሁሉ ነገር ይከናወንልሃል፣ ለእርሱ ከታዘዝህ፣ ዘርህ ይህችን ምድር ለዘላለም ይገዛል ብሎ የገባልኝን ቃል ይፈጽማል።

ከዚያም ንጉሥ ዳዊት ሲሞት ንጉሡ ስሎሞን በንጉሥ ከተማ፣ በእግዚአብሔር ከተማ፣ በኢየሩሳሌም በንጉሥነት ይገዛ ጀመር። ስሎሞንም በእስራኤል አገር ሲገዛ ግዛቱ ጠንካራና አንድነት ያለው ሆነ። እንደ አባቱም እግዚአብሔርን ወደደ። አንድ ሌሊት እግዚአብሔር በሕልም ወደ ስሎሞን መጣ፣ እግዚአብሔርም "ምን እንድሰጥህ ትፈልጋለህ?" አለው።

ስሎሞንም መልሶ "እኔ ገና በጣም ወጣት ነኝ፣ ደግሞም ይህን ሁሉ ሕዝብ አስተዳድራለሁ፣ ስለዚህ በታማኝነት እንዳስተዳድርና መልካም የሆነውን ነገር እንዳደርግ እባክህ ጥበበኛ አድርገኝ" አለው።

እግዚአብሔርም ስሎሞን ከሀብትና ከዝና ይልቅ ጥበብን ስለፈለገ ደስ አለው፤ እንዲህም አለው "ከሰዎች ሁሉ ይልቅ ጥበበኛ አደርግሃለሁ፤ በተጨማሪም ሀብትና ዝናን እሰጥሃለሁ።"

እግዚአብሔርም በገባው ቃል መሠረት ስሎሞን ከሰው ሁሉ የሚበልጥ ጥበበኛ ሆነ፤ ከምሥራቅ ጥበበኞች ሁሉና፣ ከግብፅ አገር ጥበበኞች ሁሉ የበለጠ ሆነ።

ንጉሥ ስሎሞን 3,000 ምሳሌዎች ደረሰ! ጥቂቶቹ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በመጽሐፈ ምሳሌ የሚገኙት ናቸው።

ዳሩ ግን ጥበብ የሚገኘው ከእግዚአብሔር እንደሆነ ፈጽሞ አልረሳም፤ ይህም ዝም ብሎ ብልጥ መሆን ማለት አይደለም፤ ማንም ሰው እግዚአብሔርን ካላከበረና የሚለውን ካልሰማ እውነተኛ ጥበበኛ ሊሆን አይችልም።

## የሳባ ንግሥት

የስሎሞን ዝና በሩቅ ተስፋፋ፤ ነጋዴዎች የእርሱን የጥበብ ዝና ይዘው ከምድረ በዳው ባሻገር ወዳለው ወደ ሳባ ግዛት ሄዱ፤ የሳባም ንግሥት እነርሱ የነገሩአትን ከልብዋ አላመነችም፤ ዳሩ ግን ራስዋ ይህ ንጉሥ ምን ዓይነት እንደሆነ ለማወቅ ጉጉት አደረባት፤





እርስዋም እርሱን ለመፈተን የመጨረሻ ከባድ ናቸው ብላ የምታስባቸውን ጥያቄዎች ሁሉ በዝርዝር ጻፈች:: ከዚያም አሽከሮችዋንና ቅመም፣ ዕንቁና ወርቅ የጫኑ ግመሎችዋን ይዛ ረጅሙን ጉዞ ለማድረግ ተነሣች::

የኢየሩሳሌም ሰዎች የውጭ አገር እንግዶችን ማየት የለመዱ ነበሩ፤ ዳሩ ግን የሳባ ንግሥት ከዚያ ስትደርስ ቆመው ይመለከቱ ነበር::

ንግሥቲቱም ወደ ቤተ መንግሥት ተወሰደች፤ እርስዋም ንጉሥ ሰሎሞንን በዝርዝር የያዘችውን ጥያቄ ሁሉ ጠየቀችው:: እርሱም ሁሉንም መለሰላት! የቤተ መንግሥቱን ግቢ ሁሉ አስጎበኙአት፤ ለንጉሡ የሚዘጋጀውን ምግብና ታላላቅ ግብዣዎቹን ሁሉ አየች፤ የቤተ መንግሥቱን ሰዎችና የሚለብሱትን የደምብ ልብስ አየች:: በዚህም ነፍስ አልቀረላትም!ለንጉሡም እንደዚህ አለችው:–

"ስለ አንተ የነገሩኝን ሁሉ አላመንኩም ነበር፤ አሁን ግን ራሴ አይቻለሁ፤ እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለወደደ ጥበበኛ ንጉሥ ሰጥቶአቸዋል" እርስዋም ይዛ የመጣችውን ስጦታ ለንጉሥ ሰለሞን ሰጠችው:: እነዚህም በአገር የማይገኙ ቅመሞች፣ ዕንቁና ወርቅ ነበሩ:: ንጉሡም በተራው የራሱን ስጦታና ሌላም እርስዋ የጠየቀችውን ሁሉ ሰጣት:: ከዚያም ንግሥቲቱና ተከታዮችዋ ወደ ሳባ  አገር ተመለሱ::





# ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤት ሠራ

1ኛ ነገሥት 5–8፤ 11–12


ሰሎሞንም በነገሠ በአራት ዓመቱ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስን መሥራት ጀመረ፤ ከድንጋይ መቆፈሪያ ቦታ ለመሠረቱና ለግድግዳው የሚሆኑ ታላላቅ ድንጋዮች ተጠረቡ፤ ደግሞም ሰሎሞን የዝግባ እንጨትን ፈለገ፤ ጥሩ ጥሩ የዝግባ ዛፎችም የሚገኙት በእስራኤል ሳይሆን በሰሜን በኩል ባለው በንጉሡ በኪራም አገር በጢሮስ ነበር:: ስለዚህ ንጉሥ ሰሎሞንና ንጉሥ ኪራም ስምምነት አደረጉ፤ ዝግባዎቹ ተቆርጠው ወደ ባሕሩ አጠገብ እንዲቀርቡ ተደረገ፤ ግንዶቹም ታንኳ እንዲሆኑ በአንድ ላይ እየታሠሩ በውሀው ላይ ወደታች እንዲንሳፈፉ ተደረገ::

ቤተ መቅደሱ በጣም ትልቅ አልነበረም፤ ዳሩ ግን ሰሎሞን የፈለገውን ያህል ውብ ነበረ፤ እርሱም ሁለት ክፍሎች ነበሩት፤ ዋነኛው ክፍል ከስፋቱ የበለጠ ርዝመት ያለው ሲሆን የውስጠኛው ደግሞ ስፋቱና ርዝመቱ እኩል ነበረ፤ በመካከልም ድርብ በር ነበር፤

የውስጠኛው ክፍል መስኮት ስላልነበረው ውስጡ ጨለማ ነበር፤ በዚህ ክፍል የእግዚአብሔርን ሕግ የያዘው ሳጥን /ታቦት/ ነበረበት፤ በላዩም ላይ በወርቅ ተሸፍነው ከወይራ እንጨት የተሠሩ ክንፋቸው የተዘረጋ ሁለት ግዙፍ እንስሶች ነበሩበት:: ይህም ለእግዚአብሔር የተለየ ክፍል ነበር፤ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ በማስተሰርያው ቀን ከሚገባው ከሊቀካህናቱ በስተቀር ሌላ ማንም አይገባበትም ነበር::

በውጭው ክፍል አንድ መሠዊያና አሥር መቅረዞች ነበሩ፤ እንደ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በውስጡ አይገቡም ነበር፤ እርሱ የእግዚአብሔር ቤት ብቻ ነበር:: የቤተ መቅደሱ ግድግዳዎች ከወለሉ እስከ ጣራው ድረስ በዝግባ እንጨት ሳንቃ የተለበጡ ነበሩ፤ እነዚህም ክንፍ ባላቸው እንስሳት፣ በዘንባባ ዛፎችና በአበቦች ቅርጾች ያጌጡ ነበሩ:: የቤተ መቅደሱ የውስጥ አካል በሙሉ፣ የጥዱ ወለል እንኳን ሳይቀር በወርቅ የተሸፈነ ነበር::

በቤተ መቅደሱ ውጭ ካህናቱ ለእግዚአብሔር መስ ዋዕት ያቀርቧቸው ዘንድ ሕዝቡ የሚያመጡአቸው እንስሶች የሚገኙበት አደባባይ ነበር። በቤተ መቅደሱ መግቢያ ያሉ ትን ሁለት የነሀስ ምሰሶዎች ለመሥራት አንድ የታወቀ አንጥረኛ ከጢሮስ አገር መጥቶ ነበር፤ ደግሞም ከነሀስ ተሠርቶ በአሥራሁለት የበሬዎች ቅርጽ ላይ የተቀመጠ ትልቅ ገንዳና ሳህኖች የተቀመጡባቸው ከነሀስ የተሠሩ ተንቀሳቃሽ መቀመጫዎች ይኸው ባለሙያ ሠራ።






የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ሠርቶ ለመጨረስ ብዙ ሠራተኞች ሆነው ሰባት ዓመታት ፈጀባቸው፤ በመጨረሻ ግን ተፈ ጸመ። እንዴት ውብ ነበር፤! በእግዚአብሔርም ዓይኖች ምንም የማይወጣለት ቆንጆ ነበር።

ከዚያም ሰሎሞን ሕዝቡን ሁሉ ሰበሰበ፤ ካህናቱ ለእግዚአ ብሔር ልዩ መስዋዕትን አቀረቡ፤ እነርሱም የእግዚአብሔር ሕግ ያለበትን ቅዱሱን ታቦት አመጡና በውስጠኛው ክፍል አኖሩት፤ የእግዚአብሔርም ክብር ቤተ መቅደሱን ሞላው።

ሰሎሞንም በሕዝቡ ፊት ቆመ፤ እንዲህም በማለት ጸለየ:- "አ ጌታ እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ፤ ሕዝቡን የሚወ ድና ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ እንደ አንተ ያለ ሌላ አምላክ የለም፤ ቤተ መቅደስህን ተመልከት፤ የሕዝብህንም ፀሎት ስማ፤ ዘወትርም ይቅር በላቸውና እርዳቸው።" ከዚያም ወደ ሕዝቡ ተመለሰ፤ እንዲህም አለ:-"ከአባቶቻችን ጋር እንደነበረ እግዚ አብሔር ከእኛም ጋር ይሁን፤ ለእግዚአብሔር ታማኞችና ትእዛዛቱንም የምትጠብቁ ሁኑ።"
ከሥነ ሥርዓቱ በኋላም ለአንድ ሳምንት
ሙሉ የቆየ በዓል አደረጉ፤
ከዚያም በኋላ ሕዝቡ
ወደ ቤታቸው ሄዱ።




የንጉሥ ሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ለእስራኤል ወርቃማ ዘመን ነበር፤ የእርሱ ነጋዴዎች በርቀትና በስፋት እየሄዱ በመነገድ ባለጠጎች ሆኑ፤ የሠራቸው መርከቦች ክቡር የሆኑ ዕቃዎችን ያመጡ ነበር፡ ያማሩ ሕንፃዎችና ታላላቅ የተመሸጉ ከተሞችም ተሠሩ፤

ዳሩ ግን ሁሉም ነገር እንዲህ መልካም አልነበረም፤ ለግንባታው ሥራ በየጊዜው ቁጥሩ የሚጨምር ገንዘብና የሰው ኃይል አስፈለገ፤ ሕዝቡ ቀረጥ መክፈል ነበረበት፤ ሰዎችም ለራሳቸው በመሥራት ፈንታ ለንጉሡ ለመሥራት ይገደዱ ነበር።

ንጉሥ ሰሎሞንም ብዙ የውጭ አገር ልዕልቶችን አገባ፤ ይህ ለንግድና ለሰላም ጥሩ ነበር፤ ዳሩ ግን እነዚህ ልዕልቶች የራሳቸውን አማልክት ይዘው መጡ፤ እግዚአብሔርን አያመልኩም ነበር። ሰሎሞንም በሸመገለ ጊዜ ሚስቶቹ የእነርሱን አማልክት እንዲያመልክ አግባቡት፤ እንደ አባቱ እንደዳዊት ለእግዚአብሔር ታማኝ ሊሆን አልቻለም

እግዚአብሔርም ለሰሎሞን፣ "ትእዛዛቴን ስላልጠበቅህ መንግሥትህ ከልጅህ ይወሰዳል" አለው። የእግዚአብሔርም ቃል ተፈጸመ፤ ሰሎሞንም ሞተ፤ ብዙም ሳይቆይ የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ተከፈለ፤ የደቡቡ ክፍል የሆነው ይሁዳ ለሰሎሞን ልጅ ለሮብዓም ታማኝ ሆኖ ቀረ፤ ዳሩ ግን አሥር ነገዶች ያሉበት የሰሜኑ ክፍል ተገንጠለና ከሰሎሞን ባለሥልጣኖች አንዱ የሆነውን ኢዮርብዓምን ንጉሥ አደረጉ፤ ኢዮርብዓምም የእግዚአብሔር ሰዎች ያመልኳቸው ዘንድ ሁለት የወርቅ በሬዎችን ሠራ፤ አንደኛውን በደቡብ ባለው በቤቴል ሲያስቀምጥ ሌላውን ደግሞ በሰሜን ባለው በዳን አስቀመጠው፤ በዚህም በኢየሩሳሌም ወዳለው ወደ እግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንዳይሄዱ ለማገድ ፈልጎ ነበር፤ ይህ ያደረገው ግን ስህተት ነበር፡ መጥፎ ችግርን አስከተለ።





# ኤልያስና የበዓል ነቢያት

1ኛ ነገሥት 17 – 19



ኢዮርብዓም የመጀመሪያው የሰሜኑ የእስራኤል ግዛት ንጉሥ ነበር። ከእርሱ በኋላ የነበሩት የእስራኤል ነገሥታት ማንኛቸውም ቢሆኑ ለእግዚአብሔር ታማኝ አልነበሩም። ሁሉም ኢዮርብዓም ያሠራቸውን የበሬዎች ምስሎች እንዲያመልኩ ሕዝቡን ያደፋፍሩ ነበር።

ሰባተኛው ንጉሥ አክአብ ከሌሎቹ እንኳን የባሰ ሆነ፤ የሲዶን ንጉሥ ልጅ የሆነችውን ኤልዛቤል የምትባለውን ጨካኝ ንግሥት አገባ፤ ኤልዛቤልና የእርስዋ ሕዝቦች ለሚያመልኩት በዓል ለተባለው የጦርነትና የአየር አምላክ የተለየ ቤተመቅደስ ሠራለት።

ኤልዛቤልም እግዚአብሔርን እንዲወዱና እንዲታዘዙለት ሕዝቡን የሚያስተምሩትን የእግዚአብሔርን ነቢያት ብዙዎቹን ገደለች። ዳሩ ግን በአክአብ ግዛት ለእግዚአብሔር በድፍረት የሚናገር አንድ ሰው ነበር። እርሱም ነቢዩ ኤልያስ ነበር።



ከእለታት አንድ ቀን እግዚአብሔር ለኤልያስ እንዲህ አለው:-"ሂድና ያደረገውን ክፉ ነገር ሁሉ እኔ እንዳወቅሁ ለንጉሥ አክአብ ንገረው፤ እኔ እስከምናገርበት ቀን ድረስ በእስራኤል ምንም ዝናብ እንደማይዘንብ ንገረው፤"

ኤልያስም የእግዚአብሔርን መልእክት አደረሰ፤ ከዚያም እግዚአብሔር በዮርዳኖስ ወንዝ ትይዩ ባለው በኮራት ፈፋ ውስጥ በሰላም ይቀመጥ ዘንድ ላከው፤ ኤልያስም ከፈፋው ውሀ እየጠጣ ቁራዎችም ምግቡን በየቀኑ እንዲያመጡለት እግዚአብሔር ይልካቸው ነበር፤

ዳሩ ግን ዝናብ ስላልነበረ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የፈፋው ውሀ ደረቀ፤ እግዚአብሔርም ለኤልያስ "ተነሣና ወደሰሜን በሲዶና አጠገብ ወዳለችው ወደ ሰራፕታ ሂድ፤ በዚያም ምግብ የምትሰጥህ አንድ መበለት አለች" አለው። ኤልያስም እንደታዘዘው አደረገ፤ ወደ ከተማም ሲመጣ አንዲት መበለት እንጨት ስትለቅም አገኘ፤ እርሱም "እባክሽ ጥቂት የምጠጣው ውሀና የምበላው እንጀራ ስጪኝ" አላት።





እርስዋም መልሳ፣ "እንጀራ የለኝም፤ ያለኝ አንድ እፍኝ ዱቄትና ጥቂት ጠብታ የወይራ ዘይት ብቻ ነው፤ ይህን እንጨት ወደቤት ወስጄ የመጨረሻዋን እንጀራ ልጋግር ነው፤ ከዚያም እኔና ልጄ መራባችን ነው" አለችው።

ኤልያስም፣ "አታስቢ፣ አስቀድመሽ ለኔ ትንሽ ቂጣ ጋግሪልኝ፤ እግዚአብሔር የረሃቡ ጊዜ እስኪያልፍ ድረስ ዱቄትሽና ዘይትሽ አያልቅም ይላል፤" አላት

ሴትዮዋም ኤልያስ እንዳለው አደረገች፤ በኋላም እውነቱን እንደሆነ አረጋገጠች፤ ዱቄቱና ዘይቱ አላለቀም፤ በየቀኑ እንጀራ ብትጋግርም ሁልጊዜ በቂ ዱቂትና በቂ ዘይት ነበራት።

አንድ ቀን ግን የመበለቲቱ ልጅ ታመመ፤ እየባሰበት ሄደና ከዚያም ሞተ፤ ሲትዮዋም ለኤልያስ "ምንድነው ያደረግኸው? ይህ ቅጣት ነውን? ያደረግሁትን ኃጢአት ለእግዚአብሔር ነግረህ ብኛልን?" አለችው።



ኤልያስም መልሶ "ልጁን ስጪኝ" አላት፤ ከዚያም ልጁን ይዞ እርሱ ወደሚያድርበት ወደ ፎቁ ላይ አወጣውና በአልጋው ላይ አጋደመው። ኤልያስም ድምፁን ከፍ አድርጎ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እንዲህም አለ:- "ይህች ሴት ለእኔ እንዴት ቸር እንደነበረች ታውቃለህ፤ እባክህን የልጇን ሕይወት መልስላት"

ሦስት ጊዜም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም የልጁን ሕይወት መለሰ፤ መበለቲቱም ይህንን ማመን አቃታት፤ ልጁንም በክንዷ ታቅፋ ወደ ነቢዩ ተመለሰችና፣ "አሁን በእውነት አንተ የእግዚአብሔር ሰው እንደሆንክና የምትናገረውም እውነት እንደሆነ አውቄአለሁ" አለችው

# ፈተና

ለሦስት ዓመታት ዝናብ ባለመኖሩ ሕዝቡ ሁሉ በረሃብ ላይ ነበሩ፤ ከዚያም እግዚአብሔር ኤልያስን ወደ ንጉሥ አክአብ እንዲሄድ አዘዘው፡ ንጉሡም "ለምን መጣህ? አንተ በእስራኤል የመጨረሻ መጥፎ ችግር ፈጣሪ ነህ" አለው::

ኤልያስም መልሶ" ይህ ከእውነት የራቀ ነው፤ እግዚአብሔርን ትተህ በዓልን በመከተልህ በእስራኤል ላይ ችግር ያመጣህ አንተ ነህ፣ አሁንም ሕዝቡ ሁሉና የበዓል ነቢያት በቀርሜሎስ ተራራ ከእኔ ጋር እንዲገናኙ ንገራቸው" አለው:: ንጉሡም እርሱ እንዳለው አደረገ::

ሁሉም ከመጡ በኋላ ኤልያስ እንዲህ ሲል ተናገራቸው:– "አሁን ውሳኔ አድርጉ፤ በዓልንና እግዚአብሔርን ማምለክ አትችሉም፤ እውነተኛው አምላክ የትኛው እንደሆነ አሁን እናያለን፤ እግዚአብሔር አምላክ ከሆነ እርሱን አምልኩት፤ በዓልም አምላክ ከሆነ እርሱን አምልኩ"


ከዚያም ወደ በዓል ነቢያት ተመለሰ፤ እንዲህም አለ:– "ሁለታችንም መስዋዕትን እናቅርብ፤ እናንተ ለበዓል በሬን አቅርቡ እኔም ለእግዚአብሔር በሬን አቀር ባለሁ፤ በእሳትም የሚመልስ አምላክ እርሱ እውነተኛ አምላክ ይሆናል::"



ስለዚህ የበዓል ካህናት መሠዊያን ሠሩ፤ በመሠዊያውም ላይ እንጨት አስቀመጡና በሬአቸውን አረዱ፤ ከዚያም በሬውን በእንጨቱ ላይ አስቀመጡት፤

ቀኑንም ሁሉ "በዓል ሆይ ስማን!" እያሉ ተጣሩ፤ በኃይልም ይጨፍሩ ነበር፤ ዳሩ ግን ምንም መልስ አልነበረም፤ ምንም የሆነ ነገር አልነበረም፤

ኤልያስም ተራው በደረሰ ጊዜ መሠዊያን ሠራ፤ እንጨቱን በላዩ ረበረበ፤ በሬውንም አረደ፤ ከዚያም እንጨቱ እስኪርስ ድረስ በሞተው በሬ ላይ ውኃን አፈሰሰ፤ በመሠዊያውም ዙሪያ ጉድጓድ ቆፈረና ውሀ ሞላው፡ ከዚያም እንዲህ ሲል ጸለየ:: "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤ ሕዝብ ሁሉ አንተ አምላክ እንደሆንክ ይወቁ::"
ከዚያም እግዚአብሔር እሳትን አወረደ፡ ኃይለኛ እሳት ውሀውን በላና መስዋዕቱን አቃጠለ፡ ሕዝቡም ይህን ባዩ ጊዜ በግምባራቸው ወደ ምድር ተደፉ፤ ከዚያም እየ ጮኹ፣ "እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው! እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው!" አሉ:: የበዓልንም ነቢያት በሙሉ አንድ ሳያመልጥ ያዙና ገደሉአቸው::



ከዚያም ኤልያስ ዝናብ እንዲዘንብ እግዚአብሔርን ጠየቀ፣ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ንፋስ ነፈሰ፣ ሰማይም ጠቆረ፣ ዝናብም መዝነብ ጀመረ፣ በኤልያስ ሕይወት ይህ እጅግ ታላቅ ነገር ነበረ። ከዓለም ሁሉ በላይ መሆኑ ተሰማው፣ እንዲያውም በንጉሡ ሠረገላ ፊት ለፊት እየሮጠ ኢይዝራኤል ከሚገኘው ቤተ መንግሥት ድረስ ሄደ።

በማግሥቱ ግን ነገር ሁሉ ተለወጠ፣ ኤልያስ እንደገና ይሮጥ ጀመር፣ በዚህ ጊዜ ግን ነፍሱን ለማዳን ነበር፣ ንግሥት ኤልዛቤል እርሱን ለመግደል መሃላ አድርጋ ነበር፣ ለብዙ ኪሎሜትር ሲበር፣ ሲበር ወደ ደቡብ ወደ ምድረ በዳው ደረሰ፣ እንደገናም እየበረረ ወደ ሲና ተራራ ደረሰ፣ አሁን ፍጹም ብቸኛ ነበረ፣ ሁሉም ፀጥ ያለ ነበር።አንድም ድምፅ አልነበረም። ከዚያም የእግዚአብሔር ድምፅ ወደ እርሱ መጣ፣ "ኤልያስ፣ እዚህ ምን ታደርጋለህ?" አለ።

እርሱም፣"ነቢያትህን ሁሉ ገድለዋል፣ እኔ ብቻ ቀርቻለሁ፣ እኔንም ደግሞ ሊገድሉኝ ይፈልጋሉ" አለ።

እግዚአብሔርም መልሶ "ተመልሰህ ሂድ፣ ገና የምትሠራው ሥራ አለ፣ ንግሥት ኤልዛቤልንና ንጉሥ አክአብን ለኔ ተዋቸው፣ ሂድና ከአንተ በኋላ የእኔ ነቢይ የሚሆነውን ኤልሳዕን ፈልገው፣ አንተም ብቻህን የሆንክ አይደለህም። በእስራኤል በአልን ፈጽሞ ያልተከተሉ ገና 7000 ሰዎች አሉ።

ስለዚህ ኤልያስ ተበረታታ፣ ኤልሳዕንም በእርሻ ውስጥ ሲያርስ አገኘው። በእስራኤልም የሚቀጥለው ነቢይ መሆኑን ለማሳየት ካባውን አውልቆ በኤልሳዕ ትከሻ ላይ አስቀመጠው፣ ኤልሳዕም ቤቱን ትቶ ከእርሱ ጋር ሄደ።



# ንጉሥ አክአብና የወይን ቦታው

1ኛ ነገሥት 21 – 22

በእስራኤል ከንጉሥ አክአብ ቤተ መንግሥት ጎን አንድ የወይን ቦታ ነበር። እርሱም ናቡቴ የሚባል የአንድ ሰው ነበር፣ ንጉሡም "ይህ የወይን ቦታ ግሩም የሆነ የጎመንና የሰላጣ ቦታ ይሆናል" በማለት አሰበ፣ ስለዚህ ናቡቴን ጠራና ይሸጥለት እንደሆነ፣ ወይም በእርሱ ምትክ ሌላ የወይን ቦታ ይወስድ እንደሆነ ጠየቀው፣ ናቡቴ ግን አልፈቀደም፣ እንዲህም አለው፣ "አይሆንም፣ ይህ የወይን ቦታ ከቤተሰቤ የወረስሁት ነው፣ እኔም ስሞት ለልጄ ሳወርሰው እፈልጋለሁ፣ የእግዚአብሔርም ሕግ ለሌላ ሰው እንዳልሸጥ ይከለክለኛል።"

ንጉሥ አክአብ የራሱን እርምጃ መውሰድን ያውቅበት ነበር፣ ማንም ሰው ለእርሱ እምቢ አይለውም ነበር! የናቡቴ መልስ አናደደው፣ አፍንጫውን አስነፋው፣ ፊቱ ሁሉ ስለ ተለዋወጠ ንግሥት ኤልዛቤል ምን እንደነካው ጠየቀችው፣ እርሱም በነገራት ጊዜ "ንጉሥ አይደለህም እንዴ? ይህ የወይን ቦታ የአንተ ይሆናል፣ እርሱን ለኔ ተወው" አለችው።



ንግሥት ኤልዛቤል ሁልጊዜ የፈለገችውን ነገር ታገኝ ነበር፤ ማንም ቢጎዳ ግድ አልነበራትም። ናቡቴንም በክህደት ወንጀል እንዲከሰስና እንዲፈረድበት ካደረገች በኋላ በድንጋይ ተወግሮ እንዲሞት አደረገች። ዳሩ ግን እርሱ ንጹህ ሰው ነበር፤


ከዚያም ወደ ንጉሡ ሄደችና "ናቡቴ ሞቷል፤ አሁን የወይን ቦታውን ለመውሰድ የሚከለክልህ የለም" አለችው፤ ንጉሡም ወደ ወይን ቦታው በሄደ ጊዜ ነቢዩ ኤልያስ ወደ እርሱ መጣ፤ እንዲህም አለው፡–

"እግዚአብሔር የናቡቴን ደም ስላፈሰስህ የአንተም ደም ይፈስሳል ይልሃል፤ ኤልዛቤልም በዚሁ በእስራኤል ትሞታለች፤ መላው ቤተሰብህም ይጠፋል።"

አክአብም በኤልያስ አነጋገር በጣም ደነገጠ፤ ለጊዜው አካሄዱን ለወጠ፤ ግን አልቆየም።

ከሦስት ዓመት በኋላ ንጉሥ አክአብ ከይሁዳ ንጉሥ ከኢዮሳፍጥ ጋር ኃይሉን አስተባብሮ ከሦርያውያን ጋር ሊዋጉ ሄዱ፤ በሬማት ዘገለዓድም ታላቅ ውጊያ ተደረገ።

ኢዮሳፍጥ እንደተለመደው የንጉሥ ካባ ለብሶ ነበር፤ አክአብ ግን እንዳይመታ ራሱን ለውጦ የተራ ወታደር ልብስ ለብሶ ነበር፤ ዳሩ ግን አንድ የጠላት ቀስተኛ ቀስቱን ሲያነጣጥር ቀስቱ በንጉሡ ጥሩር መጋጠሚያ ባዶ ቦታ አገኘች። አክአብም በሠረገላው ውስጥ ደሙ ፈስሶ ሞተ፤ የእግዚአብሔርም ቃል ተፈጸመ፤





# የኤልሳዕ ታሪኮች

2ኛ ነገሥር 2፡ 4 – 5



ኤልያስ አሁን አረጀ፤ የመጨረሻ ጉዞ የሚያደርግበትም ጊዜ ደረሰ፤ እንደተለመደውም ኤል ሳዕ ከእርሱ ጋር ሄደ።

በርከት ያሉ ነቢያት በኢያሪኮ ተከተሏቸውና ከዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ ሲደርሱ ቆመው ይመለከቷቸው ነበር፤ ኤልያስም ካባውን ጠቅልሎ ውሀውን መታው፤ በፊታቸውም ውሀው ተከፈለና ሁለቱ ሰዎች በደረቁ ተሻገሩ፤ ከተሻገሩም በኋላ ኤልያስ ለኤልሳዕ፡– "አሁን ትቼህ ልሄድ ነው፤ ከመሄዴ በፊት የምትፈልገው ነገር አለህን?" አለው፤ ኤልሳዕም መልሶ፣ "የአንተን ሥራ ብቻዬን ልሠራ ነው፤ እኔ ወራሽህ ስለ ሆንኩ የአንተን ኃይል ተውልኝ" አለው።

ኤልያስም መልሶ፣ "ይህ ከባድ ነገር ነው፡ ዳሩ ግን እኔ ከአንተ በምወሰድበት ጊዜ ብታየኝ የጠየቅኸውን ነገር እንደምታገኝ እርግጠኛ ልትሆን ትችላለህ" አለው፡፡ ገና በመነጋገር ላይ እያሉ በእሳት ፈረሶች የሚጎተት የእሳት ሠረገላ በመካከላቸው አረፈ፡ ኤልሳዕም ኤልያስን በታላቅ አውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ሲወሰድ አየው፡ እርሱም ብቻውን ቀረ፡፡

በጣም እያዘነ የኤልያስን ካባ አንስቶ ወደ ወንዙ ተመለሰ፡ ውሀውን መታና፣ "የኤልያስ አምላክ እግዚአብሔር ወዴት ነው?" አለ፡፡ ወዲያውም ውሀው እንደ በፊቱ ተከፈለና ሊሻገር ቻለ፡ ከዚያም ቆመው ይመለከቱ የነበሩት ነቢያት ዳግመኛ ኤልያስን እንደማያዩትና እግዚአብሔር ኤልሳዕን የእርሱን ቦታ እንዲወስድ እንደመረጠው አወቁ፡

## የሱነሙ ቤት

ኤልሳዕ በእስራኤል የእግዚአብሔር ነቢይ እንደመሆኑ መጠን የእግዚአብሔርን ሕግ እያስተማረ ከቦታ ወደ ቦታ ብዙ ጉዞ አደረገ፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን በጣም እርቦትና ደክሞት በአቧራም ተሸፍኖ ወደ ሱነም ደረሰ፡ አንዲት ባለጠጋ ሴትዮም በበርዋ አጠገብ ሲያልፍ ምግብ እንዲበላ ጋበዘችው፡፡ በልቶም ሊሄድ ሲል "በፈለግህ ጊዜም እንደገና መምጣት ትችላለህ" አለችው፡፡

ሴትዮዋ ባለጠጋ የመሆኗን ያህል ርህሩህም ስለሆነች ኤልሳዕ ወደዳት፡ ከዚያም በኋላ ብዙ ጊዜ ወደ ቤቷ መጣ፡፡

ከዚያም ሴትዮዋ ለባልዋ እንዲህ አለችው:- ለዚህ ለእግዚአብሔር ሰው አንድ ክፍል ቤት እንሥራለት፡ ከዚያም ወደ ሱነም በመጣ ጊዜ በዚህ ያርፋል፣"

በቤታቸው ጣራ ላይ አንድ ክፍል ሠሩለት፡ ባለቀም ጊዜ ሴትዮዋ አንድ አልጋ፣ አንድ ጠረጴዛ፣ አንድ ወንበርና አንድ ፋኖስ አስቀመጠችለት፡፡ ኤልሳዕም ተደሰተ፣ ለአገልጋዩም ለግያዝ "እነዚህ ሰዎች ብዙ ነገር አደረጉልን፡ እኛስ በአጸፋው የምናደርግላቸው ነገር የለምን?" አለው፡፡





ግያዝም "ከልጅ በስተቀር ሁሉ ነገር አላቸው፤ ሀብታሞች ናቸው" አለው፤ ኤልሳዕም ሴትዮዋን ወደርሱ ጠራት፤ እር ሱም፣ "የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ" አላት። ኤልሳዕም የተናገረው ተፈጸመና ደስ አላት።

ዳሩ ግን ከጥቂት ዓመታት በኋላ አሳዛኝ ነገር ሆነ። ትንሹ ልጅ በእርሻ መካከል አባቱን በመርዳት ላይ እያለ በድንገት "ራሴን ራሴን!" ብሎ ጮኸ። አባቱም ወደ እናቱ ወደ ቤት ላከው፤ ዳሩ ግን ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ሞተ። የልጁም እናት ወደ ኤልሳዕ ክፍል አገባችውና በሩን ዘጋችበት። ከዚያም አህያዋን ጫነችና ኤልሳዕን ፈልጋ ለማምጣት ሄደች። ኤልሳዕም ወደሱነም በደረሰ ጊዜ ብቻውን ወደ ክፍሉ ሲገባ ልጁ ሞቶ በአልጋው ላይ ተጋድሞ አየው።

ኤልሳዕም "ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ የልጁን ሕይወት መልስ" ብሎ ጸለየ። አፉንም በልጁ አፍ ላይ ባደረገ ጊዜ የልጁ አካል መሞቅ ጀመረ፤ ልጁም ሰባት ጊዜ ካስነጠሰ በኋላ ዓይኖቹን ከፈተ፤ ኤልሳዕም ሴቲቱን ጠራና "ቶሎ ነይ፣ ልጅሽ ድኖአል!" አላት።

# የሶርያው አዛዥ



ንዕማን በሶርያ አገር ታላቅ ሰው፣ የንጉሡም የጦር ሠራዊት አዛዥ ነበረ። እርሱም የተመኘው ነገር ሁሉ ነበረው፤ ሥልጣን፣ ዝና፣ ሀብት፣ ቤትና የሚጠብቁት አሽከሮች ሁሉ ነበረው፤ ዳሩ ግን በዚያን ጊዜ ፈውስ ያልነበረው አስከፊ የቆዳ በሽታ ደግሞ ነበረበት፤ እርሱና ሚስቱ በጣም ይረበሹ ነበር።

አንድ ጊዜ ባደረጉት ዘመቻ ሶርያውያን አንዲት እስራኤላዊት ሴት ልጅ ማርከው ነበር። እርስዋም ለንዕማን ሚስት አገልጋይ ነበረች።

እርስዋም "ጌታዬን ሊፈውሰው የሚችል በእስራኤል ነቢይ አለ" አለች። የሶርያም ንጉሥ መሸኛ ደብዳቤ አዘጋጀለትና ንዕማን ኤልሳዕን ሊፈልግ ወደ እስራኤል ሄደ፤ የኤልሳዕም አገልጋይ በበር ተቀበለውና "ጌታዬ ሂድና በዮርዳኖስ ወንዝ ሰባት ጊዜ ታጥበህ ትድናለህ ይልሃል" አለው።

ምን ዓይነት ንቀት! ንዕማን የፈለገው ኤልሳዕ አንድ ተአምር እንዲያሳየው ነበር፡ በዚህ በጣም ተበሳጨ፤ እንዲህም አለ

"መታጠብ ብቻ ከሆነማ ከዚህ የተሻሉ ወንዞች በሶርያ አሉ" ዳሩ ግን አሽከሮቹ ሁሉ በአንድ ቃል እንዲሞክር አግባቡት፤ ምክሩም ሠራ፤ ወደ ወንዙ ሄደና በውሀው ውስጥ እየተራመደ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ አለ፤ ከዚያም ፈጽሞ ተፈወሰ፤ ነቢዩንም ሊያመሰግን ተመለሰ። እርሱም "እውነተኛው አምላክ የእስራኤል አምላክ እንደሆነ አሁን አወቅሁ" አለ።



## የእግዚአብሔር ሠራዊት

በሶርያና በእስራኤል መካከል እንደገና ጦርነት ተነሣ፡ ሦርያውያን የደፈጣ ተዋጊዎች አቋቋመው ነበር፡ ኤልሳዕ ግን ለእስራኤል ንጉሥ ወደዚያ ቦታ እንዳይጠጋ አስጠንቀቀው፡ ሶርያውያን ስቅድ ባዘጋጁ ጊዜ ሁሉ ኤልሳዕ ያውቅና የእስራኤልን ንጉሥ ያስጠነቅቅ ነበር።

የሦርያም ንጉሥ ኤልሳዕን ፈልጋችሁ ያዙና አምጡልኝ ሲል ፎከረ፡ ኤልሳዕም በዶታን አለ የሚል ወሬ መጣ፡ የሦርያም ንጉሥ ከተማውን ለመክበብ በሌሊት ፈረሶችንና ሠረገሎችን ላከ፡ በማግስቱ የኤልሳዕ አገልጋይ እነርሱን ባያቸው ጊዜ በፍርሃት ተንቀጠቀጠ።



እርሱም ለኤልሳዕ "ተይዘናል፣ምን ይሻለናል?" አለው፡ ኤልሳዕ ግን በጭራሽ አልተጨነቀም፡ እርሱም ሲጸልይ፣

"ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ የዚህን አገልጋይ ዓይኖች ክፈት" አለ። አገልጋዩም ቀና ብሎ ሲመለከት ብዙ የእሳት ፈረሶችና ሠረገሎች የሦርያን ሠራዊት ከብበው አየ። እርሱም እግዚአብሔር ነቢዩን ከጉዳት እንደሚጠ ብቀው አወቀ።

ኤልሳዕም በሕይወት ዘመኑ ብዙ ታላላቅ ድንቅ ነገሮችን አደረገ፣ ነገሥታት እንኳን ከእርሱ ምክር ሊጠ ይቁ እስከሚመጡ ድረስ ዝነኛ ሆነ። ዳሩ ግን ደግሞ ተራ ሰዎችን ለመርዳት ጊዜ ነበረው፡ በሞተም ጊዜ አገሩ በሞላ አዘነ።



# ኢዮአስ ወጣቱ ንጉሥ

2ኛ ነገሥት 11 – 12

ኤልያስና ኤልሳዕ ይኖሩበት በነበረው በሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት የማያቋርጥ የሥልጣን ትግል ነበር። ነገሥታቱ ለእግዚአብሔር ታማኝ አልነበሩም፡ ስለዚህ ብዙ ጦርነትና አመፅ ነበረ፡

በደቡቡ መንግሥት በይሁዳ ነገሮች ከዚህ የተሻሉ ነበሩ፡ በዋና ከተማዋ በኢየሩሳሌም ነገሥታት በየተራ በዙፋኑ ይፈራረቁ ነበር። ሁሉም ደግሞ ከንጉሥ ዳዊት ቤተሰብ ዘር ነበሩ። አብዛኞዎቹ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ መልካም ነገሥታት ነበሩ፡ አንዳንዶቹ ግን እንደ እስራኤል ነገሥታት ነበሩ፡ ጣዖታት የሆኑትን በዓልንና ሌሎችን አማልክት ለማምለክ ከሕያው አምላክ ዘወር ብለው ነበር።

ከሰሎሞን በኋላ ልጁ ሮብዓም ነገሠ፡ ከሮብዓምም በኋላ ልጁ ንጉሥ አቢያ፡

. . . ከዚያም ልጁ ንጉሥ አሳ፣

. . . ከዚያም ልጁ ንጉሥ ኢዮሳፍጥ

. . . ከዚያም ልጁ ንጉሥ ኢዮራም

ንጉሥ ኢዮራም ሞኝ ሥራ ሠራ፡ የእስራኤልን ንጉሥ የአክአብን ልጅ ጎቶልያን አገባ፡ እንደዚህ ያለው ጋብቻ ችግርን እንደሚያመጣ ማወቅ ነበረበት፡ ደግሞም አመጣ። የባሰው ችግር ግን ኢዮሬም ከሞተ በኋላ ነበረ። የንጉሥ ኢዮራምና የንግሥት ጎቶልያ ልጅ የሆነው አዲሱ ንጉሥ አካዝያስ ቤተሰብ ለመጎብኘት ወደ እስራኤል ንጉሥ ለመሄድ ወሰነ፡ እንዳጋጣሚ ወቅቱ መጥፎ ነበር።

በዚያ በነበረበት ጊዜ ኢዩ የሚባል አንድ ወታደራዊ መኮንን አመፅ አካሄደ፡ የእስራኤልም ንጉሥ ሞተ፡ ንግሥቲቱም ኤልዛቤል በኢይዝራኤል ከቤተ መንግሥት በመስኮት ተወረወረችና እግዚአብሔር እንደተናገረው አስከፊ ሞት ሞተች።

አካዝያስም ወደ ሠረገላው ውስጥ ገባና ለማምለጥ ሞከረ፤ ዳሩ ግን የኢዩ ሰዎች ደረሱበትና በጽኑ ስላቆሰሉት እቤቱ ሳይደርስ ሞተ። ንግሥት ጎቶልያም የሆነውን በሰማች ጊዜ በቁጣ ነደደች፤ እያንዳንዱ ንጉሣዊ ቤተሰብ እንዲገደል ወታደሮቹን አዘዘች፤ የይሁዳንም ግዛት ራስዋ ለመግዛት ፈለገች። ይህ ማለት የንጉሥ ዳዊት ቤተሰብ ሥርወ መንግሥት ተቋረጠ ማለት ነበር። እግዚአብሔር ግን ለንጉሥ ዳዊት "የአንተ ሥርወ መንግሥት አይቋረጥም" ብሎ ተስፋ ሰጥቶት ነበር።



ጎቶልያም ከአንዱ በስተቀር ንጉሣውያን ቤተሰብን ሁሉ ገደለች፤ የንጉሥ አካዝያስ ሕፃን ልጅ የሆነው ኢዮአስ አክስቱ በቤተ መቅደስ ውስጥ ወስዳ ደበቀችውና ተረፈ። ኢዮአስ ለስድስት ዓመታት በሊቀ ካህኑ በዮዳሄ ይጠበቅ ነበር፤ ይህም ፍጹም ምስጢር ነበር፤ ማንም አያውቅም ነበር። ዳሩ ግን ሰባት ዓመት በሆነው ጊዜ ዮዳሄ ለክብር ዘብ አዛዦች ላከባቸውና ምስጢሩን ነገራቸው።



"የምታደርጉት እንዲህ ነው" አለና ዕቅዱን ነገራቸው። በሚቀጥለው ቅዳሜ /በሰንበት/ በእረፍት ላይ የነበሩት የክብር ዘበኞች በሙሉ በቀጥታ ወደ ቤተመቅደስ ሄዱ። ከዚያም ዮዳሄ ኢዮአስን ሰይፍ በመዘዙ የክብር ዘበኞች አሳጅቦ ከቤተ መቅደስ አወጣው፡ ዘውዱንም በራሱ ላይ አስቀምጦ የይሁዳ ንጉሥ ብሎ አዋጅ አስነገረ፡

ሕዝቡም በጣም ተደሰተ፡ እየጮኹም "ሺህ ዓመት ንገሥ!" አሉ። ንግሥት ጎቶልያም ጩኸቱን ሰምታ ወደ ቤተመቅደስ ስትሮጥ ኢዮአስን በዚያ ቆሞ አየችው፡ እርስዋም "አመፅ ነው! አመፅ ነው!" ብላ ጮኸች።

ግን ማንም ወደ እርሷ አልመጣም፡ የንግሥት ጎቶልያ አገዛዝ የሽብር አገዛዝ ነበር፡ ሁሉም ይፈራትና ይጠላት ነበር፡ ስለዚህ ወታደሮቹ ወስዱአትና ገደሏት። ከዚያም ሕዝቡ ወደ በዓል ቤተ መቅደስ ሄዱና ጣዖታቱን ሁሉ አፍርሰው መሠዊያውንም አደቀቁት፡ አሁን እንደገና እግዚአብሔርን ለማምለክና በሰላም ለመኖር ነፃነት አገኙ፡

ኢዮአስ ለአርባ ዓመታት ነገሠ፡ ሊቀ ካህናቱ ዮዳሄም እግዚአብሔርን እንዲያውቅና ትእዛዛቱንም እንዲወድ ከልጅነቱ ጀምሮ አስተምሮት ነበር። እርሱም አልረሳውም ነበር።

የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ችላ ተብሎ ነበር፡ ኢዮአስ ሊያደርግ የፈለገው የመጀመሪያው ነገር እርሱን ማደስና እንደ ቀድሞው ማድረግ ነበር።

ስለዚህ ኢዮአስ የታወቀው ወጣት ንጉሥ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ያደሰ ንጉሥ በመሆኑ ነው።



# ከሰሜን የመጣ ወራሪ

2ኛ ነገሥት 18-20፤ ኢሳይያስ

ንጉሥ ኢዮአስ ከሞተ ከሰባት ዓመታት በኋላ በትውልድ ሐረግ የእርሱ የብዙ ጊዜ የልጅ ልጅ የሆነው ሕዝቅያስ በይሁዳ ላይ ነገሠ፤ ሕዝቅያስም ችግር ነበረበት፤

በሰሜን ምሥራቅ በኩል የአሦር መንግሥት ኃይለኛ ሆኖ ነበር፤ አሦራውያን ወታደሮች ወሰን እያለፉ ወደ ጎረቤት አገሮች ይፈልሱ ነበር፤ ከተሞችን ይወርሩ ይዘርፉና ይገድሉ ነበር፤ አስከፊ የሆነው የጭካኔአቸው ወሬ ሁሉንም ያስፈራ ነበር።


በአካባቢው የነበሩ ትናንሽ መንግሥታት በአሦር ግዛት አንድ በአንድ እያሉ ተውጠው ነበር፤ ሕዝቅያስ ለአራት ዓመታት እንደነገሠ አሦራውያን ወደ ደቡብ ተጉዘው እስራኤል ውስጥ ገብተው ነበር፤ የሰሜኑ ግዛት የእስራኤል ዋና ከተማ የሆነችውን ሰማርያን ለሦስት ዓመታት ያህል ከብበዋት ነበር። ከተማዋ በእጃቸው ከመውደቋ በፊት ብዙ ሰዎች በረሃብ ሞተው ነበር።

አሦራውያን የእስራኤልን ንጉሥ ይዘው አሠሩት፤ እስራኤላውያን አገራቸውን እንዲለቁና ወደ ሩቅ አገር ለብዙ ኪሎሜትር እንዲጓዙ አስገደዱአቸው። ከዚያም በኋላ እንደገና ወደ አገራቸው ፈጽሞ አልተመለሱም። የውጭ አገር ሰዎች ወደ እስራኤል አገር መጥተው ተቀመጡ፤ እነርሱም የራሳቸውን አማልክት ይዘው በሰማርያ ተቀመጡ።



ይህም በጣም አስከፊ ነገር ነበር፡ ይህም ሁሉ የሆነው እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ለመስማትና ለመታዘዝ እምቢ ስላሉ ብቻ ነበር፡ ብዙ ጊዜ አስጠንቅቆአቸው ነበር፡ ዳሩ ግን ፈጽሞ አንሰማም አሉ።

በይሁዳ አገር ነገሮች ሁሉ ብዙም የተሻሉ አልነበሩም፡ ሕዝቡ ከእንጨትና ከድንጋይ የተሠሩ ምስሎችን ያመልኩ ነበር። እግዚአብሔር ጭራሽ በመረሳት ላይ ነበር፡ ዳሩ ግን ሕዝቅያስ ንጉሣቸው በመሆኑ የይሁዳ ሰዎች ዕድለኞች ነበሩ፡ ሕዝቅያስም በእግዚአብሔር የሚታመን መልካም ሰው ነበረ፤ ምስሎቹ ከቦታቸው ተነስተው እንዲሰባበሩ አደረገ።






እርሱም፣ "ሕዝቤ እንደ እኔ በእግዚአብሔር እንዲታመኑ እፈልጋለሁ" አለ፤ የይሁዳ ሰዎች በሌላም በኩል የታደሉ ነበሩ፡ ኢሳይያስ ነቢያቸው ነበረ፤ ኢሳይያስም የእግዚአብሔርን ሀሳብ ይነግራቸው ነበር።

እርሱም፣ "እንደ እስራኤል ሕዝብ አትሁኑ፤ ይህ ምን እንደሚያመጣባችሁ ማየት ትችላላችሁ፡ እግዚአብሔርን ውደዱ ታዘዙለት፤ አሦራውያን እየመጡ ናቸው፡ ቢሆንም አትፍሩ፤ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው" አላቸው።

ልክ ከሰባት ዓመት በኋላ አሦራውያን መጡ፤ ወደ ደቡብ ወደ ይሁዳ ተጉዘው ጠረፍ ላይ ያለውን ምሽግ አጠቁት፤ እየቀረቡ እየቀረቡ መጡና ወደ ኢየሩሳሌም በሮች ደረሱ፤ ንጉሡን ሕዝቅያስን፣ ኢሳይያስን፣ እንዲሁም ሕዝቡን ሁሉ በወጥመድ እንደተያዘች ወፍ በውስጥ እንዳሉ ዘጉባቸው።

ከአሦራውያን ሠራዊት ሦስቱ ከከተማዋ በበሮች አጠገብ ቆመው ነበር፤ ወደ ንጉሡም በጮኹ ጊዜ ሦስት የሕዝቅያስ ሹማምንት ወደ እነርሱ ወጡ፤ የኢየሩሳሌምም ሰዎች በከተማዋ አጥር ላይ ሆነው ይጠብቁና ያዳምጡ ነበር፤ የአሦራውያን ወታደሮች ጦርና ጋሻ በፀሐይ ብርሃን ሲያንፀባርቅ እየተመለከቱ በፍርሃት ተንቀጠቀጡ። አሦራውያንም እንዲህ አሉ፣





"ይህ የታላቁ የአሦር ንጉሥ የሰናክሬብ ቃል ነው። አሁን እርቅ አድርጉ፥ እናንተ በእጄ ውስጥ ናችሁ። አምላካችሁ የሚያድናችሁ ይመስላችኋልን? የሌሎች አገሮች አማልክት ከእኛ ንጉሥ አድነዋቸዋልን? ሰማርያን ያዳናት አለን? እግዚአብሔር ያድናችኋል ብሎ ሕዝቅያስ አያታልላችሁ፥ ይልቅስ አሁን ውጡና እጃችሁን ስጡ!"

ሕዝቡ ግን ምንም አልመለሱም፤ ሕዝቅያስም እርዳታ እንዲያደርግለት ወደ ነቢዩ ኢሳይያስ ሰዎችን ላከ፥ ነቢዩም ሰማቸው፣ ኢሳይያስም መልሶ፣ "ሕዝቅያስን እንዳይፈራ ንገሩት፤ እግዚአብሔር ከተማይቱን በእርግጥ ያድናታል" አለ። የአሦርም ንጉሥ ሰናክሬብ ለንጉሥ ሕዝቅያስ ደብዳቤ ጻፈ። እርሱም፣ "ከተማችሁን አጠፋታለሁ፥ አምላካችሁ ሊያድናችሁ አይችልም" አለው። ሕዝቅያስም ደብዳቤውን ወደ ቤተ መቅደስ ወሰደና ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገረ፤ እንዲህም አለ፦ "አምላክ አንተ ብቻ ነህ፥ ዓለምን የፈጠርህ የነገሥታት ንጉሥ ነህ፥ ስለዚህ እባክህ ከአሦራውያን አድነን"



ኢሳይያስ እንደገና ለንጉሡ እንዲህ የሚል መልእክት ላከ፥ "እግዚአብሔር የአሦራውያንን ስድብ ሰምቶአል፥ እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል፣ 'ኃይል የሰጠሁት እኔ ነኝ፥ ዳሩ ግን አሁን እኔ እይዘዋለሁ፤ ወደ ከተማዋ አይገባም፥ ወታደሮቹም አንዲት ቀስት እንኳን አይወረውሩባትም፤ ኢየሩሳሌምን እኔ እጠብቃታለሁ'"

በዚያች ሌሊት በአሦራውያን ሠፈር አስከፊ ነገር ተፈጸመ፤ በሺህ የሚቆጠሩ የአሦራውያን ወታደሮች ሞቱ፤ በምን እንደሆነ አልታወቀም፤ በማግሥቱ ጧት ሠፈሩ ሁሉ ሬሳ ብቻ ነበር።

ከዚያም የአሦር ንጉሥ ወራሪ መጥቶአል የሚል ወሬ ሰማ፤ ወደ ዋና ከተማውም ወደ ነነዌ ተመለሰ፤ ብዙም ሳይቆይ የገዛ ሁለት ልጆቹ ገደሉት፤ ኢየሩሳሌምም አረፈች።

## ኢሳይያስ የወደፊቱን አየ

ሕዝቅያስ ባረጀ ጊዜ ከባቢሎን ንጉሥ ሰዎች ወደ እርሱ መጡ፤ ሕዝቅያስም በወዳጅነት አስተናገደና ግምጃ ቤቱን ሁሉ አሳያቸው፤ ከዚያም ኢሳይያስ ለንጉሡ እንዲህ አለው፦

"ባቢሎናውያን አሁን ወዳጆቻችን ናቸው፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር አንድ ቀን ግምጃ ቤቶችህና ከሕዝብህ ብዙዎቹ ወደ ባቢሎን ይማረካሉ ይልሃል" እግዚአብሔር ለኢሳይያስ በሕዝቡ ላይ የሚሆነውን ነገር አሳይቶት ነበርና ነው።

ኢሳይያስም ለሕዝቡ፦"እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ከአሦራውያን አድኖአታል፤ ዳሩ ግን እናንተ በእውነት ለእርሱ ካልታዘዛችሁና ካልታመናችሁበት አንድ ቀን ኢየሩሳሌም ትወድቃለች፤ የጠላት ወታደሮች ወደ ሩቅ አገር በግዞት ሊያኖሩአችሁ ይወስዱአችኋል፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ፈጽሞ አይተዋችሁም፤ እንደገና ወደ ቤታችሁ ይመልሳችኋል" አላቸው። የነቢዩ ዓይኖች በሩ፤ እግዚአብሔር ሊያደርግ ያቀዳቸውን አንዳንድ ድንቅ ነገሮች ተመለከተ፤ አሁን አይፈጸሙም፤ በቅርብም አይሆኑም፤ ዳሩ ግን ወደፊት ይፈጸማሉ፤ አንድ ቀን እግዚአብሔር የራሱን ንጉሥ ይልካል።

"እግዚአብሔር ገገርአችን የሚሆን ሕፃን ይልክልናል፤
እርሱም ድንቅ መካር፤
ኃያል አምላክ፤ የዘላለም አባት
የሰላም አለቃ . . . . ተብሎ ይጠራል፤
እርሱም በዳዊት ዙፋን ላይ ይገዛል፤
ኢሳይያስም "ለእግዚአብሔር ንጉሥ መንገድ
ማዘጋጀት አለብን። በምድረ በዳ መንገድ ጥረጉለት
ሸለቆውም ዝቅ ይበል፤

ከዚያም ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ክብር ያያሉ" አለ።

ኢሳይያስም የተናገረው ሁሉ ተፈጸመ፤ በዚያ ጊዜ ግን አልነበረም። ዳሩ ግን ከብዙ ዘመን በኋላ ነበር፡



# ኢዮስያስ ያገኘው ነገር

2ኛ ነገሥት 22 – 23



ከሕዝቅያስ በኋላ የነገሡት ነገሥታት እርሱ ያደረገውን መልካም ነገር ሁሉ አበላሹት፤ ሕዝቡ እንደገና ምስሎችን ሠርተው አመለኩ፤ እንዲያውም የራሳቸውን ልጆች እንኳን እያረዱ ለእነዚህ አማልክት መስዋዕት አቀረቧቸው። ወደ ጥንቆላም ተመልሰው ፀሐይንና ጨረቃን አመለኩ።

የይሁዳ ሰዎች የእስራኤልን መጥፎ ምሳሌ ተከተሉ፤ ብዙ ሳይቆይ ይሁዳም ትጠፋለች፤ ዳሩግን ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆነ ኢዮስያስ የሚባል አንድ የመጨረሻ ንጉሥ ነበረ።

ኢዮስያስ በነገሠ ጊዜ እንደ ኢዮአስ ልጅ ነበረ፤ አሥራ ስምንት ዓመት በሆነው ጊዜ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንዲታደስ ትእዛዝ ሰጠ፤ ሠራተኞችም ሲሠሩ አንድ ትልቅ መጽሐፍ በመጋዘን ውስጥ ተደብቆ አገኙ፤ ካህኑ ኪልቅያስ ለኢዮስያስ ጸሐፊ ሰጠውና ጸሐፊውም ለንጉሡ ጮክ ብሎ አነበበለት፤ ኢዮስያስም እያዘነ አዳመጠው፤ እርሱም እንዲህ አለ:-

"ይህ የእግዚአብሔር ሕግ መጽሐፍ ነው፤ እነዚህም ሕጎች ለብዙ ዓመታት ተረስተዋል፤ ለእግዚአብሔር የገባነውን ቃል አፍርሰናል፤ እርሱ የሚለን ምን እንደሆነ ማወቅ አለብን፤"

ኪልቅያስም "እስኪ ሕልዳናን እንጠይቃት" አለ፤ ሕልዳና የእግዚአብሔር ነቢይት የነበረችና በጥበበኛነቷም የታወቀች ነበረች፤ እነርሱም ወደ ቤቷ ወደ ከተማ ሮጠው "ምንድን ነው የሚለው? ምን እናድርግ?" ብለው ጠየቋት፤ ሕልዳናም፣ እግዚአብሔር የሚለው እንዲህ ነው፤ "ሕዝቤ እምቢተኞች ሆነዋል፤ ምስሎችን አምልከዋል፤ ስለዚህ ይቀጣሉ፤ ዳሩ ግን ንጉሡ ለእኔ ታማኝ ስለሆነ በእርሱ ጊዜ አልቀጣቸውም" ይላል አለች።

ንጉሥ ኢዮስያስም ለመሪዎቹና ለሕዝቡ ሁሉ ላከ ባቸው፤ እነርሱም ከቤተ መቅደሱ ውጭ በተሰበሰቡ ጊዜ የሕጉን መጽሐፍ ጮክ ብሎ አነበበላቸው። ሕዝቡም ሁሉ ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ ቃል ገቡ፤ ከዚያም ኢዮስያስ ታላቅ የጽዳት ዘመቻ ጀመረና ሕዝቡ ያመለኩአቸውን የበዓልንና የሌሎችን አማልክት ምስሎች አስወገደ።

የእንጨት ምስሎቹን አቃጠለ፤ የአማልክቱንና የአጋን ንትን መሰዊያዎች አፈራረሰ፤ በሄኖም ሸለቆ ሕዝቡ ልጆቻ ቸውን ሞሎክ ለተባለ አምላክ የሚቃጠል መስዋዕት ያቀር ቡበት የነበረውን ቦታ ደመሰሰ፤ ፀሐይን ለማምለክ የሚጠ ቀሙበትን ሠረገላ አቃጠለ፤

በመላው ግዛቱ የቀደሙት የይሁዳ ነገሥታት ያቆሙ አቸው የአህዛብ የማምለኪያ ቦታዎች ተደመሰሱ። የበዓል ካህናት፣ ጠንቋዮችና አስማተኞች ሁሉ ከአገር እንዲወጡ ተደረገ። ኢዮስያስም፣

"የእግዚአብሔር ሕዝብ ከግብፅ አገር ሲወጡ እንዳደ ረጉት አሁን የፋሲካን በዓል ማክበር እንችላለን" አለ።



ለብዙ መቶ ዓመታት የዚህ ዓይነት ያፋሲካ በዓል ተከብሮ አያውቅም ነበር። በሺህ የሚቆጠሩ በጎች፣ ጠቦቶች፣ ፍየሎችና በሬዎች ታርደው ተጠበሱ። እያንዳንዱም የቤተሰብ ቡድን ድግሡን በአንድነት በሉ።

በዓሉም ለሰባት ቀናት ቆየ። ሰዎቹም እግዚአብሔርን አመለኩ። ንጉሥ ኢዮስያስ እግዚአብሔርን ከልቡ ይወድ ነበር፤ ከዚያም በፊትና ከዚያም በኋላ እንደ እርሱ ያለ ንጉሥ አልነበረም፤ ዳሩ ግን ኢዮስያስ በጦርነት ሲሞት ሕዝቡ እንደገና ወደ ቀድሞው መንገዳቸው ተመለሱ፤ ንጉሡ ያደረገው ሁሉ የጠቀመው ነገር ቢኖር የእግዚአብ ሔርን ቅጣት ማዘግየቱ ብቻ ነው።

# ኤርምያስና የኢየሩሳሌም ውድቀት

ኤርምያስ

እግዚአብሔር ኤርምያስን ለነቢይነት ሲጠራው ኢዮስያስ ገና የይሁዳ ንጉሥ ነበር። ኤርምያስ ወጣትና ዓይነ አፋር ነበር እንጂ በሕዝብ ፊት ቆሞ ንግግር ለማድረግ የሚችል ዓይነት ሰው አለነበረም። እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፦

"በእናትህ ማህፀን ሳለህ ነቢይ እንድትሆንልኝ መርጬሃለሁ፤ አትፍራ፤ አንተ ራስህን ከምታውቀው የበለጠ እኔ አውቅሃለሁ፤ የምትናገረውንም እኔ እሰጥሃለሁ፤ ከክፉም እጠብቅሃለሁ።"

ኤርምያስ በዚህ ጊዜ ምንም ምርጫ አልነበረውም፤ የእግዚአብሔር መልእክት ልክ እንደ እሳት ስለነበረ ካል ታዘዘለት የሚያቃጥለው ሆኖ ታየው፤ ስለዚህ መናገር ነበረበት።

እርሱ የኖረው በአስቸጋሪ ጊዜ ነበር፤ ትንሿ የይሁዳ ግዛት የሰሜኑና የደቡቡ ታላላቅ መንግሥታት ለበለጠ ሥልጣን በሚፋጩበት ፉክክር መካከል ነበረች፤ ንጉሡ ኢዮስያስ የአሦር ንጉሥ ባቢሎናውያንን ለማባረር በሚያ ደርገው ጦርነት ለመርዳት የግብፅ ንጉሥ በአገሩ ላይ እንዳያልፍ ሲዋጋ በጦርነት ሞተ።







ከአራት ዓመታት በኋላ ባቢሎናዊው ናቡከደነፆር ታላቅ የውጊያ ድል አገኘ። ግብፅን አሸንፎ ይሁዳን ተቆጣ ጠረ፤ በዚህ ጊዜ ሁሉ ኤርምያስ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ካልተመለሱ ስለሚደርስባቸው አሰቃቂ ነገር በማስጠንቀቅ እግዚአብሔር የሚለውን ለሕዝቡ በታማኝነት ይናገር ነበር። ዳሩ ግን ምንም ልዩነት አላመጣም፤ ሕዝቡ ልክ እንደ ቀድሞው ምስሎችን ያመልኩ ነበር፤ ኤርምያስን ማንም ጉዳይ ያለው አልነበረም፤ እርሱም ብዙ ስለ መቅሰ ፍት ሲያወራ መቀለጃና መሳለቂያ አደረጉት፤ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ቃል ጆሮአቸውን ደፍነው የሚመጣባቸ ውንም እንዳያዩ ዓይናቸው ተሸፍኖ ነበር።

ኤርምያስ ቃሉን ለማስተላለፍ በምስል ይጠቀም ነበር፤ ወደ ሸክላ ሠሪ ቤት ሄደና ሲሠራ ይመለከት ጀመር፤ መንኩራኩሩ ሲሽከረከር ሸክላ ሠሪው ጭቃውን የማሰሮና የጆግ ቅርጽ ይሰጠው ነበር። አንዳንድ ጊዜም ይበላሽበት ነበር። በዚህ ጊዜ የተሠራውን ጨፍልቆ እንደገና ይሠራው ነበር። እግዚአብሔርም ለኤርምያስ እንዲህ አለው፦

"ጭቃው በሸክላ ሠሪው እጅ እንደሆነ ሁሉ የእስራኤል ሕዝቦች በእጄ ውስጥ ናቸው፣ የማይሰሙኝ ከሆነ አፍርሼ እንደገና ልሠራቸው መብት አለኝ፤ መንገዳቸውን ቀይረው የማይገባውን ነገር መተው አለባቸው።"

ኤርምያስ ለሕዝቡ ቢናገርም አሁንም ሊሰሙት አልፈለጉም። በሌላ ቀን ደግሞ ኤርምያስ በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት ቆመ፤ እንዲህም አለ፦

"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እኔን ካልሰማችሁና ትእዛዛቴን ካልጠበቃችሁ ቤተ መቅደሱንና ኢየሩሳሌምን አጠፋለሁ።"

ካህናቱም መታገስ አልቻሉም፤ ኤርምያስንም ዳግመኛ ወደ ቤተ መቅደስ አጠገብ እንዳይደርስ ከለከሉት፤ ታስሮም ተደበደበ፤

ዳሩ ግን እግዚአብሔርን ማንም ዝም ሊያሰኘው አይ ችልም! ኤርምያስም የእግዚአብሔርን መልእክት በአፉ መናገር ቢከለከልም መጻፍ ግን ይችል ነበር። መናገር የሚፈልገውን ሁሉ በረጅም ብራና ጻፈው። /በዚያን ጊዜ መጻሕፍት ወይም የመጻፊያ ደብተር አልነበረም/ ለንጉሡም በተነበበለት ጊዜ ንጉሡ በጣም ተናደደና ብራናውን በእሳት ውስጥ ጣለው፤ ይህም ሊሠራ አልቻለም፤ ኤርም ያስ እንደገና ሁሉንም ጻፈው። ኤርምያስም፣ "የእግዚአ ብሔር ቃል እንደ እሳት ነው፤ ልታጠፉት አትችሉም፤ ደግሞም ዓለቱን እንደሚያደቅ መዶሻ ነው" አለ።





የይሁዳም ንጉሥ ለናቡከደነፆር ቀረጥ አልከፍልም አለ፤ አመፅም ባካሄደ ጊዜ ዙፋኑን አጣ!

የናቡከደነፆር ሠራዊት ወደ ኢየሩሳሌም መጡና ከሌሎች በሺህ ከሚቆጠሩ ምርኮኞች ጋር ወደ ባቢሎን ወሰዱት፤ /በእነርሱም መካከል ሕዝቅኤል የሚባል ወጣት ነበረ። ዳንኤል ከጥቂት ዓመታት በፊት ተይዞ ሄዶ ነበር/

ሴዴቅያስ የመጨረሻው የይሁዳ ንጉሥ በመሆን ነገሠ፤ ዳሩ ግን አሁንም የእግዚአብሔር ሰዎች ካለፈው ስህተት አልተማሩም፤ ኤርምያስም እንዲህ አለ፡–

"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ ለባቢሎናውያን ተገዙ፤ ያለበለዚያ ያጠፉአችኋል፤ የማይጠቅሙ ምስሎችን አታም ልኩ፤ ካአሁኑ ወደ ሕያው አምላክ ተመለሱ፤ ጊዜው አጭር ነው።"

ኤርምያስም በኢየሩሳሌም የተናቀ ሰው ሆነ፤ ሕዝቡም እየጮኹ "ከሀዲ ነህ፤! ከሀዲ ነህ! የጠላት ቅጥረኛ ነህ" አሉት። ነቢዩንም ያዙትና ከደበደቡት በኋላ ወደ ወህኒ ቤት ጣሉት። ሴዴቅያስም ለአሥር ዓመታት ከነገሠ በኋላ እርሱም አመፀ፤ ናቡከደነፆርም መጥቶ ኢየሩሳ ሌምን ከበባት፤ ኤርምያስም ለሕዝቡ፣





"ነፍሳችሁን ለማዳን ከፈለጋችሁ እጃችሁን ስጡ፤
እግዚአብሔር ይህችን ከተማ ለባቢሎናውያን ይሰ
ጣል" አላቸው፤

መሪዎቹም ተናደዱ። ኤርምያስንም በጥልቅ ጉድጓድ
ውስጥ ወረወሩት፤ ከጭቃም በስተቀር ምንም ውሀ አልነበ
ረበትም፤ በዚያም በረሃብ እንዲሞት ጥለውት ሄዱ፤ ዳሩ
ግን አቤሜሌክ የተባለ በቤተ መንግሥት የሚሠራ የኢት
ዮጵያ ሰው ወደ ንጉሡ ሄደ፤ የነቢዩን ነፍስ እንዲያድን
ለመነው፤ ከዚያም እርሱና ሌሎች ሦስት ሰዎች ገመድ
አወረዱና ኤርምያስን አወጡት፤ ንጉሡም ሴዴቅያስ
ከነቢዩ ጋር በምስጢር ተነጋገረ፤ እርሱም፣ "ምን ላድርግ"
ሲል ጠየቀው፤ ኤርምያስም መልሶ፦ "ከተማይቱ ትጠፋ
ለችና እጅህን ስጥ" አለው።



ዳሩ ግን ንጉሡ ኤርምያስ ያለውን በማድረግ ፈንታ
ሕይወቱን ለማዳን ሸሸ፤ ባቢሎናውያን ግን ያዙትና ሁለት
ልጆቹን ገድለው የእርሱንም ዓይኖች አሳወሩ። የከተማይ
ቱንም ግንብ ሰብረው ቤተ መንግሥቱንና ቤተ መቅደሱን
እንዲሁም ቤቶቹን ሁሉ አፍርሰው በእሳት አቃጠሏቸው።
የቤተመቅደሱን ንብረቶች ሁሉ ዘረፉ፤ ሕዝቡንም ማርከው
ከብዙ መቶ ዓመት በፊት እግዚአብሔር አብርሃምን ወደ
ጠራበት ወደ ባቢሎን አገር ባሪያዎች እንዲሆኑላቸው
ይዘዋቸው ሄዱ። ኤርምያስም በዚያ ከቀሩት ከጥቂት
ሰዎች ጋር ቀረ፤ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ሁሉ ችላ ተብሎ
ነበር። እግዚአብሔርም አመፀኞቹን ሕዝብ ቀጣቸው፤ ዳሩ
ግን እነርሱን መውደዱን አልተወም ነበር።

ኤርምያስም ለግዞተኞቹ የማጽናኛ ደብዳቤ ጻፈ፤
እንዲህም አለ፦ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ አንድ
ቀን ወደ አገራችሁ እመልሳችኋለሁ። በምርኮ አገር
ሳላችሁ እኔን መውደድን ትማራላችሁ፤ ትእዛዛቴ
ንም በማሰብ ትክክል የሆነውን ነገር ታውቃላችሁ፤
ከግዞት አገር ወደ ገዛ አገራችሁ የምትመለሱበትን
ቀን ጠብቁ።"



# ሕዝቅኤልና ግዞተኞቹ

ሕዝቅኤል



ሕዝቅኤል አገሩን እጅግ ናፈቀ፤ ለብዙ ዓመታት፣ ሠላሳ ዓመት ሲሆነው የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በክህነት የሚያገለግልበትን ጊዜ ይጠብቅ ነበር።

ዳሩ ግን በብዙ መቶ ኪሎሜትር ከአገሩ ርቆ ይቀመጥ ነበር። ሕዝቅኤል ንጉሡ ናቡከደነፆር ይሁዳን በተቆጣጠረ ጊዜ ከይሁዳ ኮረብቶችና ሸለቆዎች ከማረካቸው ከአሥር ሺህ ምርኮኞች መካከል አንዱ ነበር፤

ሕዝቅኤል ከአገሩ ከወጣ አምስት ዓመታት አልፈዋል፤ እርሱም፣ "ቤተ መቅደሱ እንዴት ይርቃል፤ እግዚአብሔርስ እንዴት ሩቅ ነው" ብሎ አሰበ። እርሱም፣ ድንገተኛ አውሎ ነፋስ ባየ ጊዜ ቀና ብሎ ተመለከተ፤





ማዕበል ይሆንን? ያልተለመደ ጥቁር ደመና ወደ እርሱ መጣ፤ መብረቅም ነበረበት፤ ወደ እርሱ በጣም እየቀረበ ሲመጣ ሕዝቅኤል ወደ መካከሉ ተመለከተ፤ በቤተ መቅደሱ ውስጥ የእግዚአብሔር ሕጎች ያሉበትን ታቦት እንደ ሚጠብቁት እንስሶች ያሉ ክንፎቻቸውን አጋጥመው የሚበሩ፤ መንኮራኩሮቻቸውም ወዲያና ወዲህ የሚዘዋወሩ፣ ዓይኖቻቸውም ወደ ሁሉም አቅጣጫ የሚዞሩ አራት እንስሶች ነበሩ። ከጨለማው በላይ ሕዝቅኤል ከሰማይ ይልቅ የጠራ፣ በቀስተ ደመና ቀለሞች የተዋበ ብሩህ ሰማያዊ ሕዋ አየ።

ከዚያም ምድርን የሚያንቀጠቅጥ ድምፅ ሰማ፤ ሕዝቅኤልም ተንቀጠቀጠ፤ በዚያ በባቢሎን አገር እግዚአብሔር ራሱ ይሆንን?

ድምፁም እንዲህ አለ፣ "የሰው ልጅ ሆይ፣ በግዞት ወዳሉት ሕዝቤ እልክሃለሁ፤ በእኔ ላይ አምፀውብኛል፤ መንገዳቸውን እንዲያሻሽሉ ንገራቸው፤ እኔም የምትናገረውን ቃል እሰጥሃለሁ፤"

ከዚያም በኋላ ራእዩ ጠፋ፤ ሕዝቅኤልም እየተንቀጠቀጠ ወደ ሠፈሩ ተመለሰ፤ እግዚአብሔር እዚህም ነበረ፤ በእርግጥ እርሱ በሁሉም ቦታ አለ።

እርሱም በቤተ መቅደስ ሳይሆን በግዞተኞቹ ሠፈር የተለየ ሥራ ሰጠው፤ እግዚአብሔር ከዚያም በኋላ ለሕዝቅኤል ብዙ አስፈሪና አስደናቂ የሆኑ ራእዮችን አሳየው፤ እርሱም ናቡከደነፆር እንዴት ወደ ይሁዳ እንደገና እንደሚመጣና ኢየሩሳሌምን አሸንፎ ቤተ መቅደሱን እንደሚያጠፋ ለሕዝቅኤል አሳየው፤ ሕዝቅኤልም ይህን ለሌሎች በቃላት ብቻ ሳይሆን ማንም እንዳይረሳው ሁኔታውን በግልጽ በድርጊት አመለከተ፤ እንዲህም አለ፡-

"ይህ የእኛ ጥፋት ነው፤ እግዚአብሔር ብዙ ፍቅርንና መልካምን ነገሮች ካደረገልን በኋላ ትእዛዛቱን አፈረስን፤ ስህተትን ሠራን፤ እንዲያውም ጣዖታትን አመለክን፤ ስለዚህ ይህ ቅጣታችን ነው::

ከዚያም ልክ ሕዝቅኤል እንደተናገረው ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ማርኮ ከተማይቱንና ቤተ መቅደሱን እንዳጠፋ ሰሙ፤ ግዞተኞቹም ተስፋ ቆረጡ፤ እነርሱም "አሁን ምንም ተስፋ የለንም፤እግዚአብሔር ፈጽሞ ትቶናል" አሉ::

ሕዝቅኤልም የተቻለውን ያህል አጽናናቸው፤ "የምትሉት እውነት አይደለም፤ እግዚአብሔር አሁንም ይወደናል" አላቸው፤ ሰዎቹ ግን ሊጽናኑ አልቻሉም፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል የተለየ አዲስ ራእይ ሰጠው፤ እርሱም በሸለቆው ውስጥ ቆሞ ነበር፤ በዙሪያውም የደረቁ የአጽም አጥንቶች ነበሩ፤ እግዚአብሔርም "ለእነዚህ አጥንቶች ሕይወትና ትንፋሽ ያላቸው ሰዎች እንደማደርጋቸው ንገራቸው" አለው፤ ሕዝቅኤልም እንደታዘዘው አደረገ፤ የእግዚአብሔርንም ቃል ሲናገር ተአምር ሆነ፤ አጥንት ከአጥንት ጋር ተገጣጠመ፤ አጽሞቹም ቆሙ፤ ሥጋና ደምም ያላቸው አካሎች ሆኑ፤ ደግሞም እግዚአብሔር በቃሉ አማካይነት የሕይወትን ትንፋሽ ሰጣቸው::

እግዚአብሔርም ለሕዝቅኤል እንዲህ አለው:-"ለሕዝቤ የማደርገውን ንገራቸው፤ የሕይወትን እስትንፋስ ሰጥቼ እንደገና አንድ ሕዝብ አደርጋቸዋለሁ፤ ወደ አገራቸውም እመልሳቸዋለሁ፤ እነርሱም በዚያን ጊዜ ለእኔ ታማኝ ይሆናሉ፤ ይህም የተስፋ ቃሌ መሆኑን ንገራቸው፤ እኔም ቃሌን የምጠብቅ መሆኔን ይወቁ::"





# የዳንኤል ታሪክ

ዳንኤል 1 – 6

ዳንኤል ናቡከደነፆር ከቤቱ ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን ማርኮ ሲወስደው ገና ልጅ ነበር::

በዚያም ከደረሱ በኋላ ወዲያውኑ ዳንኤልና ሦስት ጓደኞቹ ለተለየ ሥልጠና ተመረጡ፤ እነርሱም በይሁዳ እጅግ ምርጥ ከሆኑት ቤተሰቦች መካከል የሆኑ መልከ መልካም ልጆች ነበሩ፤ ብሩህ አዕምሮም ነበራቸው! ንጉሡም እንዲህ አለ:- "በትምህርት ቤቴ አስገቡአቸውና ቋንቋችንን አስተምሩአቸው፤ ጽሑፎችንንም ያጥኑና ከታላላቆቹ ፈላስፎቻችን ይማሩ፤ እኔም የተመረጠ ምግብንና የወይን ጠጅን እንዲቀርብላቸው አደርጋለሁ፤ ሥልጡንና ብልህ እንዲሆኑ እፈልጋለሁ::"

እግዚአብሔር ግን ለሕዝቡ ስለሚበሉና ስለማይበሉ ነገሮች የተለየ ሕግ ሰጥቶአቸው ነበር፤ ዳንኤልና ጓደኞቹም የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለመጠበቅ ፈለጉ፤ እነርሱም ኃላፊያቸው ሆኖ ለተመደበው ጠባቂ ንጉሡ በሚያቀርበው ምግብ ፈንታ ቅጠላ ቅጠል እንዲበሉና ውሀ ብቻ እንዲጠጡ ለመኑት:: ጠባቂውም:- "ብትከሱና ብትታመሙ በሕይወቴ ላይ ታስፈርዱብኛላችሁ፤ ለማንኛውም ለአሥር ቀናት ያህል ሞክሩና ከዚያ በኋላ እናያለን" አላቸው:: ከአሥር ቀን በኋላ ዳንኤልና ጓደኞቹ ከቤተ መንግሥት የታዘዘውን ምግብ ከበሉት ወጣቶች ይልቅ ብቁና ጠንካሮች ሆነው ተገኙ፤ በትምህርታቸውም የተሻሉ ሆነው ተገኙ፤ ስለዚህ ጠባቂው በራሳቸው ምግብ እንዲቀጥሉ አደረጋቸው::

በሦስተኛውም ዓመት እነርሱ ሽልማቶቹን ሁሉ ወሰዱ፤ ከባቢሎንም ጠቢባን ሁሉ በልጠው ተገኙ:: ስለዚህ ንጉሡ የቤተ መንግሥቱ አባሎች አደረጋቸው::

## ሕልሙ

አንድ ሌሊት ንጉሡ በጣም የሚያስፈራ ሕልም አየ፤ በድንጋጤም ነቃና ወደ ጠቢባኑ መልእክት ላከ፤

እርሱም "ሕልሙን አላስታወስሁትም፤ እናንተ ሕልሙንና ትርጉሙን ንገሩኝ" አላቸው፤ ጠቢባኑም ይህን ሲሰሙ በጣም ተጨነቁ፤ እነርሱ መተርጎም ይችሉ ነበር፤ ዳሩ ግን መጀመሪያ ሕልሙን ማወቅ ነበረባቸው፤

እነርሱም፣ "ሕልሙን ብትነግረን እንተረጉምልሃለን" አሉት፤ ንጉሡም እጅግ ተቆጣ፤ እርሱም፣ "ሰውነታችሁን እቦጫጭቀዋለሁ" ብሎ ጮኸ፤ ሰዎቹም "አንተ የጠየቅኸውን ማንም ሊፈጽመው አይችልም" አሉት፤ከዚያም በኋላ ንጉሡ በባቢሎን ያሉ ጠቢባን ሁሉ እንዲገደሉ ወታደሮቹን አዘዘ:: እነርሱም ዳንኤልን ሊይዙት መጡ፤ እርሱም፣ "ለንጉሡ እንድናገር ይፈቀድልኝ፤ ሕልሙንና ትርጉምን እነግረዋለሁ" አለ::



ዳንኤልም ለጓደኞቹ ነገራቸውና ምስጢሩን እንዲገልጽላቸው ሁሉም ወደእግዚአብሔር ጸለዩ:: እግዚአብሔርም ሕልሙንና ትርጉሙን ለዳንኤል ገለጸለት፤ ንጉሡም የዳንኤልን አምላክ ማክበር ጀመረ፤ እርሱም፣ "የእናንተ አምላክ እንደዚህ ምስጢርን የሚገልጥ ከሆነ የአማልክት አምላክ ነው" አለ::

## የወርቁ ምስል

ዳሩ ግን ከጥቂት ዓመታት በኋላ ናቡከደነፆር ለአንደኛው አምላኩ ታላቅ የወርቅ ምስል አቆመ፤ ከፍታውም ዘጠና ጫማ ነበረ፤ ለምርቃቱም ታላላቅ ሰዎች፣ ገዢዎች፣ አማካሪዎችና ዳኞች ሁሉ ተጠሩ፤ የታወቁት ሙዚቀኞች ዋሽንታቸውን፣ መሰንቆአቸውንና በገናቸውን ይዘው ተገኙ::

ንጉሡም፣ "የሙዚቃው ድምፅ ሲሰማ ሰው ሁሉ ወድቆ ለዚህ አምላክ መስገድ አለበት፤ ያለበለዚያ ግን በጋለው እሳት ውስጥ ይቃጠላል" አለ:: ከሦስቱ የዳንኤል ጓደኞች በስተቀር ሁሉም ሰዎች እንደታዘዙት አደረጉ፤ /ዳንኤል ራሱ ግን በቤተ መንግሥት ቀርቶ ነበር/ እነርሱም ለንጉሡ፣



"አምላካችን ከእሳቱ ሊያድነን ይችላል፤ ለእርሱ የሚያቅተው ነገር የለም:: ዳሩግን ባያድነን እንኳን ሌላ አምላክ አናመልክም፤ ለምስሉም አንሰግድም" አሉት:: ንጉሡም እጅግ ከመናደዱ የተነሣ እሳቱን ከሌላው ጊዜ ሰባት እጥፍ የበለጠ እንዲያነድዱት አደረገ፤ ሰዎቹም እጅና እግራቸውን ታስረው በውስጡ ተጣሉ::

ከዚያም ንጉሡ በመገረም ዓይኖቹን አሸ፤ በእሳቱም ውስጥ የሚመላለሱ ሦስት ሳይሆን አራት ሰዎችን ተመለከተ፤ እርሱም ". . . አራተኛውም አምላክን ይመስላል" አለ፤ እርሱም "ኑ ውጡ" ብሎ ሲጣራ ሦስቱ ጓደኛሞች ወጡ! አሁን እሥራታቸው ተፈትቶ ነበር፤ ዳሩ ግን እሳቱ ልብሳቸውን ወይም ከራሳቸው አንዲት ፀጉር እንኳን አላቃጠለም፤ ጭስ ጭስ እንኳን አልሸተቱም፤ ንጉሡም፣ "ይህን የሚያደርግ በእርግጥ ታላቅ አምላክ ነው፤ በእነዚህ ሰዎች አምላክ ላይ ማንም ሰው ቃል እንዳይናገር!" አለ::



## የብልጣሶር ድግሥ

ዓመታት አለፉ፤ ናቡከደነፆር ሞተና ብልጣሶር የባቢሎን ንጉሥ ሆነ፤ እርሱም በሺህ ለሚቆጠሩ ታላላቅ ሰዎች ታላቅ ግብዣ አደረገ፤ ከሚያስፈልገውም በላይ የወይን ጠጅ ጠጣ፤ ብልፅግናውንም ለማሳየት ፈለገ፤ እርሱም፣ "ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ያመጣቸውን የወርቅና የብር ዋንጫዎችና ሳህኖች አምጡልኝ" ብሎ ጮኸ:: አሽከሮቹም ለመታዘዝ ተሯሯጡ ከዚያም ንጉሡና ታላላቆቹ ሰዎች በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ዋንጫዎች ከብረት፣ ከእንጨትና ከድንጋይ በተሠሩ አማልክቶቻቸው ስም ጠጡባቸው፤ እነርሱም እየጮኹና እየሳቁ ሲተራመሱ



የሰው እጅ በአየሩ ውስጥ ታየ፤ እጅ ብቻ ነበረ፤ እርሱም በግድግዳው ላይ መጻፍ ጀመረ፤ እንግዶቹ ፀጥ አሉ፣ የንጉሡም አካል ነጭ መሰለ፤ እርሱም፣ "ጠቢባኖችን ጥሩልኝ የዚህን ትርጉም የሚነግረኝ ጠቅላይ ሚኒስቴር ይሆናል" ሲል ጮኸ፤ ዳሩ ግን ማንም ጥበበኛ የጽሑፉን ፍቺ ያወቀ አልነበረም::

ከዚያም ንግሥቲቱ ዳንኤል የናቡከደነፆርን ሕልም እንደፈታለት አስታወሰች፤ ስለዚህ ዳንኤል እንዲመጣ ተላከበት፤ ንጉሡም፣ "የዚህን ፍቺ ብትነግረኝ ሀብትንና ሥልጣንን አሰጥሃለሁ" አለው፤ ዳንኤልም መለሰ፣

"ስጦታህ ለአንተ ይሁንልህ፤ የምነግርህ የሚያስደስትህ ነገር አይደለም፤ ከቤተ መቅደሱ በመጡት ዋንጫዎች በአማልክቶችህ ስም በመጠጣትህ እግዚአብሔርን አዋርደሃል፤ እግዚአብሔር የመንግሥትህ ቀናት ተቆጥረዋል፤ ለሜዶንና ለፋርስም ይሰጣል ይልሃል" አለው::

በዚያው ሌሊት ብልጣሶር ተገደለ፤ የሜዶንና የፋርስ ሰዎች ባቢሎንን ማርከው አለቃቸውን ዳርዮስን በዙፋኑ ላይ አስቀመጡ::

## ዳንኤልን ለመግደል የተደረገው አድማ


ዳርዮስ ዳንኤልን ከሦስቱ ዋና ዋና ገዢዎች አንዱ አደረገው፤ ዳንኤል አሁን በጣም አርጅቶ ነበር፤ ዳሩ ግን ንጉሡን በጨዋነትና በታማኝነት ያገለግል ነበር:: እንደ ልማዱም በቀን ሦስት ጊዜ ሳያቋርጥ ፊቱን ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ በማድረግ እየተንበረከከ ወደ አምላኩ ይጸልይ ነበር፤ ሌሎቹ ሹማምንቶች በዳንኤል ስለ ቀኑበት ሊገድሉት አድማ አደረጉ፤ በምን ሊከስሱት ይችሉ ይሆን፤ በሃይማኖቱ በኩል ካልሆነ በስተቀር አንድም ጥፋት አልተገኘበትም:: ስለዚህ ንጉሡ አንድ የማይለወጥ ሕግ እንዲያወጣ አግባቡት:: ለሠላሳ ቀን ማንም ሰው ለማንኛውም አምላክ ልመና እንዳያቀርብ፣ ይህንን ሕግ የጣሰ ወደ አንበሶች ጉድጓድ ይጣላል::

ዳንኤል ንጉሡ ትእዛዙን እንደፈረመበት አወቀ፤ ዳሩ ግን አሁንም በግልጽ ወደአምላኩ በቀን ሦስት ጊዜ ጸለየ፤ የዳንኤልም ጠላቶች ተደሰቱ፤ አድማቸው ስመረላቸው:: ለንጉሡም ሊነግሩ ሮጡ፤ ዳርዮስም ተቆጣ ተበሳጨ፤ በጣም ቢያስብም ዳንኤልን ለማዳን መንገድ አጣ፤ በዚያ ሌሊት ዳንኤል የተራቡ አንበሶች በሞሉበት በጥልቅ ጉድጓድ ተጣለ፤ ንጉሡ እራቱን መብላት አልቻለም፤ የመንግሥቱንም ሙዚቀኞችና አስተናጋጆች አባረረ፤ ትንሽ እንኳን እንቅልፍ አልተኛም፤ ገና ትንሽ ሊነጋጋ ሲል ወደ አንበሶቹ ጉድጓድ ሮጠ::



እርሱም፣ "ዳንኤል" ብሎ ጠራና "አምላክህ ከአንበሶቹ ሊያድንህ ችሎአልን?" አለው፤ መልስም አልጠበቀም፤ ዳሩ ግን እስኪገረም ድረስ ዳንኤል መልስ ሰጠ፤ "አዎን ንጉሥ ሆይ፣ አንበሶቹ አልጎዱኝም፤ ምክንያቱም ጥፋት እንደ ሌለብኝ እግዚአብሔር አውቆአል፤ አንተንም አልበደ ልኩም፤" ዳርዮስም "በፍጥነት ልቀቁት፤ እርሱን የከሰ ሱትንም ሰዎች ወደ አንበሶቹ ጣሏቸው!" ብሎ ጮኸ::

ስለዚህ ዳንኤል በአምላኩ ስለ ታመነ ያለ አንዳች ጉዳት ወጣ፤ ንጉሥ ዳርዮስም አዲስ ትእዛዝ አወጣ፤ እንዲህ የሚል:- "በግዛቴ ውስጥ ማንኛውም ሰው ዳንኤ ልን ከአንበሶች አፍ ላዳነው አምላክ እንዲንቀጠቀጥና እርሱንም ብቻ እንዲፈራ አዝዣለሁ፤ እርሱ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም የሚኖር አምላክ ነው፤"



# እንደገና በኢየሩሳሌም!

*ዕዝራ፣ ነህምያ*

በዚህ ጊዜ የባቢሎን ገዢ የሆነው የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ
መልካም ሰው ነበር፤ እርሱም አዋጅ አስነገረ፤

"እግዚአብሔር ሕዝቡን አይሁዳውያንን /ይህ ስም
የተሰጣቸው ከይሁዳ ስለመጡ ነበር/ በኢየሩሳሌም ያለውን
ቤተ መቅደስ መልሰው እንዲሠሩ እንድለቃቸው ነግሮ
ኛል፤ ሁሉም ለመሄድ ይችላሉ፤ ንጉሡም ናቡከደነፆር ቤተ
መቅደሱን ከማፍረሱ በፊት ከውስጡ የወሰዳቸውን
ንብረቶች ሁሉ እመልሳለሁ።"

በዚያን ቀን የባቢሎን ጎዳናዎች በደስታ ጮኸት አስ
ተጋቡ! "ግዞቱ አለፈ፤ እግዚአብሔር ቃሉን ጠብቆአል፤
ወደቤታችን መሄድ እንችላለን!" አሉ።

የእግዚአብሔር ሰዎች በገዛ አገራቸው እንደገና እር
ሱን ሊያመልኩት ናፍቀው ነበር፤ በግዞት የኖሩባቸው
ዓመታት ወደ ራሳቸው ተመልሰው እግዚአብሔርን
እንዲወዱትና እንዲታዘዙለት ትምህርት ሰጣቸው።

አርባ ሁለት ሺህ ሰዎች ከአገልጋዮቻቸውና ከንብ
ረታቸው ጋር ምድረ በዳውን ሊሻገሩ ጉዞ ጀመሩ።
ፈረሶቻቸው በቅሎዎቻቸውና ግመሎቻቸው ዕቃዎቻቸ
ውንና ለጉዞው የሚሆናቸውን ምግብ ተጭነው ነበር።
በመጨረሻም ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ የመጀመሪያው
ሃሳባቸው የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ሥራ ለመጀመር
ነበር። ለሥራውም የሚሆን የወርቅና የብር ስጦታ ጎረፈ፤
በታላቅ ጉጉት የቤተ መቅደሱን መሠረት ጣሉ። አይሁዳ
ውያኑም በግዞት በነበሩበት ዘመን በምድሩ ይኖሩ የነበ
ሩት ሰዎችም እገዛ አደረጉ፤ እነርሱም "እኛም እግዚአብ
ሔርን እናመልካለን"አሉ። ዳሩግን አይሁዶቹ ለብቻቸው
ለመሥራት ፈለጉ፤ ከዚያም በኋላ የአገሩ ሰዎች ችግር
ፈጠሩ።





ሥራው ለረጅም ጊዜ ቀጠለና ተቋረጠ። የእግዚአብ
ሔር ነቢያት ተናገሩ፤ እንዲህም አሉ:- "በጣም አሳፋሪ
ነው፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ፈርሶ እያለ እናንተ
የራሳችሁን ቤት ትሠራላችሁ።"

ከዚያም አይሁዶቹ እንደገና መሥራት ጀመሩ፤ በመጨ
ረሻም የቤተመቅደሱ ሥራ ተፈጸመ። በታላቅነቱ የንጉሥ
ሰሎሞንን ቤተ መቅደስ የሚያህል አልነበረም፤ ቢሆንም
እንደዚያው ጥሩ ሥራ ነበር።

## ምሁሩ ዕዝራ

ዓመታት አለፉ፤ በዚያው በባቢሎን የእግዚአብሔርን ሕግ የሚያውቅ ዕዝራ የተባለ ምሁር ይጨነቅ ነበር፤ በእስራ ኤል ያሉት አይሁዶች የእግዚአብሔርን ሕግ ያወቁ አይመስልም፤ እርሱም ሄዶ እንዲያስተምራቸው ንጉሡን ጠየቀ፤ ንጉሡም ለዕዝራ ታላቅ አክብሮት ነበረው፤ እር ሱም "መሄድ ትችላለህ፤ ከአንተም ጋር ሊሄዱ የሚፈል ጉትን ይዘህ ሂድ፤ እኔም ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ወርቅና ብር ሌላም የሚያስፈልግህን ነገር እሰጥሃለሁ" አለው፤ ዕዝራም እንዲህ ሲል አሰበ፡–

"ይህን ነገር በንጉሡ ልብ ያስቀመጠ እግዚአብሔር ነው፤ መንገዱ አደገኛ ነው፤ በመንገድ ዘራፊዎች ሊኖሩ ይችላሉ፤ እግዚአብሔር ግን ሊጠብቀን ይችላል፤ ንጉሡ ጠባቂ እንዲሰጠኝ አልጠይቅም፤"

እግዚአብሔርም ጠበቃቸው፤ በኢየሩሳሌም ዕዝራ ብዙ ነገሮች ተበላሽተው አገኘ። ሰዎቹ አማልክቶቻቸውን ይዘው የመጡ የውጭ አገር ሴቶችን አግብተው ነበር፤ ይኸ ከግዞቱ በፊት ችግር የፈጠረ ጉዳይ ነበር፤





## ገዢው ነህምያ

ቤተመቅደሱ ተሠራ፤ ከተማዋ ግን እንደፈረሰች ነበረች፣ አጥሩ ፈርሶና ተቃጥሎ ነበር። በፋርስ ቤተ መንግሥት ሳለ ነህምያ ይህን ዜና ሲሰማ አለቀሰ።

ነህምያ የፋርስ ንጉሥ የወይን ጠጅ አሳላፊ የሆነ የቤተ መንግሥት ታላቅ ሰው ነበር፤ እርሱም አይሁዳዊና እግዚአብሔርን የሚወድ፣ ለሕዝቡም የሚጠነቀቅ ሰው ነበረ። ለብዙም ቀናት ምግብ ሳይበላ ወደ እግዚአብሔር ይጸልይ ነበር፤ ፊቱ አዝኖ ስለነበር ንጉሡ አወቀበት፤ እርሱም "ችግርህ ምንድን ነው ብሎ?" ጠየቀው።

ነህምያም "ንጉሥ ሆይ ኢየሩሳሌም ፈርሳለች" አለው። ወዲያው ወደ እግዚአብሔር አስቸኳይ ጸሎት አደረገ። ቀጥሎም "እባክህ ሄጄ እንድሠራ ፍቀድልኝ" አለ።

እግዚአብሔርም የነህምያን ጸሎት መለሰ፤ ንጉሡም ነህምያ እንዲሄድ መፍቀድ ብቻ ሳይሆን በመንገድ ችግር እንዳይገጥመውና የሚያስፈልገውን እርዳታ ሁሉ እንዲያደ ርጉለት የአውራጃ ገዢዎቹን አዘዘለት።





ስለዚህ ነህምያ ኢየሩሳሌም ደረሰ፤ ቀኑ እስኪጨልም ጠበቀና በእንስሳ ላይ ተቀምጦ ከተማዋን እየዞረ አጥሮቹን ሁሉ ተመለከተ:: በማግሥቱ ከካህናቱና ከመሪዎቹ እንዲሁም ከሕዝቡ ሁሉ ጋር ተነጋገረ፤ እርሱም፣ "እነዚህ የፈረሱ አጥሮች የሚያሳፍሩን ናቸው፤ ተነስተን እንሥራ፤ እግዚአብሔርም ይረዳናል" አላቸው:: ደግሞም እግዚአብሔር ጸሎቱን እንዴት እንደመለሰለትና የፋርስ ንጉሥ ለመምጣት እንዴት እንደፈቀደለት ነገራቸው::

ነህምያም መጸለይንና መሥራትን የሚያውቅ ሰው ነበር፤ እርሱም የይሁዳ ገዢ ሆኖ ተሾመና ሰውን ሁሉ አስተባበረ፤ እያንዳንዱ ቤተሰብ በቤቱ አቅራቢያ ያለውን የከተማዋን አጥር ሠራ፤ ሥራቸውንም በመቀጠል እውነተኛ ሥራ እንዲሠራ ፈለጉ፤

ዳሩ ግን የአገሩ ሰዎች ፈሩ፤ ኢየሩሳሌም እንደገና የታጠረች ጠንካራ ከተማ እንድትሆን አልፈለጉም:: ሥራውም እንዲቆም ፈለጉ::

በመጀመሪያ በአይሁዶቹ ሠራተኞች ይቀልዱባቸው ጀመር፤ እያሾፉም "ምን ዓይነት አጥር ነው የምትሠሩት? ቀበሮ እንኳን ሊያፈርሰው ይችላል" አሏቸው::

አይሁዶቹ ግን ለሥራው በነበራቸው ጉጉት ዝም ብለው ሥራቸውን ቀጠሉ፤ አጥሩም ማደግ ጀመረ፤ ከዚያም ጠላቶቻቸው ጥቃት ለመሰንዘር አሰቡ:: ነህምያም እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ጸለየና ጠባቂ መደበ::





ግማሾቹ ሰዎች ሲሠሩ ሌሎቹ የጦር መሣሪያ ይዘው ቆሙ፤ ጠላቶቻቸውም ሌላ ታክቲክ አቀዱ፤ "እስኪ እንወያይ" አሏቸው:: ነህምያም መልሶ "ይህ ሥራ ታላቅ ሥራ ነው፤ ለመወያየት ጊዜ የለንም" አለ:: ከዚያም ነህምያ በንጉሡ ላይ ሊያምፅ እያቀደ ነው ብለን እንናገራለን ብለው ሊያስፈራሩአቸው ሞከሩ፤ ዳሩ ግን ሊያስፈራሩአቸው አልቻሉም::

በእግዚአብሔር እርዳታ ሥራው ተፈጸመ፤ ሥራውም ሃምሳ ሁለት ቀናት ፈጀ፤ ኢየሩሳሌምም እንደገና የምታኮራ ጠንካራና የተመሸገች ከተማ ሆነች::

አይሁዶቹም ታላቅ በዓል አደረጉ፤ በግንቡም አጥር ላይ እየተራመዱ በከተማው ዙሪያ እየዞሩ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ይጮኹና ይዘምሩ ነበር፤ ካህናቱ ጥሩምባ ይነፉ ነበር:: ሙዚቀኞቹም ይጫወቱ ነበር፤ ሁሉም ተደሰቱ::

ምሁሩ ዕዝራም የእግዚአብሔርን ሕግ ለሕዝቡ ጮክ ብሎ እያነበበ ሀሳቡንም ያብራራላቸው ነበር:: ሕዝቡም እግዚአብሔር ጥፋታቸውን ይቅር እንዲላቸው ጠየቁት:: እግዚአብሔርን ለመውደድና ትእዛዛቱንም ለመጠበቅ ቃል ገቡ::

ስለዚህ ገዢው ነህምያና ምሁሩ ዕዝራ ሕዝቡን እየመሩ የቀናውንም መንገድ አስተማሩአቸው::

አስቴር



የፋርስ ንጉሥ አርጤክስስ በዋና ከተማው በሱሳ ለሕዝቡ ሁሉ ታላቅ ግብዣ አደረገ፤ ግብዣውም በቤተ መንግሥቱ የአትክልት ሥፍራ ሆኖ ለሰባት ቀናት ቆየ፤ የወይን ጠጅም የሚጠጣው በወርቅ ዋንጫ ሆኖ ሰው ሁሉ የፈለገውን ያህል ይጠጣ ነበር።

በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ደግሞ ንግሥቲቱ አስጢን ለሴቶች ግብዣ አደረገች። በሰባተኛውም ቀን ንጉሡ በጣም ደስታ በተሰማው ጊዜ የንግሥቲቱን ቁንጅና ለማሳየት ፈለገ፤ አሽከሮቹንም "ንግሥት አስጢንን ወደዚህ አምጧት" አላቸው።

ዳሩ ግን ንግሥቲቱ አልመጣም አለች! ንጉሡም በእንግዶቹ ፊት እንዲያፍር አደረገችው። እርሱም በጣም ተቆጣ፤ ንጉሡም አማካሪዎቹን አስጠራ፤ እነርሱም "ሌሎች ሴቶች ይህን ከሰሙ በመላው ፋርስ ያሉ ሴቶች ለባሎቻቸው አይታዘዙም" አሉ።

የነበረው አማራጭ አንድ ብቻ ነበር፤ ንጉሡም "ንግሥት አስጢንን አባርሩልኝ፤ ሌላ ንግሥት እፈልጋለሁ" ሲል ትእዛዝ ሰጠ፤ ስለዚህ ሌላ ንግሥት ፍለጋ ተጀመረ።

በፋርስ ያሉ ቆንጆዎች ልጃገረዶች ሁሉ ወደ ቤተ መንግሥት ተላኩ፤ ለአንድ ዓመት ያህልም በንጉሡ የሴቶች ቤት ተቀመጡ፤ የሚበሉትም የተለየ ምግብ ሲሆን በየቀኑም ሽታው በሚጣፍጥ ዘይት ይታሹ ነበር።





ከዚያም ንጉሡ እያንዳንዳቸውን በየተራ ልኮ አስመጣቸው፤ ከሁሉም የበለጠች ቆንጆ ሆና የተገኘችው አይሁዳዊው መርዶክዮስ የሚያሳድጋት አስቴር የምትባለው ነበረች። እርስዋን ሁሉም ወደዷት፤ ንጉሡም ባየት ጊዜ ንግሥት እንድትሆነው መረጣት፤

ከዕለታት አንድ ቀን መርዶክዮስ በንጉሡ ላይ የግድያ አድማ መደረጉን ሰማ፤ ለአስቴርም ነገራት፤ ንጉሡም በጣም አመሰገነው፤ የመርዶክዮስንም ስም በቤተ መንግሥቱ መዝገብ ላይ አሠፈረው፤

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሐማ የሚባል ሰው የንጉሡ ከፍተኛ ሹም ሆነ፤ እርሱም ትምክህተኛ፣ ከንቱና ጨካኝ ሰው ነበር፤ ከመርዶክዮስ በስተቀር ሁሉም ይሰግዱለት ነበር፤ መርዶክዮስም "እኔ አይሁዳዊ ነኝ፤ እኛም የምንሰግደው ለእግዚአብሔር ብቻ ነው" አለ::

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሐማ መርዶክዮስንና አይሁዶችን በሙሉ ለመግደል ቈረጠ፤ ወደ ንጉሡም ሄደ፤ እርሱም፤

"በመንግሥትህ ግዛት ውስጥ ለአንተ ሕግ የማይገዛ አንድ ሕዝብ አለ፤ እንዳጠፋቸው ፍቀድልኝ" አለው:: ንጉሡም ለሐማ ለመንግሥቱ ማህተም የሚጠቀምበትን ቀለበት ሰጠው፤ ሐማም ለአውራጃ ገዢዎቹ አይሁዶቹን በአንድ ቀን እንዲገድሉአቸው በንጉሡ ማህተም አትሞ ትእዛዝ አስተላለፈ፤ አስቴር አይሁዳዊ መሆንዋን ከቤተ መንግሥት ማንም አያውቅም ነበር::

መርዶክዮስና ሕዝቡ ሁሉ በሀዘን ውስጥ ገቡ፤ ምግብ ሳይበሉ በጩኸት ማልቀስ ጀመሩ:: አስቴርም "ምንድን ነው ነገሩ" አለች:: መርዶክዮስም ነገራት፤ እርሱም "ወደ ንጉሡ ግቢና ስለ ሕዝብሽ ሕይወት ለምኚው" አላት:: እርስዋም መልሳ "ንጉሡ እኔን ካስጠራኝ አንድ ወር ሆኖአል፤ ሳልጠራም ወደ እርሱ ብገባ ሊያስገድለኝ ይችላል" አለች:: መርዶክዮስም "እግዚአብሔር ንግሥት ያደረገሽ እኛን ሊያድነን ይሆናል፤ ስለእኛ ለንጉሡ የሚናገር ማንም የለንም" አላት::

ስለዚህ አስቴር ወደ ንጉሡ ገባች፤ ሐማም ከንጉሡ ጋር ነበርና እርሷን ሲያያት ደስ አለው፤ አስቴርም ጊዜው እስኪደርስ ጠበቀች፤ እርሷም በዚያ ምሽት ሁለቱንም እራት ስትጋብዛቸው ነገሩ መልካም ሆነ፤ እርስዋም "ነገም እንድትመጣ" አለችው፤ ሐማም ከንጉሡና ከንግሥቲቱ ጋር ማዕድ በመጋበዙ በጣም ደስ አለው! ዳሩ ግን የመርዶክዮስ ነገር ሁሉንም አበላሸበት፤ ስለዚህ በማግሥቱ መርዶክዮስ የሚሰቀልበትን እንጨት እንዲያዘጋጁ ለአሽከሮቹ ትእዛዝ ሰጠ::



ዳሩ ግን በዚያ ሌሊት ንጉሡ መተኛት አልቻለም፤ የቤተ መንግሥቱን መዛግብት እያገላበጠ ሲያነብ የመርዶክዮስን ስም አገኘ፤ ንጉሡ "እርሱን መሸለም አለብኝ" ብሎ አሰበ፤ ስለዚህ መርዶክዮስ ሐማ እንዳቀደው መሰቀሉ ቀረና የቤተ መንግሥት ክብር ተሰጠው::



ንጉሡም በሚቀጥለው ምሽት በእራት ጊዜ ስለ ንግሥቲቱ ቁንጅና አሰበ፤ እርሱም "የምትፈልጊውን ሁሉ ጠይቂኝ እኔም እሰጥሻለሁ"አላት፤ አስቴርም "እኔና መላው ሕዝቤ ልንገደል ነው፤ ስለእኔና ስለ ሕዝቤ ሕይወት እለምንሃለሁ" አለችው::

ንጉሡም ደነገጠ፤ ይህንን ያደረገ ማነው አለ፤ እርስዋም "ሐማ ነው" አለች፤ ከአሽከሮቹም አንዱ "መርዶክዮስን ለመስቀል እንጨት አዘጋጅቶአል" ሲል በተጨማሪ ተናገረ፤ ንጉሡም"እንግዲያውስ በራሱ እንጨት ላይ እርሱን ስቀሉት" አለ:: እነርሱም እንዲሁ አደረጉ፤

በዚያም ሌሊት አስቴር የሕዝቧን ሁሉ ሕይወት አዳነች፤ ንጉሡም መርዶክዮስን በሐማ ፈንታ ሾመው::

# ኮ ብ ላ ዩ

## ዮናስ

በአጠቃላይ አነጋገር እግዚአብሔር ወደሕዝቡ የሚል ካቸው ነቢያት እግዚአብሔር ያለውን ያደርጉ ነበር፣ ዳሩ ግን አንዱ ከዚህ የተለየ ነበር፣ እርሱም ዮናስ ነበር።

እግዚአብሔር ለዮናስ ተናገረው፣ "ወደ ነነዌ ሂድና የምታደርጉትን ክፋት አይቻለሁ፣ በአርባ ቀን ውስጥ ነነዌ ትጠፋለች በላቸው" አለው።

ነነዌም የአሦር ዋና ከተማ ነበረች፣ አሦራውያ ንም የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ነበሩ፣ ስለዚህ ዮናስ እግዚአብሔር እንደሚያጠፋቸው ለነነዌ ሕዝብ ለመንገር ግድ አልነበረውም!

እርሱም "እግዚአብሔር አፍቃሪ ነው፣ ሰዎችን ይቅር በማለት ሌላ ዕድል ይሰጣቸዋል። ነነዌንም ስለማያጠፋት እኔ እንደ ሞኝ እቆጠራለሁ" ብሎ አሰበ። ዮናስም ወደ ነነዌ ሳይሆን ወደ እስፓኝ በሚሄደው መርከብ ለመሳፈር ወደ ኢዮጴ ወደብ ለመሄድ ተነሣ።







መርከቧም ጉዞ ስትጀምር እግዚአብሔር ታላቅ ማዕበል አመጣ፣ የመርከቡ ነጂና ሠራተኞቹ እጅግ ፈሩ፣

እነርሱም ለመንገደኞቹ "ወደ አምላኮቻችሁ ለነፍሳችሁ ጸልዩ" ብለው ጮኹ። ዮናስም በከባድ እንቅልፍ ተኝቶ ነበር። የመርከቡ ነጂም በኃይል ቀሰቀሰውና "እንደ ሌሎች ጸልይ እንጂ" አለው።

ዮናስም "ወደ እግዚአብሔር መጸለይ አልችልም፣ ከእርሱ እየኮበለልሁ ነኝ፣ ይህንም ማዕበል የላከው እግዚአብሔር ነው፣ እኔን ከመርከቡ አውጥታችሁ ጣሉኝ፣ ማዕበሉም ፀጥ ይልላችኋል" አለው፣

በመጀመሪያ የመርከቡ ነጂ ዝም አለ፣ ዳሩ ግን ማዕበሉ እየባሰበት ሄደ፣ በመጨረሻ ዮናስ እንዳለው አደረገ፣





ዮናስ ወደ ታች እየሰጠመ እየሰጠመ ሲሄድ ባሕሩ ፀጥ አለ፤ በመርከቡም ውስጥ ያሉት ሰዎች ለዮናስ አምላክ ምሥጋና አቀረቡ፤ ዮናስም ሰጥሞ የሚቀር መሰለው፤ ማዕበሉ ሰውነቱን ሲሸፍነው ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፤ እግዚአብሔርም ትልቅ አሣ ላከና ከነሕይወቱ እንዲውጠው አደረገ።

ዮናስም ለሦስት ቀናት በአሣ ውስጥ በጨለማ ሲቆይ ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ አዘነ፤ ተናዘዘም፤ ከዚያም እግዚአብሔር ቃሉን ላከና አሣው ዮናስን በባሕሩ ዳርቻ ተፋው፤ ፀሐይንም በማየቱ እንደዚያ ጊዜ ተደስቶ አያውቅም ነበር! እርሱም የእግዚአብሔርን መልእክት ለመንገር በቀጥታ ወደ ነነዌ ሄደ፤ "በአርባ ቀን ውስጥ ነነዌ ትጠፋለች" አለ።

ሕዝቡም እግዚአብሔር ያለውን አመኑ፤ እነርሱም ከዝቅተኛው አገልጋይ አንስቶ በቤተ መንግሥት እስካለው ንጉሥ ድረስ መንገዳቸውን አስተካከሉ፤ እግዚአብሔር ተደሰተ፤ ክፉ መንገዳቸውንም ስለተዉ አላጠፋቸውም።

ዮናስም ተቆጥቶና ተበሳጭቶ ከከተማዋ ውጭ ተቀመጠ፤ እርሱም ለእግዚአብሔር "እኔ ያልኩት ይህን አልነበረምን? ለመሸሽ የሞከርኩትም ለዚህ ነበር፤ አንተ ቸር መሆንክን አውቄ ነበር፤ ስለዚህ አሁን ግደለኝ!" አለ። እግዚአብሔር ግን ዮናስን እንዲሞት አላደረገም፤ ይልቁንስ ከፀሐይ ሙቀት የምትከልለው አንዲት ዛፍን አሳደገለት፤ ዮናስም ተሻለው፤ በሚቀጥለው ቀን ዛፍዋ ደረቀችና ፀሐይ በዮናስ ላይ በሀይል ወረደበት።



ዮናስም "በዚያች ዛፍ ተደስቼ ነበር፤ አሁን ግን በመድረቋ አዝናለሁ" አለ። እግዚአብሔርም "ልትማር ጀምረሃል፤ አንተ ላልደከምህባት ዛፍ አዝነሃል፤ አላሳደግሃትም፤ እኔስ የእንስሳቱን ተወውና በነነዌ ለሚገኙ ለእነዚያ ሁሉ ሰዎችና ለየዋህ ሕፃናት አላዝንምን? ሕይወትን ሰጥኋቸው፤ እነርሱንም በመጠበቅ ብዙ ችግር አይቻለሁ" አለው። ዮናስም በመጨረሻው ሊገነዘብ ቻለ።